# በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተናና ግምገማ

ለድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ቴሴስ
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አማርኛን በማስተማር
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በ
አቴነሽ ተገኝ
ሰኔ ፣ 1986

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት
ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ
ይዘቶች ትንተናና ግምገማ

በ
አቴነሽ ተገኝ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

ጥናቱን ያጸደቁት

[illegible]
አማካሪ

Marew Zewdie (Dr.)
ፈታኝ

Haile Michael Aberra Dr
ፈታኝ

# ማውጫ

ርእስ ገጽ


አህጽሮተ ጥናት ........................... i
ምስጋና ........................... ii
የሠንጠረዥና የግራፍ ማውጫ ........................... iii
ምዕራፍ ፩ : መግቢያ ........................... 1
1.1 የጥናቱ አላማ ........................... 1
1.2 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................... 1
1.3 ወሰነ ጥናት ........................... 1
1.4 ሰበበ ጥናት ........................... 2
1.5 የቃላት መፍቻ ........................... 4
ምዕራፍ 2:— የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........................... 5
2.1 ሀገርኛ ሥራዎች ........................... 5
የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ........................... 5
2.2 ንድፈ ሀሳባዊ መንደርደሪያዎች ........................... 8
2.2.1 መርሀ ትምህርት ........................... 8
_ ትርጉም ........................... 8
_ አስፈላጊነት ........................... 9
_ ዓይነት ........................... 11
_ አዘገጃጀት ........................... 13
2.2.2 የማዳመጥ ክሂል ........................... 18
_ የማዳመጥ ትምህርት ........................... 18
_ የማዳመጥ ይዘት ምርጫ........................... 22
_ የማዳመጥ ይዘት ቅንብር ........................... 26
ምዕራፍ 3 :— የአጠናን ዘዴ ........................... 28
3.1 ይዘቶችን መለየት መተንተንና መገምገም... 28
3.2 መጠይቆችን ማዘጋጀት ........................... 28
3.3 ናሙና መምረጥና መጠይቅን ማስሞላት..... 29


ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ርእስ ገጽ


ምዕራፍ 4:- ጥናቱና ውጤት .................. 32

4.1 የይዘት ትንተናና ግምገማ ውጤት ....... 32

4.2 የመጠይቆች ምላሽ ................ 45

4.2.1 ከተማሪው መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ....... 46

4.2.2 ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ....... 62

4.2.3 ከመርሀ ትምህርት ባለሙያው የተገኘ ምላሽ. 72

4.3 የመጠይቆች ምላሽ ትንተናና ንጽጽር .... 75

ምዕራፍ 5:- ማጠቃለያና ጥቆማ ................ 81

5.1 ማጠቃለያ ...................... 81

5.2 ጥቆማ ....................... 85

የዋቢ መጸሀፍት ዝርዝር ...................... 86

አባሪዎች:- ......................... 89

አባሪ 1 : የተማሪው መጠይቅ ............

አባሪ 2 : የመምህሩ መጠይቅ ............

አባሪ 3 : የመርሀ ትምህርት ባለሙያው መጠይቅ.

አባሪ 4 : የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርትን አወቃቀር የሚያሳይ ሠንጠረዥ ...............

አባሪ 5 : ጥናቱ ያተኮረበትን የመርሀ ትምህርቱን ክፍል የሚያሳይ ሠንጠረዥ .......

አባሪ 6 : በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡ መምሪያዎች - የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ከቀረቡ ይዘቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው....

አባሪ 7 : በአዲስ አበባ የሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ዝርዝር በፊደል ተራ ቀደም ተከተላቸው መሠረት.......

## አህጽሮተ ጥናት

በዚህ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ለመተንተንና ለመገምገም፣ ከተማሪዎች ፍላጎት ችሎታና ዝንባሌ ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ተሞክሯል ::

ጥናቱም ይዘቶቹን በለማዳመጥ ክሂል ከተለያዩ ምሁራን ከተገኙ ንድፈ ሃሳቦችና ከተማሪዎች ፍላጎት አሰሳ ከተገኙ ውጤቶች ጋር በማገናዘብ ተጠንቷል :: ከጥናቱም የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል ::

- በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ከተማሪዎቹ ፍላጎት አንጻር ሲታዩ በጣም አነስተኛና የተለያዩ የማዳመጥ አይነቶችን ያላካተቱ ናቸው ::
- ይዘቶቹ የተኛውን ክሂል ለማዳበር እንደተፈለገ በግልጽና በዝርዝር አያሳዩም :: ይዘቶቹም ሆኑ በየይዘቶቹ አንጻር የቀረቡት የክፍል ውስጥ ልምምዶች የተገለጹበት ቋንቋ ግልጽነት የጎደለው በመሆኑና ከዚህም ጋር የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን የሚያዳብሩ ይዘቶች በአንድነት በመቀረባቸው በየትኛው ክሂል ላይ ሊተኮር እንደተፈለገ አሻሚ ትርጉም ይሰጣሉ ::
- ይዘቶቹ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡበት ቅደም ተከተል የክብደት ደረጃቸውን የጠበቀ አይደለም :: በአንዱ ሴሚስተር በተከታታይ በቀረቡትም ሆነ በአንደኛውና በሁለተኛው ሴሚስተር በቀረቡት ይዘቶች መካከል የክብደት ደረጃቸው አለመጠበቅ በግልጽ ታይቷል ::
- ይዘቶቹ ግልጽነት በጎደለው ሁኔታ በቃላት ተድበስብሰው ቢገለጹም አንዳንዱ የማዳመጥ ዋና ንኡሳን ክሂሎችን ለመዳሰስ ሞክረዋል፤ በዚህም በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማዳመጥ ትምህርት ሊተኮርባቸው በሚገቡ የማዳመጥ አይነቶች ላይ አተኩረዋል :: ይህም በተማሪዎች የፍላጎት አሰሳ የተገኘው መረጃ ከሚያሳየው የተማሪዎቹ አፍ መፍቻ ቋንቋ 92.6 % አማርኛ /ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ/ ከመሆኑ ጋር የሚጣጣምና በይዘቶቹ ላይ የታየ ጠንካራ ጎን ነው ::

ባጠቃላይ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ተገቢውን ትኩረት አላገኘም :: የማዳመጥ ክሂል በአጠቃላይ አላማ፣ በዝርዝር አላማና በይዘት ምርጫ ደረጃ ከመናገር ክሂል ጋር ተደርቦ በመቅረብ ፈንታ ራሱን ችሎ መቅረቡና በርካታ ይዘቶችና ልምምዶች ሊቀርቡበት ያስፈልጋል :: ከዚህም ጋር የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት፣ ችሎታና [illegible] የቋንቋ [illegible] ይዘቶችን መርጦ ማቅረብ ያስፈልጋል ::

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን መስዋእት በማድረግ ረቂቁን በማረም ገንቢ ሃሳቦችን በመስጠት ለረዱኝ አማካሪዬ ለዶክተር ደጀኔ ለታ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዱ መጠይቆችን በማዘጋጀበት ጊዜ መጠይቆችን በማረምና ገንቢ አስተያየታቸውን በመስጠት ለተባበሩኝ ለዶክተር ታደለ አጋሙ ፤ ይህን ጥናት በምሰራበት ጊዜ ሁሉ በሃሳብና በቁሳቁስ ረገድ ያጋጠሙኝን ችግሮች በመካፈል ለረዱኝና ላበረታቱኝ ለአቶ ወልደሰላሴ አቡዬና ለወይዘሮ ሣሌሀት አወል ፤ እንዲሁም ጥናቱን በረቂቅ አንስቶ እስከ መጨረሻው ተየባ ድረስ ያለ መታከት በመተየብ ለረዱኝ ለወ/ት ብዙወርቅ ወ/ጻድቅንና ለወ/ት ፋጡማ አወል ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

ርእስ ገጽ

## የሠንጠረዦና የግራፍ ማውጫ


| | | | |
|---|---|---|---|
| ሠንጠረዥ | 1: | የማዳመጥን ክሂሎ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለማዳበር በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ................ | 30 |
| ሠንጠረዥ | 2: | በየአጠቃላይ አላማው ሥር የቀረቡ ይዘቶች ብዛት ................ | 32 |
| ሠንጠረዥ | 3: | በየሴሚስተሩ የቀረቡ የማዳመጥ ይዘቶች. | 34 |
| ሠንጠረዥ | 4: | የተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ ...... | 46 |
| ሠንጠረዥ | 5: | የተማሪዎች እድሜ ............ | 46 |
| ሠንጠረዥ | 6: | የተማሪዎች ፆታ ............ | 47 |
| ሠንጠረዥ | 7: | የማዳመጥን ክሂሎ ማዳበር ለሚለው አላማ የተሰጠ ምላሽ ............ | 48 |
| ሠንጠረዥ | 8: | ተማሪዎች የሚያዘውትሯቸው የማዳመጥ ተግባራት.................... | 50 |
| ሠንጠረዥ | 9: | የማዳመጥ ጉዳይ የአቀራረብ ዝንባሌ .. | 51 |
| ሠንጠረዥ | 10: | የተማሪዎች የማዳመጥ ችግር ....... | 52 |
| ሠንጠረዥ | 11: | የማዳመጥ ይዘቶች ጠቀሜታ ........ | 54 |
| ሠንጠረዥ | 12: | የማዳመጥ ችሎታ የመተማመን መጠን ... | 55 |
| ሠንጠረዥ | 13: | በቋንቋ ክሂሎች የመጠቀም ችሎታ .... | 56 |
| ሠንጠረዥ | 14: | የክሂሎች መዳበር የሚያስገኘው ጠቀሜታ መጠን .................... | 57 |
| ሠንጠረዥ | 15: | የተማሪዎች ዝንባሌ :- የሚዳመጥ ጉዳይ. | 58 |
| ሠንጠረዥ | 16: | የተማሪዎች የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ... | 60 |
| ሠንጠረዥ | 17: | የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ ማጠቃለያ ................. | 61 |

| ርእስ | | | ገጽ |
|---|---|---|---|
| ሠንጠረዥ | 13 | በቋንቋ ክሂሎች የመጠቀም ችሎታ ......... | 56 |
| ሠንጠረዥ | 14 | የክሂሎች መዳበር የሚያስገኘው ጠቀሜታ መጠን. | 57 |
| ሠንጠረዥ | 15 | የተማሪዎች ዝንባሌ :— የሚዳመጥ ጉዳይ ... | 58 |
| ሠንጠረዥ | 16 | የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ...... | 60 |
| ሠንጠረዥ | 17 | የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ ማጠቃለያ. | 61 |
| ሠንጠረዥ | 18 | የተማሪዎች የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች የመረዳት ሁኔታ በመምህራን አይን .......... | 62 |
| ሠንጠረዥ | 19 | መምህራን ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩት ክሂል | 63 |
| ሠንጠረዥ | 20 | የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ዝርዝር አላማዎች ብዛት .................... | 64 |
| ሠንጠረዥ | 21 | የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ይዘቶች ብዛት ........................ | 66 |
| ሠንጠረዥ | 22 | የተማሪዎች የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ በመምህራን ምዘና ........................ | 68 |
| ሠንጠረዥ | 23 | የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ በመምህራን ምዘና — ማጠቃለያ ............. | 69 |
| ሠንጠረዥ | 24 | የተማሪዎች አዳምጦ የመረዳት መጠን ...... | 70 |
| ሠንጠረዥ | 25 | በአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ችሎታ ለሌሎች ትምህርቶች ያለው ጠቀሜታ ............... | 71 |
| ሠንጠረዥ | 26 | የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች የብቃት ደረጃ በመርሀ ትምህርት ባለሙያዎች ምዘና | 74 |
| ግራፍ | 1 | የይዘቶችን ስርጭት የሚያሣይ መስመራዊ ግራፍ. | 33 |

# ምዕራፍ 1 : መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዓላማ

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ላይ የቋንቋው ትምህርት አላማዎች ተገልጸዋል:: ከአላማዎቹ አንዱ የማዳመጥን ክሂል ማዳበር ሲሆን ይህም "የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራል" ተብሎ ተገልጿል / ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1984*1/ :: ከዚሁ አላማ ሥርም የተማሪውን የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች ያዳብራሉ ተብለው የተመረጡ ይዘቶች ቀርበዋል :: የዚህ ጥናት አላማ እነዚህ ይዘቶች የማዳመጥ ክሂልን የማዳበር ብቃታቸው ምን ያህል ነው ? ይዘቶቹ የተማሪውን ፍላጎት መሠረት አድርገው የተመረጡ ናቸው? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ መፈለግ ይሆናል ::

## 1.2 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የሚመረጥ ይዘት እንዴት ያለ መሆን እንዳለበት በተለያዩ ምሁራን የተጠቆሙትን [illegible] ሃሳቦች መሠረት በማድረግ በዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡትን የማዳመጥ ክሂል ይዘቶች ጠንካራና ደካማ ጎን ለይቶ ለማሳየት ይሞክራል፤ ይዘቶቹ ከተማሪው ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለመሆናቸውን በተጨባጭ ለማረጋገጥ ይሞክራል :: በተጨማሪም ለመርሀ ትምህርት ዝግጅት በመረጃነት ሊያገለግልና ተመሳሳይ ጥናት ማድረግ ለሚሹ መነሻ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አለ ::

## 1.3 ወሰነ ጥናት

ይህ ጥናት በ1984 ዓ.ም በታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ያዳብራሉ ተብለው በቀረቡ ይዘቶች ላይ ያተኮረ ጥናት ነው :: ጥናቱ በአዲስ አበባ በሚገኙ በመንግስት

---

* በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሰው ጊዜ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር /እ.ኤ.አ/ ተብሎ ካልተገለጸ ወይም በውጭ ጸሀፍት ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሰ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር የተገለጸ መሆኑ ይታወቅ ::

በሕዝብና በግል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመደበኛ ትምህርት ላይ የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን፣ ቀደም ሲል ወይም ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የነበሩትንና የሆኑትን እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት አዘጋጆችን ያካተተ ነው ::

## 1.4 ሰበበ — ጥናት

የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶችን በተመለከተ ቀደም ሲል አንዳንድ ጥናቶች ቢቀርቡም፣ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ለቋንቋው ትምህርት የተመደበውን የክፍለ ጊዜ መጠን፣ የመምህራኖችን የሥልጠና ደረጃ፣ የትምህርቱን አሰጣጥ ይዘት በጥቅሉ የሚያካትቱ ናቸው ::

በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ የቋንቋ ሴሚናሮችና ሲምፖዚየሞች ላይ፣ እንዲሁም በሊትሬቸር ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍል የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች ለዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ባቀረቧቸው ጥናቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘት ላይ የሚታዩ ችግሮች ተነስተዋል :: በነዚህ ጥናቶች ላይ በአብዛኛው የተተኮረባቸው በፈተናዎችና በመማሪያ መጽሀፍት ውስጥ በቀረቡ ምንባቦችና መልመጃዎች ላይ ነው ::

መማሪያ መጽሀፍትም ሆኑ ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ ለክፍሉ የተዘጋጀውን መርሀ ትምህርት መሠረት አድርገው ይዘጋጃሉ :: ስለዚህ በመጽሀፍቱና በፈተናዎቹ ላይ የተጠቀሱትን ዕክሎች ለማስወገድ አስቀድሞ መርሀ ትምህርቱን መመርመር፣ በመርሀ ትምህርቱ ላይ የሚታየውን ጠንካራና ደካማ ጎን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ማጥናት ያስፈልጋል :: በመማሪያ መጽሀፍቱና በፈተናዎቹ ላይ የታየው ደካማ ጎን ምናልባትም መንስኤው መርሀ ትምህርቱ ሊሆን ይችላል :: ከዚህም ጋር የአማርኛ ቋንቋ ስርአተ

ትምህርትን አሳማና ይዘት ከመረመሩ ጽሁፎች ለመረዳት እንደተቻለው በተለያዩ ጊዜያት በወጡት ስርአተ ትምህርቶች ውስጥ የማዳመጥ ክሂል እምብዛም ትኩረት አላገኘም :: ስለዚህም በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ማጥናትና መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ::

...// 4

## 1.5 : የቃላት ፍቺ

የሚከተሉት የአማርኛ ትርጉሞች ለእንግሊዝኛው ስያሜ ይመጥናሉ በማለት በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ናቸው ናቸው ::

| | |
|---|---|
| Abstract | = አህጽሮት ጥናት |
| Communication | = ተግባቦት |
| Curricculum | = ስርአተ ትምህርት |
| Grammatical /Structural Syllabus | = ሰዋሰዋዊ / አገባባዊ መርሀ ትምህርት |
| Interactional Listening | = ለማህበራዊ ምልልስ ማዳመጥ |
| Notional /Functional Syllabus | = አሳብያዊ / ግብራዊ መርሀ ትምህርት |
| Post- Listening | = ድህረ ማዳመጥ |
| Pre- Listening | = ቅድመ ማዳመጥ |
| Syllabus | = መርሀ ትምህርት |
| Transactional Listening | = ለመረጃ መሸት ማዳመጥ |
| While- Listenning | = እያዳመጡ |

...// 5

## ምዕራፍ 2:- የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

### 2.1 ሀገርኛ ሥራዎች

### የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት

በየጊዜው ተዘጋጅተው በሥራ ላይ የዋሉት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች በመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች ውስጥ ከመማሪያ መጽሀፍትና ከፈተናዎች ጋር ሊኖራቸው ከሚገባ ዝምድና አንጻር በጥቂቱ ተዳስሰዋል ፡፡ ለአብነት ያህል ደመቀ ብርሃኑ /1973/ ፡ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናና የስርዓተ ትምህርት /ከ1969 – 72/ ፤ ሰለሞን ደበበ /1976/ ፡ በአዲስ አበባ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ1975 ዓ/ም የተሰጡ የአማርኛ ፈተናዎች ግምገማ ፡ የሚሉ ይገኙበታል ፡፡

በነዚህ ጽሁፎች ውስጥ የቋንቋ ትምህርቱን ይዘት በተመለከተ ይዘቶቹ ከተማሪዎቹ ገጠመኝ የራቁ፤ ለተማሪው ፍላጎት፤ ልምድና አካባቢ ተገቢነት የሌላቸውና አቀራረባቸውም አንድ ዓይነት በመሆኑ የተማሪዎቹን ስሜት የማይቀሰቅሱ መሆናቸው ተጠቅሷል ፡፡

እንዲሁም በ1982 ዓ/ም ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ሲምፖዚየም በቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች ላይ የቋንቋው ምሁራን የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥን፤ ስርአተ ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሀፍቱን በተመለከተ አንዳንድ የግምገማ ነጥቦችንና አስተያየቶችን ሰንዝረዋል ፡፡ ከነዚሁም ውስጥ ፈቃደ አዘዘ /1982 / ፤ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ስርአተ ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ በ1994 ሲዘጋጅ የትምህርቱ ይዘት የሰዋሰው፤ የንባብና የድርሰት ትምህርት መሆኑን ፡ የስርአተ ትምህርት ታሪክ በኢትዮጵያ ፡ የተሰኘውን ረቂቅ ጽሁፍ በመጥቀስ አስፍረዋል /1982 :1 / ፡፡

ለምሳሌ በትምህርት ቤት የምናገኛቸው የተማሪዎች ዕድሜ በአስተሳሰብ ከመብሰሉና የሚያስፈልጋቸውን የቋንቋ ትምህርት ለይተው ከማወቅ ጋር ሊኖር የሚችለው ሁኔታ፣ የትምህርቱ ባህል — ተማሪው ሁሉን ነገር ከመምህሩ የሚጠብቅ መሆኑ፣ እነዚህና የመሳሰሉት ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ ።

አስቀድሞ የሚዘጋጅ መርሀ ትምህርት የትምህርቱን ግብና ከግቡ ሊያደርሱ የሚችሉ አማራጮችን አስቀድሞ በመምረጥ ጊዜንና ገንዘብን ይቆጥባል፣ ለትምህርት የሚቀርበው ይዘት ደረጃ በደረጃና በቅደም ተከተል እያደገ እንዲሄድ ያደርጋል፣ ለመምህሩ የሚያስተምርበትን፣ ለተማሪውም የሚማርበትን አላማና ግብ አስቀድሞ ማሳወቅ ወደ ተፈለገው ግብ እንዲገሰግሱ ይመራል ።

> በየጊዜው የቋንቋና ቋንቋን የማስተማር ቲዎሪዎች ውስብስብ እየሆኑ ከመምጣታቸውና የተማሪዎች ፍላጐት፣ ዝንባሌና ምኞት በጣም የተለያየ እየሆነ በመምጣቱ ጋር የሁለተኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት አስፈላጊነትና ጠቀሜታ እየጐላ መጥቷል ። ...... መርሀ ትምህርት በአሁኑ ጊዜ የሚታየው፣ መምህሩ በመርሀ ትምህርት አዘጋጅ እየታገዘ በተማሪዎች ፍላጐትና አላማ እና በክፍል ውስጥ በሚከናወኑ የመማር ማስተማር ክንውኖች መሀከል መስማማትን የሚፈጥር መሳሪያ ሆኖ ነው / ያልደን ፣ 1987 : 85—86 / ።

...// 11

<u>አይነት</u>

የተለያዩ የመርሀ ትምህርት አይነቶች በየጊዜው በተለያዩ ምሁራን ሲዘጋጁ፣ አገልግሎት ላይ ሲውሉና ሲተቹባቸው፣ አዳዲስ የቋንቋ ትምህርት ጽንሰ ሃሳቦች በፈለቁ ቁጥር ቀደም ብሎ ሲሰራባቸው የነበሩት የመርሀ ትምህርት አይነቶች ሲሻሻሉና በሌላም ሲተኩ ቆይተዋል ። በተለያዩ የመርሀ ትምህርት አይነቶች መሀከል የሚኖረው መሠረታዊ ልዩነት የቋንቋ ትምህርት ይዘትንና የማስተማር ዘዴን በተመለከተ የሚታየው ልዩነት ነው ። ለምሳሌ በቀስቃሽ/አገባባዊ መርሀ ትምህርት በይዘት መረጣ ረገድ በቋንቋው የድምጾች፣ የቃላት፣ የዐረፍተ ነገር ቀንበር፣ በምእላዳች፣ በአገባብና በመሣሰሉት ላይ ሲያተኩር ዘዴውም እነዚህን ለተማሪው በማስጠናት ላይ ያተኮረ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ አሰቢያዊ/ገብራዊ መርሀ ትምህርት ይዘቶቹ በቋንቋው ተግባቦታዊ አገልግሎት ላይ ያተኮሩና የቋንቋ ክሂሎችን የሚያዳብሩ ሲሆኑ፣ የማስተማር ዘዴውም ተማሪው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ በቋንቋው መግባባት እንዲችልና በቋንቋው እንዲጠቀም በማለማመዱ ላይ ያተኮረ ነው ።

የመርሀ ትምህርት አይነቶች በየጊዜው ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቷል ። በይዘቱ ላይ ያተኮረ፣ ተርጓሜ ላይ ያተኮረ፣ ማህበራዊ አገልግሎት ላይ ያተኮረ፣ መነጋገሪያ ርዕስ ጉዳይ ላይ ያተኮረ፣ ወዘተ... ። ዋና ዋና የሚባሉት የመርሀ ትምህርት አይነቶች በቀስቃሽ/ አገባባዊ፣ ... ሁኔታዊ፣ አሳቢያዊ/ገብራዊ መርሀ ትምህርቶች ናቸው ።

አንዱ አይነት መርሀ ትምህርት ሁሉንም የትምህርት አላማዎች ከግብ ማድረስ በማይችልበት ሁኔታ የተለያዩ የመርሀ ትምህርት አይነቶችን በማቀናጀት ለመጠቀም የሚደረግ ጥረት እንዳለ ኋይት ሲገልጽ ፡-

> በመርሀ ትምህርት ንድፍ ሃሳብ ምክንያት ሳይሆን
> በማስተማር የዕለት ተዕለት ሂደት ምክንያት አንዱ
> የተወሰነ አይነት መርሀ ትምህርት ፍላጎታቸውን ሊያሟላ
> ባለመቻሉ፣ ከተለያዩ አይነት መርሀ ትምህርቶች
> የተውጣጣ መርሀ ትምህርት መጠቀም የብዙዎችን
> ፍላጎት እያሟላ መጥቷል /ኋይት ፣ 1988 :111/ ።

እነ ሀቺንሰን፣ አበያን 1985ን በመጥቀስ እንዳብራሩት፡—

> ዋናው ጉዳይ የትኛው የመርሀ ትምህርት አይነት ይቀደም የሚለው ሳይሆን የተለያዩ መርሀ ትምህርቶችን/ ተግባራዊ፣ አሳቢያዊ፣ ሁኔታዊ፣ ርዕስ ጉዳያዊ፣ ሥነ ድምጻዊ፣ ጽርጉማዊ፣ አገባባዊ፣ ክሂሎዊ/ አቀናጅቶ ስሜት ሊሰጥ የሚችል የትምህርት ፕሮግራም ማዘጋጀት መቻሉ ላይ ነው ፡፡ /ሀቺንሰንና ዋተርስ 1987፡89/ ፡፡

ከሁሉም በላይ የመርሀ ትምህርት አይነት ምርጫን በተመለከተ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ የታቀደውን አላማ ከግብ የሚያደርስ መርሀ ትምህርት ማዘጋጀት መቻሉ ነው ፡፡ የመርሀ ትምህርት አይነት ምርጫም የሚወሰነው በቋንቋው ትምህርት አላማ ላይ ተንተርሶ ይሆናል ፡፡

የትኛውን የመርሀ ትምህርት አይነት እንጠቀም ለሚለው ይህ ኛው ወይም ያኛው መርሀ ትምህርት ጥሩ ነው ብሎ በደፈናው መወሰን ትክክለኛ ውሣኔ አይሆንም ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የቋንቋ አገልግሎት ነጣጥሎ የማቀረቡ ሁኔታ እየቀረ፣ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ የግ ንኙነትና የመግባባት ችሎታን ማዳበር የሚለው ትኩረት እያገኘ መጥ ቷል ፡፡ ለዚህም በተማሪው ፍላጎት ላይ በመመስረት የተገባበት ክሂልን የሚያዳብሩ ይዘቶችን የያዘ መርሀ ትምህርት የማዘጋጀት አስፈላጊነት አጠያያቂ አይሆንም ፡፡

<u>አዘገጃጀት</u>

የቋንቋ መርሀ ትምህርት ለማዘጋጀት አንዳንድ ቅድመ ዝግጅቶችን ማድረግ ያስፈልጋል ። ዋና ዋናዎቹ የአገሪቱን የቋንቋ ፖሊሲ ማወቅ፣ ለትምህርት የሚቀርበው ቋንቋ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን አገልግሎት ፦ የጋራ መግባቢያ ፣ ለተወሰኑ ጉዳዮች የሚያገለግል፣ የማስተማሪያ ቋንቋ፣ ወዘተ... መሆኑን ማወቅ፣ የተማሪውን ዕድሜ፣ የትምህርት ዓራ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ማወቅ ናቸው ።

የመንግሥት የቋንቋ ፖሊሲ ቋንቋው ለማን ? ለትምህርት ይቀረብ ? ለምን አላማ ይማራት ? በትምህርት ቤት ምን ያህል ክፍለ ጊዜ ይመደብለት ? በሚያስፈልጉት የትምህርት መሣሪያዎች ረገድ ምን ያህል ወጪ ይመደብለት ? በሚሉት ውሳኔዎች ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል ። ለትምህርት የሚቀርበው ይዘት በኅብረተሰቡ ውስጥ ባለው የቋንቋ አጠቃቀም ላይ የተመሠረተና ተማሪው በኅብረተሰቡ ውስጥ ሊገለገልባቸው የሚችለውን የቋንቋ ግብራዊ ክሂሎች የሚያዳብር እንዲሆን ቋንቋው በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚኖረውን አገልግሎት ማወቅ አስፈላጊ ነው ። የተማሪው ዕድሜ ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ የመካሰሉትን ማወቅ ለተማሪው የሚቀርብለትን ይዘት በመወሰን ረገድ፣ ከተማሪው ሥነ-ልቦና፣ ችሎታ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ አንጻር ከማሟና ተማሪው አጥቅም ላይ ሊያውለው የሚችለው ለምምድ የሚቀርብበት ይዘት ለመምረጥ ይረዳል ::

አንድ የቋንቋ መርሀ ትምህርት አዘጋጅ መርሀ ትምህርት ለማዘጋጀት ሲነሳ ከላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ ጉዳዮች በግንዛቤ ማስገባት ይኖርበታል ። ከዚህም ጋር መርሀ ትምህርት ለአዘጋጁ ተከታታይ የክንዋኔ ደረጃዎችን እንደሚከተል ማወቅ ይሻል ። ሬጅደብ፣ ታባ 1962ን በመጥቀስ እንዳስፈረው የአንድ የተወሰነ ትምህርትን መርሀ ትምህርት የሚያዘጋጅ ባለሙያ የሚከተሉትን ደረጃዎች ሊከተል ይገባል፦

...// 14

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

1. የተማሪውን ፍላጎት ማጥናት ፣
2. አላማ መንደፍ ፣
3. ይዘት መምረጥ፣
4. ይዘት ማቀናበር ፣
5. የትምህርት ልምድ መምረጥ፣
6. የትምህርት ልምዶችን ማቀናበር፣
7. ምን እንደሚገመገምና እንዴት እንደሚገመገም መግለጽ፣ / ሪቻርድስ ፣ 1990 ፣ 8 / ።

የቋንቋ ትምህርትን አላማና ይዘት ከመወሰን በፊት ተማሪው በቋንቋው በት/ቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዴትና ለምን ለምን ጉዳዮች እንደሚጠቀም ፍላጎቱን ማጥናት በመርሀ ትምህርት ዝግጅት ወቅት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው ። የፍላጎት ጥናት በሰፋት የሚታወቀው ቋንቋን ለተወሰነ ጉዳይ የሚማሩ ከፍሎችን ፍላጎት በማጥናት ቢሆንም በአጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት መስክም የፍላጎት ጥናት ማድረግ አስፈላጊነቱና ጠቀሜታው እየጎላ መጥቷል ።

> ተማሪው እንግሊዝኛን ለምን መማር ፈለገ ? የሚለው ጥያቄ ቋንቋውን ለተወሰነ አላማ ለሚማሩት ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ለሚማሩትም ምላሽ ማግኘት ያለበት ጥያቄ ነው ። ሁሉም ትምህርቶች ሊገለጹ በሚችሉ በአንዱ አይነት ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። ... የትኛውም ትምህርት በተማሪው ፍላጎት ትንተና ላይ መመስረት ይኖርበታል / ሀቺንሰንና ዎተርስ፣ 1987 : 53 /

የተማሪውን ፍላጎት ማወቅ ሲባል ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ይይዛል ። አንደኛው ተማሪው ቋንቋውን ለመማር ምን ማድረግ እንዳለበት፣ በቋንቋው ለመጠቀም እንዲችል ምን ምን እውቀቶችና ችሎታዎች እንደሚያስፈልጉት ማወቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚታየውን የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅንና ከዚህም በመነሳት ለተማሪው የሚያስፈልገውን የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅ ነው ። /ሀቺንሰንና ዋተርስ 1987 / ።

ስለ ተማሪው ፍላጎት በቀላሉ ማወቅ የሚቻል ባይሆንም መጠይቆችን አዘጋጅቶ በተማሪው በራሱ በማስሞላት፣ የቋንቋ መምህራንን ስለ ተማሪዎቻቸው ችሎታና ዝንባሌ በመጠየቅ፣ ቋንቋው በትምህርት ቤትና በሥራ መስክ እንዲሁም በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን አገልግሎት በማጥናት በተለያዩ መንገዶች መረጃ ማሰባሰብ ይቻላል ። በነዚህ መንገዶች መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ከመረጃዎቹ በተገኘው ውጤት መሠረት የቋንቋ ትምህርት አላማ ይነደፋል ።

የተማሪውን ፍላጎት መሠረት አድርገው የተነደፉት አላማዎች ወደ ትምህርት ይዘት ይተረጎማሉ ። ማለት አላማውን በግቡ ለማድረስ ለተማሪው በተለያየ ሁኔታ እየቀረቡለት ለምምዱ የሚያደርጋቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ይመረጣሉ ። ይዘት ምርጫንና ቅንብርን አጣምሮ ይይዛል ።

ለተማሪው የሚቀርበው የትምህርት ይዘት አመራረጥና ቅንብር በመርሀ ትምህርት ዝግጅት ወቅት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው ።

> ቋንቋን የማስተማር ተግባር ' ጥሬ ' የመርሀ ትምህርት አይነት ከመምረጥ በላይ የሚሄድ ነው ። ከሁሉም በላይ ይዘትን ለመምረጥና ለማቀናበር ረጅም ጊዜና ጥረት ሊደረግ ይገባል / ኑይት፣ 1988 ፡ 111 / ።

ADDIS ABABA UNIV...
ILS LIBRARY



የይዘት ምርጫ በመርሀ ትምህርት ውስጥ የሚቀርበው የቋንቋ ክሂል የትኛው ነው ? የሚለውን ጥያቄ ሲመልስ የይዘት ቅንብር ደግሞ በመርሀ ትምህርት ውስጥ የሚቀርበው የቋንቋ ክሂል በምን ቅደም ተከተል ይቀርባል ? ቅደም ተከተሉንስ ለመወሰን የምንጠቀመው መመዘኛ ምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል ::

በትምህርት ቤት የሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ይዘት የተመረጠ መሆን ይኖርበታል :: ሁሉንም የቋንቋ ክሂል እና ቀርብም :: ለይዘት ምርጫ መሠረት የሚሆነን የተማሪው ፍላጎት መሆኑ ተደጋግሞ ተነስቷል :: ለዚህም ነው የፍላጎት አሰሳ ማድረግ የሚያስፈልገው :: የይዘት ብቃትና ተገቢነት ከሚመዘንባቸው መመዘኛዎች አንዱና ዋነኛው ከተማሪው ፍላጎት ጋር መጣጣሙ ነው ::ለትምህርት የሚቀርቡት ይዘቶች ለተማሪው ከሚሰጡት ጥቅምና ፍላጐቱን ከማሟላታቸው አንጻር ይታያሉ :: ዊድውሰን ስለዚሁ ጉዳይ ዊልኪንስ 1976ን ጠቅሶ ያሰፈረውን ብንመለከት :-

> ምን ማስተማር እንደሚገባ የመወሰን ሂደት
> ተማሪዎች በቋንቋው ለመግባባት በአብዛኛው
> የሚጠቀሙበት የትኛውን የቋንቋ ክሂል ነው ?
> ለሚለው ጥያቄ ትኩረት በመስጠት ላይ
> የተመሠረተ ይሆናል :: ይላል / ዊድውሰን፣1990:131/::

የቋንቋ ትምህርት ይዘት ተማሪዎቹ በዕለት ተለት ኑሮአቸው ወይም ለአንዱ ለተወሰነ ጉዳይ ሊጠቀሙበት የሚያስፈልጋቸው መሆን ይኖርበታል ::ከቋንቋ ክፍል ውጭ አጥቀም ላይ የማያውሉትን የቋንቋ ትምህርት ይዘት ማቅረቡ አምብዛም አርባና አይኖረውም ::

የተመረጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የተማሪውን ችሎታ መሠረት በማድረግ የክብደት ደረጃቸውን ጠብቀው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከግልጽ ወደ ውስብስብ ደረጃ በደረጃ እያደጉ በሚሄዱበት ቅደም ተከተል ይቀናበራሉ ::

ይዘቶች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑባቸው የትምህርት ልምዶች ቋንቋው በነበረ ክበቡ ውስጥ ባለው አገልግሎት ላይ ተመሥርተው ይዘጋጃሉ ::

ለምሣሌ:- የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች ለማስተማር ቢፈለግ፣ በነበረ ክበቡ ውስጥ ለደስታ መግለጫ፣ ለሀዘን መግለጫ፣ለአክብሮት፣ ወዘተ... የሚውሉ ባህላዊ አገላለጾችን ምን እንደሚባልና እንዴት እንደሚባል ለማሣየት ምልልሶችን በማዘጋጀት፣ ተማሪዎች ባህርያትን ወክለው እንዲለማመዱ በማድረግ ይዘቱ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ::

ታይለር የትምህርት ልምዶች ጥርቅም ውጤት እንዲያስገኙ አንዱ በሌላው ላይ ተመሥርተው መቀናበር አለባቸው ይላል ::

> ውጤታማ በሆነ መንገድ የተቀናበረ የትምህርት ልምዶችን ለማግኘት ሦስት ዋና ዋና መመዘኛዎች አሉ :: እነርሱም:- ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነትና አንድነት ናቸው :: ተከታታይነት:- የአንዱን የትምህርት ልምድ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለተማሪው መቅረብ ያመለክታል፣ ተለጣጣቂነት:- ከተከታታይነት ጋር ይመሣሰላል :: ነገር ግን ተለጣጣቂነት እያንዳንዱ የትምህርት ልምድ አንዱ በሌላው በቀደመው ላይ ተመሥርቶ እያደገ የሚሄድ መሆኑን ያሳያል :: አንድነት:- አንድነት አንዱ የትምህርት ልምድ ከሌላው የትምህርት ልምድ ጋር ተደጋግፎና ተቀናጅቶ መቅረቡ የሚታይበት ነው / ታይለር፣ 1949 :83 / ::

ሌላው በመርሀ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የሚተኮርበት ጉዳይ ግምገማ ነው :: ይኸውም በአላማው የተገለጸው ጉዳይ ከግቡ መድረሱ የሚታይበት ክፍል ነው ::ግምገማ በትምህርት ውጤት ላይ ያተኩራል :: ትምህርቱን ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የአሠራርና የአስተሳሰብ ለውጥ አሳይተዋል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከእያንዳንዱ ትምህርት በኋላ ግምገማዎች ይኖራሉ :: ግምገማው በክፍል ሥራ፣ በቤት ሥራ ወይም በፈተና መልክ ሊሆን ይችላል : :

> ቋንቋን በማስተማር ሂደት ማዳመጥ ከፍተኛ ድርሻ
> አለው፤ ስለዚህ በሌሎች ክሂሎች ውስጥ በአንድነት
> መገኘት አለበት የሚለው አመለካከት ተቀባይነት አያገኘ
> መጥቷል ። ይህ ማለት ግን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ
> በማዳመጥ ላይ ያተኮረ ትምህርት ማቀድ አይቻልም ማለት
> አይደለም ። በአንድ ክሂል ላይ ማተኮር ማለት ደግሞ
> ሌሎችን ክሂሎች አለማገናኘት አይደለም ።
> / አንደርወድ ፤ 1989:23 /

ክሂሎችን ለማዳበር በሚቀርብ የቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ ክሂሎችን በተቀናጀ ሁኔታ የማዳበሩ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ ክሂል የሚፈለገውን የችሎታ ደረጃ ለመወሰንና ትኩረት ለመስጠት ሲባል ክሂሎችን ነጣጥሎ ማቀረቡም ተቀባይነት አለው ።

የማዳመጥ ክሂል በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድ እንጂ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ዳብሮ የሚያበቃ አይደለም ። ስለዚህ ተማሪው በየጊዜው በተለያዩ የማዳመጥ ሁኔታዎች ውስጥ በበቂ ሁኔታ መሣተፍ እንዲችል ክሂሉን የሚያዳብሩ ልምምዶች ማቀረብና በየጊዜው ክሂሉን ማሳደግ ያስፈልጋል ። በአፍ መፍቻ ቋንቋም ቢሆን የማዳመጥ ክሂል ሙሉ በሙሉ ሊዳብር እንደማይችል በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማዳመጥ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ያበረዳሉ ። ጥናቶቹን በመከለስ አንደርሰንና ሊንች እንዳበረሩት፡—

> ቋንቋውን በአፍ መፍቻነት በሚጠቀሙት ዘንድ
> እንኳ ቢሆን የማዳመጥ ክሂሎች ሁሉ ጊዜ ሙሉ
> በሙሉ ሊዳበሩ አይችሉም ። በአብዛኛው የዚህ
> ችግር ምክንያቶች መረጃዎችን አዳምጦ የመረዳት
> ወይም መረጃዎችን ተርጉሞ የመጠቀም ክሂሎች
> ናቸው ። / አንደርሰንና ሊንች፤ 1988:60 / ።

...// 22

ABABA UNIVERSITY
ES LIBRARY



በአፍ መፍቻ ቋንቋም ሆነ በሌሎች ያለውን የማዳመጥ ችግር በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከሁሉን ትኩረት ሰጥቶ በማስተማር ማስወገድ ይቻላል ። አዳምጦ የመረዳት ችሎታን መቶ ፐርሰንት ማድረስ ባይቻልም በማስተማር፣ ለተማሪው አስፈላጊ የሆኑትንና ሊጠቀምባቸው የሚችሉባቸውን ችሎታዎች ማስጨበጥ ይቻላል ። /ብራውንና ዬል፣ 1983/።

የማዳመጥ ክሂል በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድ ነው ስለዚህ ለአፍ መፍቻ ቋንቋም ቢሆን የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ልምምዶች መዘጋጀትና ተማሪው ትኩረት ሰጥቶ እንዲለማመድባቸው የማድረጉ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም።

## የማዳመጥ ይዘት ምርጫ

የማዳመጥኛ ክሂል በትምህርት ቤት የማስተማር ዋነኛ አላማ፣ ተማሪው የሚሰማውን ነገር የመረዳት ፣ የመተርጎም፣ የመገምገምና የራሱን ምላሽ መስጠት የሚያስችለውን ክሂል ለማስጨበጥ፣ በማዳመጥ ችሎታው እንዲተማመንና በህብረተሰቡ ውስጥ ማዳመጥን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀም ለማስቻል በልዩ ልዩ የማዳመጥ አውዶችና የማዳመጥ ዓይነቶች ተግባራዊ ልምምድ መስጠት ነው ። በዚህም መሠረት የማዳመጥ ልምምዶችን በምናዘጋጅበት ጊዜ ተማሪዎች የሚጠቀሙበትን በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የማዳመጥ ሁኔታና ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ የማዳመጥ ችግሮችን ከግምት ማስገባት ይኖርብናል ።

ኧር፣ በተለያዩ የማዳመጥ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ለማዳመጥ ትምህርት የሚሆኑ ይዘቶችን ማዘጋጀት እንደሚቻል ተጠቁማለች ተማሪዎች በህብረተሰቡ ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን የማዳመጥ ሁኔታ እንዲለማመዱ ከተፈለገ በነዚህ የማዳመጥ ሁኔታዎች ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ባህርያትን ያካተተ ልምምድ ሊቀርብላቸው ይገባል ። ይኸውም :-

በህብረተሰቡ ውስጥ ስናዳምጥ:-

1. የምናዳምጥበት አላማ ይኖረናል፣ ስለምናዳምጠው ነገር ይዘት አስቀድመን እንገምታለን ።
2. ለምንሰማው ነገር ወዲያውኑ ምላሽ እንሰጣለን ።
3. የምናዳምጠውን ሰው እናያለን ።
4. የምንሰማውን ነገር ትርጉም የሚጠቁሙ አንዳንድ አካባቢያዊ መገለጫዎች ይኖራሉ ።
5. የሚሰማው ነገር አጠር አጠር ባሉ ምልልሶች የተከፋፈለ ይሆናል ።

6. አብዛኛው ምልልስ ያልታቀደ ምልልስ ነው :: ስለዚህ ከመደበኛ ንግግር በውግግሮሽ፣ በንግግር ቋንቋነት ባህሪው፣ ንግግሩ በግልጽ እንዳይሰማ እንቅፋት በሚሆኑ ሁኔታዎችና በመደመጥ ባህሪው ይለያል ::
/ሾር፣ 1984: 3–10/

የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ይዘቶች ሲመረጡና የትምህርት ልምዶች ሲዘጋጁ ከላይ የተጠቀሱትን የማዳመጥ ሁኔታ ባህርያት በተለያዩ አውዶች አካቶ በማቅረብ ተማሪውን በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚያጋጥሙት የማዳመጥ ሁኔታ ባህርያት ጋር ማለማመዱና በየማዳመጡ ሁኔታዎች ውስጥ በብቃት የሚያዳምጥ በትን ችሎታ ማስጨበጥ ይገባል ::

ለተማሪዎቹ የሚቀርቡ የማዳመጥ ይዘቶች ተማሪውን በተለያዩ የማዳመጥ ዓይነቶች የሚያለማምዱ መሆን ይኖርባቸዋል:: ክሂሉን በማዳበር ሂደት የተኛው የማዳመጥ አይነት ይበልጥ ሊተኮርበትና ብዙ ልምምድ ሊቀርብበት ያስፈልጋል ለሚለው ጥያቄ የተማሪዎችን ፍላጎት ማወቅን ይጠይቃል:: ተማሪ ዎቹ ብዙ ጊዜ ሊገለገሉበት የሚያስፈልጋቸውን የማዳመጥ አይነት ለይቶ በማወቅ በዚያ ላይ የተመሠረተ ይዘት ማቅረብ ያስፈልጋል ::

የማዳመጥን ክሂል በሚያዳብሩ ይዘቶች ውስጥ የተለያዩ የማዳመጥ ዓይነቶች ሊቀርቡ ይችላሉ:: ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ለማህበራዊ ምልልስ ማዳመጥና ለመረጃ መሻት ማዳመጥ ናቸው ::/አንደርሰንና ሊንች ፣ 1988፤ ሪቻርድስ፣ 1990፤ ሮስት ፣ 1990/::

ለማህበራዊ ምልልስ ማዳመጥ አላማው በቋንቋ ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ የተናጋሪውን የመልእክት አቀራረብ መለየት ሲሆን፣ በምልልሱ ተሳታፊዎች መሀከል መግባባትን መፍጠር ላይ ያተኩራል ::

ለመረጃ መሻት ማዳመጥ አላማው አዲስ መረጃን ማግኘት ሲሆን የሚተላለፈውን መልእክት በትክክል አዳምጦ መረዳት ላይ ያተኩራል :: በዚህ የማዳመጥ አይነት የሚቀርበው ነገር የትርጉም ገለጻነትና ቀጥተኛነት እንዲኖረው ይጠበቅበታል ::/ሪቻርድስ ፣ 1990/::

በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማዳመጥን ትምህርት ይዘት በተመለከተ ፣ ተማሪው የማህበራዊ ምልልስ ክሂሎችን በተለያዩ የማዳመጥ ሁኔታዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ለማዳበር አድሉ ሰፊ ስለሆነ በትምህርት ቤት በይበልጥ ሊተኮርባቸው የሚገባው የመረጃ መሻት ክሂሎች ላይ መሆን አለበት ::/አንደርሰንና ሊንች፣ 1988/::

የማዳመጥ ክሂሎ በጥሩ ሁኔታ ሊዳበር የሚችለው አጠቃላይ አዳምጦ የመረዳት ችሎታንና ንዑሳን የማዳመጥ ክሂሎችን የሚያለማምዱ ይዘቶች በተቀናጀ መልክ ሲቀርቡ ነው ፡፡ ለተማሪው ሊቀርቡለት ስለሚገባ የማዳመጥ ንዑሳን ክሂሎች በተመለከተ በርካታ ጸሀፍት የተለያዩ ዝርዝሮችን አመልክተዋል፡፡ ከነዚህም መሀከል ፤

መንበረ ፤ 1978 ፤ ሀርመር፤ 1983 ፤ ሊውስና ሂለ፤1986 ፤ ሪክስን ፤ 1986፤ እና ሮስት ፤ 1990 ይገኙበታል ፡፡

- ከረጅም ንግግር አበይ ሀሳብ ወይም ጭብጥ ማውጣት ፤
- የንግግሩን ተከታታይ ክፍሎች አስቀድሞ መገመት ፤
- ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት ፤
- ተናጋሪው ሀሳብ ለማስተዋወቅ፤ ርእስን ለመቀየር ፤ ለትኩረት ፤ ነጥቦችን ለማብራራትና ለማስፋፋት ፤ ተቃራኒ ሀሳቦችን ለመግለጽ የሚገለገልባቸውን ነጥቦች መገንዘብ ፤
- ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት ፤
- ተናጋሪው የሚሰጠውን መረጃ ስሜቱን መገንዘብ ፤
- በንግግሩ ውስጥ የማይታወቁ ቃላትን ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት ፤
- የተናጋሪውን አላማ መረዳት ፤
- የተደመጠውን ነገር ቀደም ብሎ ስለጉዳዩ ካለእውቀት ጋር ማገናዘብ ፤
- የተወሰኑ ዝርዝር ጉዳዮችን መረዳት ፤
- በግልጽ የተነገሩ መረጃዎችን አዳምጠው መረዳት ፤
- በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት ፤
- የማይጠቅሙ መረጃዎችንና ድግግሞሽ በመለየት አሳጥሮ ማቅረብ፤
- መረጃዎችን አዳምጠው ወደ ግራፍ ፤ ሠንጠረዥ ወይም ካርታ መተርጎም ፤
- ያዳመጡትን በራሳቸው አባባል ማቅረብ ፤
- ከሚያዳምጡት ውስጥ ፍሬ ሀሳቡን ለይተው ማስታወሻ መያዝ፤
- ከሚያዳምጡት ውስጥ ምክንያትና ውጤትን መለየት ፤
- ስለሚደመጠው ነገር አጠቃላይ ግንዛቤ መውሰድ የሚሉት ጸሀፍት ከጠቀሟቸው የማዳመጥ ንዑሳን ክሂሎች መሀከል የሚገኙ ናቸው ፡፡

በተማሪው ፍላጎትና ችሎታ ላይ ተመስርተው የሚመረጡት የማዳመጥ ንዑሳን ክሂሎችን የሚመለከቱ ይዘቶች በንግግር ወይም በምንባብ አውዶች ውስጥ በመካተት ተማሪው ክሂሎቹን እንዲያዳብርባቸው የሚያስችሉ ልምምዶች ይቀርቡባቸዋል

የማዳመጥ ክሂል የሚዳብረው ልምምዱ በማደረግ ነው :: ተማሪው የሚደመጥ ነገር ስለቀረበለት ብቻ ያዳምጣል ማለት አይቻልም:: ሳዳመጠው ነገር አንዱ አይነት ምላሽ —የቃል ወይም የተግባር መስጠት አለበት :: አዳምጦ መረዳቱም ሊረጋገጥ የሚችለው በዚህ መንገዱ ነው ::

ለተማሪው የሚቀርበው የማዳመጥ ተግባር ተማሪውን ሊያሳትፍ የሚችል መሆን ይኖርበታል :: ለዚህም የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር በሚቀርቡ ይዘቶች ውስጥ ተማሪው አዳምጦ የሚፈጽማቸው ተግባሮች ቢታቀዱ ጥሩ ነው :: እንደ ሸር አባባል የማዳመጥ ልምምዶች የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት በተግባር ላይ ሲመሰረቱ ነው :: ለተማሪው የሚቀርበው የማዳመጥ ተግባር :-

- አስቀድሞ የታቀደ አላማ ያለው ፣
- ዠታታይ የተማሪውን ዝግትና የሚጠይቅ ፣
- ተማሪውን የሚያነቃቃ
- አንዱ አይነት ውጤት የሚያስገኝ ፣
- ተማሪው ሊያከናውነው የሚችል ፣
- ተማሪው /በቃል ወይም በተግባር /መልስ የሚሰጥበት መሆን አለበት /ሸር ፣1984: 25–29 /

የማዳመጥን ክሂል የሚያዳብሩ ልምምዶች ተማሪው የራሱን የማዳመጥ ዘዴ እንዲቀይስ የሚያለማምዱ መሆን ይኖርባቸዋል:: የማዳመጥ ዘዴዎች የሚደመጠውን ነገር በቀላሉና በትክክል ለመረዳት የሚያስችሉ መንገዶች ናቸው :: የማዳመጥ ዘዴዎች በማህበራዊ ምልልስ የማዳመጥ ሁኔታ ውስጥ፣ ስላዳመጡት ጉዳይ ማብራሪያ ለመጠየቅና በትክክል ማዳመጥን ለማረጋገጥ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ሲሆኑ፣ በመረጃ መሻት የማዳመጥ ሁኔታዎች ውስጥ ደግሞ የተደመጠው መረጃ ቀደም ሲል ከሚታወቀው የተለየና አዲስ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ናቸው ::/ርስት፣1990/

የማዳመጥ ዘዴዎች የማዳመጥን ተግባር ቀላል እንዲሆን ይረዳሉ :: ከማዳመጥ ዘዴዎች ሌላ በክፍል ውስጥ የማዳመጥ ልምምዶች ሲካሄዱ ተማሪው የማዳመጥ ተግባሮችን በቀላሉ እንዲያከናውን በቅድመ–ማዳመጥ፣ እያደመጡና በድህረ–ማዳመጥ የሚከናወኑ ተግባሮችን ከፋፍሎ ማቅረቡ ይረዳል::በዚህም መሠረት ለተማሪው የሚደመጠውን ነገር ከማቅረቡ በፊት ቅድመ ማዳመጥ መመሪያዎችን መስጠት፣ የሚደመጠውን ጉዳይ ርዕስ ማስተዋወቅ፣ ከርእሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የተወሰኑ መሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ በሚያዳምጥበት ጊዜ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ማሳወቅ የመሳሰሉት ፣ ለተማሪው በሚያዳምጥበት ወቅት ምን መፈጸም እንዳለበት ፣ የትኛው መረጃ ላይ ማተኮር እንደሚገባው በአጠቃላይ የማዳመጥ ተግባሩን ግልጽ ስለሚያደርግለት በቀላሉ አዳምጦ

መረዳት ይችላል :: የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶች በቅድመ—ማዳመጥ ፣ በአያዳመጡና ፣ በድህረ—ማዳመጥ ተግባሮች ተከፋፍለው ሲቀርቡ ትምህርቱ የተቀላጠፈና ውጤታማ ይሆናል ::

## የማዳመጥ ይዘት ቀንበር

ማንኛውም ለትምህርት የሚቀርብ ይዘት ቀንበርን በተመለከተ ተከታታይነትን፣ ተለጣጣቂነትንና አንድነትን ጠብቆ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከገለጽ ወደ ውስብስብ እያደገ በሚሄድ ቀደም ተከተል መቀረብ ይኖርበታል :: በዚህ መሠረት ለተማሪው የሚቀርቡ የማዳመጥ ክሂሎን የሚያዳብሩ ይዘቶችም ከቀላል ወደ ከባድ ከገለጽ ወደ ውስብስብ እያደጉ የተማሪውን የማዳመጥ ክሂሎ ከጊዜ ወደጊዜ የበለጠ እያዳበሩ የሚሄዱ መሆን አለባቸው :: አንደር ሰንና ሊንች የማዳመጥ ትምህርት ይዘት አቀራረብትን በተመለከተ:—

> ተማሪዎች በጣም ከባዱና ውስብስብ ወደ ሆነ ልምምዱ ከመግባታቸው በፊት ቀላል በሆኑ ልምምዶች ጥሩ ውጤት ማምጣትና መበረታታት ይኖርባቸዋል ይላሉ ::/አንደርሰንና ሊንች፣ 1988:44/

አንደርሰንና ሊንች ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መሀል የሚከተሉት ይገኛሉ ይላሉ ::

1. የሚደመጠው የቋንቋ አይነት
2. የሚደመጥበት አላማ ወይም ተግባር
3. የሚደመጥበት አውድ/አንደርሰንና ሊንች፣ 1988:46/

እንደነ አንደርሰን አባባል የሚደመጠው የቋንቋ አይነት ሲባል በሚደመጠው ምንባብ ወይም ንግግር ውስጥ ያለው የቋንቋ አቀራረብት ሁኔታ እንዴት እንደሆነ ያሳያል ::ይህም በሚደመጠው ምንባብ ወይም ንግግር ውስጥ መረጃዎች የተቀናበሩበትን መንገድ ፣ ከሚደመጠው ጉዳይ ጋር አግባብ ያለውን የተውውቀ መጠን ፣ የሚደመጠውን ነገር የገለጸነት ደረጃና የይዘት አይነት ያመለክታል:: የሚደመጠው የቋንቋ አይነት አዳምጦ የመረዳት ሁኔታን ከባድ ወይም ቀላል ያደርጋል ::

በማዳመጥ የሚፈጸሙ ተግባሮች ባህሪ ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ ያደርገዋል ሲባል፣ የተለያዩ የማዳመጥ ተግባሮች ለተማሪው የተለያዩ የክብደት ደረጃ ያላቸውን ልምምዶች ይዘው እንደሚቀርቡ ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ወሬያዎችን ምስል የማየት ተግባሮች /ምስሉ፣ስዕሎችን [illegible] መግለጽ ወይም በቀደም

ተከተለ ማስቀመጥ/ ካዳመጡ በኋላ ተፈላጊውን መረጃ መርጦ ከሚፈጸሙ ተግባሮች /ምሳሌ፡ዋናውን ሀሳብ አሳጥሮ ማቀረብ/ይልቅ ቀላል ናቸው፡፡እነዚህ ደግሞ በተራቸው በስሜታዊና በተጨባጭ አስተያየቶች መሀከል ያለውን ልዩነት መገንዘብን ከሚጠይቅ የማዳመጥ ተግባር ይልቅ ቀላል ናቸው ፡፡

የሚደመጥበት አውዱ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ይይዛል :— የሚደመጠው ጉዳይ የመረጃ ብዛትና የማዳመጥ ሂደት የሚፈጀው ጊዜ ናቸው ፡፡

ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ ሊያደርጉ የሚችሉ ምክንያቶችን ስንመረምር በይበልጥ ማተኮር ያለብን በሚደመጠው ጉዳይ የቋንቋ አቀርቦት ባህሪና በማዳመጥ የሚፈጸሙ ተግባሮች ባህሪ የክብደት ደረጃ ላይ ነው በማለት እንደርሰንና ሌንች አበክረው ያሳስባሉ ፡፡
/እንደርሰንና ሌንች ፣ 1988/፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ የሚያሰኙ ምክንያ ቶችን እንደመመዘኛ በመጠቀም፣ ለተማሪው የሚቀርቡ የማዳመጥ ክሂሎን የሚያ ዳብሩ ይዘቶችን የክብደት ደረጃቸውን የጠበቁ ከተማሪው ችሎታ ጋር የሚመ ጣጠኑ አድርጎ መምረጥና ማቀናበር ይቻላል ፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ምዕራፍ 3 :- የአጠናን ዘዴ

## 3.1 ይዘቶችን መለየት ፣ መተንተንና መገምገም

ይህ ጥናት የይዘት ትንተና ጥናት ዘዴን በመከተል በ1984 ዓ.ም በታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ተመርጠው የቀረቡ የትምህርት ይዘቶችን ለይቶ በማውጣት ይዘቶቹ ክሂሉን ከማዳበርና የተማሪዎችን ፍላጎት ከማሟላት አንጻር ያላቸውን ብቃት በማጥናት ትንትኖና ገምግሞ አቅርቧል ::

ቦርግና ጋል /1989/ ከይዘት ትንተና ጥናት አላማዎች አንዱ ስለ ሚጠናው ጉዳይ ገላጭ መረጃ መስጠት መሆኑን ይጠቁማሉ :: ይህ ጥናት የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችን በተመለከተ ገላጭ መረጃ ለመስጠት ይሞክራል :: ለዚህም ይዘቶቹን በመለየትና በመወደብ ስለማዳመጥ ትምህርትና ስለ ቋንቋ መርሐ ትምህርት በቀረቡ ንድፈ ሃሳቦችና በመጠይቆች አማካይነት በተገኘ መረጃ ላይ በመመስረት ይዘቶቹን ለመተንተንና ለመገምገም ሞክሯል ::

በዚህ የይዘት ትንተና ላይ ባተኮረ ጥናት ውስጥ የመጠይቆችን ምላሽ ለመተንተን የገላጭ የምርምር ዘዴ አሰራርም በጥምር ጥቅም ላይ ውሏል ::

ይዘቶቹ ከመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ተለይተው የተመረጡት በሁለት መንገዶች ነው ::ይኸውም: -1ኛ/በቋንቋው ትምህርት አጠቃላይ አላማ ሥር " የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራሉ " ተብሎ የተገለጸውን አላማ ከግቡ ያደርሳሉ ተብለው የተመረጡ ይዘቶችን በመለየትና፣ 2ኛ/ለሌሎች የቋንቋ ትምህርት አላማዎች ከተመረጡት ይዘቶች መሀል አገረ መንገዳቸውን የማዳመጥን ክሂል የዳበሩትን ይዘቶች በመለየት ነው :: የመጀመሪያዎቹ ይዘቶች በቀጥታ ክሂሉን ትኩረት ሰጥቶ ለማዳበር የተመረጡ ሲሆኑ ፣ ሁለተኛዎቹ ግን ማዳመጥ ለሌሎች ክሂሎች በተመረጡ ይዘቶች ውስጥ ሲዳበር የምናይባቸው ናቸው ::

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ከላይ በተገለጹት በሁለቱም መንገዶች የቀረቡት ይዘቶች ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ ናሙና ከመምረጥ ይልቅ ሁሉንም ይዘቶች ለመተንተንና ለመገምገም ተሞክሯል::

## 3.2 መጠይቆችን ማዘጋጀት

ጥናቱ የሚካሄድባቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ምን ያህል የተማሪውን ፍላጎት ያሟላሉ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንዲቻል በተማሪዎች ፣ በመምህራንና በመርሀ ትምህርት አዘጋጆች የሚሞሉ ሶስት ዓይነት መጠይቆች

ተዘጋጅተው በነርሱም አማካይነት መረጃ ተሰብስቧል ::

በሦስቱም መጠይቆች ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች በተቻለ መጠን ወደ ማዳመጥ ክሂል ያተኮሩ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል :: የተማሪው መጠይቅ የተማሪውን የተማሪውን ዳራ፣ ቋንቋውን የሚማርበትን አላማ ፣ ለትምህርቱ አቀራረብ ያለውን ዝንባሌ፣ የቋንቋ አጠቃቀሙንና የማዳመጥ ችሎታውን የሚዳስሱ ጥ ጥያቄዎችን ይዟል ፤ የመምህሩ መጠይቅ የመምህሩን ዳራ፣ የቋንቋው መምህር በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል በተመለከተ በቀረቡት ዝርዝር አላማዎችና ይዘቶች ላይ የሚኖረውን አስተያየት፣ ክሂሉን ለማዳበር የሚጠቀማቸውን ይዘቶችና የተማሪዎቹን የማዳመጥ ችሎታ የሚያመለክቱ ጥያቄዎችን ይዟል ፤ የመርሀ ትምህርት ባለሙያው መጠይቅ ከያዛቸው ጥያቄዎች ውስጥ መርሀ ትምህርቱ ሲዘጋጅ መሠረት ያደረገው ምን እንደሆነ፣ የተማሪዎች ፍላጎት መጠናት አለመጠናቱን፣ አማርኛ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በስንተኛ ቋንቋነት እንደሚሰጥ፣ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን የተመለከቱ ዝርዝር አላማዎችና ይዘቶችን ብቃት የሚጠይቁ ይገኛሉ ::
/ ስለጠቀኳኳ መረጃ አባሪ 1 2 ና 3 ን ይመለከታል /::

ከመጠይቆች የተገኙ መረጃዎች በገለጻ የተንተና ስለት በተተነተኑ በኋላ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች ጋር በማነጻጸር ይዘቶቹ ምን ያህል የተማሪውን ፍላጎት እንዳሟሉና የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ምን ያህል ብቁ መሆናቸውን ለማገናዘብ ተሞክሯል ::

በትምህርት ቤትና በኅብረተሰቡ ውስጥ ምልከታዎችን በማድረግ ለፍላጎትና አስሳው ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት እንደሚቻል ቢታመንበትም ካለው የጊዜ እጥረት የተነሣ የተቀናበረና ስርአት ያለው ምልከታ ለማድረግ አልተቻለም ::

## 3.3 <u>ናሙና መምረጥና መጠይቁን ማስመላት</u>

የማዳመጥን ክሂል በቀጥታ እንዲያዳብሩ የተመረጡትም ሆኑ በተዘዋዋሪ ክሂሉን የሚዳስሱት ይዘቶች ቁጥራቸው አነስተኛ ስለሆነ ለጥናቱ ሁሉም ተወስደዋል :: ቀጥሎ የቀረበው ሠንጠረዥ ጥናቱ ያተኮረባቸውን ይዘቶች ያሳያል:-
ሠንጠረዥ : 1 የማዳመጥን ክሂል በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለማዳበር በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ::/ለመቀሰሽ መረጃ አባሪ 4 ን ይመለከታል/

ሞልተዋል፡፡ ለመርሀ ትምህርት ባለሙያው የተዘጋጀውን መጠይቅ በስርአተ ትምህርት መምሪያ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ቡድን አባላት ከሆኑ አራት ባለሙያዎች መሀከል ሶስት ሲሞሉ፣ አንደኛው በሥራ ብዛት ምክንያት መጠይቁን ሊሞሉ አልቻሉም ፡፡

.../32

## ምዕራፍ 4 ፡ ጥናቱና ውጤቱ

### 4.1 የይዘት ትንተናና ግምገማ ውጤት

የቋንቋ ክሂሎች በተናጠል ትኩረት ተሰጥቷቸውና አንዱ ከሌላው ጋር በመቀናጀት ሊዳበሩ ይችላሉ ፡፡ በዚህ የይዘት ትንተናና ግምገማ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል፣ ክሂሉን ለማዳበር ሆን ተብለው በተመረጡት ይዘቶችና እንዲሁም ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር ተመርጠው ነገር ግን የማዳመጥን ክሂል አገረ መንገዳቸውን ለማዳበር በሞከሩት ይዘቶች አማካይነት ምን ያህል በብቃት ሊዳበር እንደሚችል እናያለን ፡፡


በዚህ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ በእያንዳንዱ አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት አላማ ሥር የቀረቡትን ይዘቶች ብዛት ስንመለከት የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች ቁጥር ከሁሉም አነስተኛ ነው ፡፡

ሠንጠረዥ 2 ይህንኑ ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 2 ፡ በአጠቃላይ አላማው ሥር የቀረቡ የይዘቶች ብዛት

| አጠቃላይ አላማ | የይዘት ብዛት | |
|---|---|---|
| | ብዛት | % |
| ማዳመጥና መናገር | 4 | 7.5 |
| ማንበብ | 12 | 22.6 |
| መጻፍ | 19 | 35.8 |
| ሥነ ልሣን | 13 | 24.5 |
| ሥነ ጽሁፍ | 5 | 9.4 |

የማዳመጥና የመናገርን ክሂሎች ለማዳበር በተመረጡት ይዘቶች ብዛትና በሌሎቹ መሀከል ሰፊ ልዩነት ይታያል ። በይዘት ብዛት ከፍተኛው 35.8% ሲሆን ፣ ዝቅተኛው 7.5 % ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች የቀረቡት ይዘቶች ናቸው ። ቀጥሎ የቀረበው መስመራዊ ግራፍ በአጠቃላይ አላማው ሥር የቀረቡት ይዘቶች ከአማካይ የይዘቶች ቁጥር ወደላይና ወደታች ምን ያህል አንደሚርቁ ያሳያል ።




ግራፍ 1 ፡ የይዘቶችን ስርጭት የሚያሣይ መስመራዊ ግራፍ ፡

በየአላማው ስር የቀረቡት ይዘቶች ስርጭት እንደሚያሳየን ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች የተሰጠው ትኩረት ከሌሎች ክሂሎች የመጨረሻውንና ዝቅተኛውን ደረጃ ይዞና ከአማካዩ በታች ርቆ ነው ያለው ።

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በሁለቱም ሴሚስተሮች ሆነ ተበሉ ክሂሉን ለማዳበር የቀረቡ አራት ይዘቶች ሲኖሩ ፣ ሌሎች ክሂሎችን አንዲያዳብሩ ተመርጠው አገረመንገዳቸውን ማዳመጥን ለማዳበር የሚከሩ ሦስት ይዘቶች አሉ ::

የሚከተለው ሰንጠረዥ በየሴሚስተሩ የቀረቡትን የማዳመጥ ይዘቶች በዝርዝር ያሳያል ::

ሰንጠረዥ 3 ፡ በየሴሚስተሩ የቀረቡ የማዳመጥ ይዘቶች

| ሴሚስተር | የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ | ገጽ | ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|
| አንደኛ ሴሚስተር | የውይይት ስርአት<br>የክርክር ስርአት<br>የጭውውት ስርአት | 22<br>23<br>24 | | |
| ሁለተኛ ሴሚስተር | የመንስኤና የውጤት ግንኙነት | 60 | በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት<br>ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ አንድን ርእስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቀረብ | 65<br>66 |

.../// 35

ከላይ በሰንጠረዥ የተመለከቱትን ይዘቶች ክሂሉን የማዳበር ብቃታቸውን ከማየታችን በፊት ለግንዛቤ እንዲረዳ የመርሀ ትምህርቱን አጠቃላይ መለክ መመልከቱ ጠቃሚ ነው :: ምክንያቱም ስለይዘት ስንናገር ይዘቱ የተመረጠለትን አላማ፣ ይዘቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ የሚጠቁመውን የመማር ማስተማር ስራ ከንውንን እንዲሁም ይዘቱ በተማሪዎች ተግባራዊ መሆኑ የሚረጋገጥበትን የግምገማ ክፍል ባና ነካ አንቀርምና ነው :: / የመርሀ ትምህርቱን አጠቃላይ መለክ የሚያሳየውን ሠንጠረዥ በአባሪ 4 ይመልከቱ / ::

'<u>የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ</u>' የሚለው የመርሀ ትምህርቱ አካል፣ የቋንቋው ትምህርት ለተማሪው ምን ምን የቋንቋ ክሂሎችንና እውቀቶችን ለማስጨበጥ እንደታቀደ አጠቃላይ በሆነ መልኩ ያሳያል :: በዚህም መሠረት የሚከተሉት አጠቃላይ አላማዎች ቀርበዋል ፡—

1. የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራል ፤
2. የማንበብ ክሂልን ያዳብራል ፤
3. የመጻፍ ክሂልን ያዳብራል ፤
4. የስነ ልሣን እውቀትን ያዳብራል ፤
5. የስነ ጽሁፍ እውቀትን ያዳብራል ::

'<u>ዝርዝር አላማ</u>' በአጠቃላይ አላማው ስር የተገለጹት አጠቃላይ ክሂሎችና እውቀቶች እያንዳንዳቸው በዝርዝር ክሂሎችና እውቀቶች ተከፋፍለው የሚቀርቡበት ክፍል ነው :: ለምሳሌ 'የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራል' ለሚለው አጠቃላይ አላማ ፣ 'ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ያዳብራሉ'፣ 'የተወሰነን ሀሳብ ባራስ አባባል የማቅረብ ዘዴን ያዳብራሉ' የሚሉ ዝርዝር አላማዎች ቀርበዋል :: የዝርዝር አላማው መገለጽ በተወሰነ የክፍል ደረጃ በየአጠቃላይ አላማው አንጻር ትኩረት የሚሰጥባቸውና ተማሪው እንዲያዳብራቸው የሚፈለጉት ንኡሳን ክሂሎች የትኞቹ እንደሆኑ ለይቶ ለማመልከት ይረዳል ::

'<u>ይዘት</u>' በዝርዝር አላማው ተለይተው የተጠቀሱት አላማዎች ወደ ቋንቋ ትምህርትነት የሚተረጎሙባቸው ይዘቶች የሚቀርቡበት ክፍል ነው :: ለምሳሌ ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ለማዳበር የተመረጡት የትምህርት ይዘቶች 1. የውይይት ስርአት ፣ 2. የክርክር ስርአት፣ 3. የጭውውት ስርአት ናቸው :: ተማሪው በመወያየት፣ በመከራከርና ጭውውት በማድረግ ተጠያቃዊ አስተሳሰብን ያዳብራል ማለት ነው ::

“<u>የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ስራ ክንውን</u>” እንዱን ክሂል ለተማሪው ለማስጨበጥ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ልምምዶችን ይዟል :: በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት የክፍል ውስጥ ልምምዶች ለናሙና ያህል መሆናቸውንና መምህሩ በዚህ መልክ ሌሎች ተጨማሪ ልምምዶችን ማቀረብ እንደሚኖርበት ተገልጿል :: በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን ሥር የሚቀርቡ ልምምዶች በይዘቱ የቀረበውን የቋንቋ አካል ምንማለት እንደሆነና የትኛውን ክሂል እንደሚያዳብር ይተረጉማሉ ::

“<u>ግምገማ</u>” ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን ሥር የቀረቡትን ልምምዶች በማከናወን ተረዷቸውን አውቀት ወይም ክሂል ጨብጠው እንደሆነ የሚታይበት ክፍል ነው :: በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት የግምገማ ነጥቦች ለናሙና ያህል መሆናቸውንና መምህሩ እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ አዘጋጅቶ መጠቀም እንደሚቻ ተገልጿል ::

የመርሀ ትምህርቱ አንዱ አካል ከሌላው ጋር የተሳሰረ፣ አንዱ ሌላውን የሚተረጉምና አንዱ በአንዱ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ስለይዘቱ ስንናገር ሌሎቹን የመርሀ ትምህርቱን አካሎችም ማንሳታችን የግድ ነው :: በዚህ መሠረት የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡትን ይዘቶች ለማየት አስቀድሞ ይዘቶቹ የተመረጡበትን አላማና ዝርዝር አላማዎች ጠቀለል ባለ መልክ እናያቸዋለን ::

/ ይህ ጥናት ያተኮረበትን የመርሀ ትምህርት ክፍል አባሪ 5 ላይ ይመለከቷል/ ::

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ= “የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራል”፤ በሚል የማዳመጥ ክሂል ከመናገር ክሂል ጋር ተዳብሎ ቀርቧል :: ሌሎች ክሂሎች ለምሳሌ የማንበብ ክሂልና የመጻፍ ክሂል እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው በተናጠል አላማ ሲነደፍላቸው የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች ግን በአላማ ደረጃ በአንድነት የቀረቡበት ምክንያት ግልጽ አይደለም :: ወይም ምክንያት አልቀረበበትም :: ብዙ ጊዜ በገሃዱ አለም የማዳመጥ ተግባር ከመናገር ጋር ተያይዞ የሚገኝ ነው ::በቃል ተግባቦት በአብዛኛው ሁኔታዎች ውስጥ ተናጋሪና አድማጭ ይኖራል፤ የተናጋሪውና የአድማጩም ድርሻ ይቀያየራል ፤ ማለት አድማጭ የነበረው ተናጋሪ፣ ተናጋሪ የነበረው ደግሞ በተራው አድማጭ ይሆናል ::ስለዚህ ክሂሎች ተዳብለው መቅረባቸው ለተማሪው ሁለቱም ክሂሎች አብረው በአንድ ጊዜ ያስፈልጉታል በማለ ይሆን ? ሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች በአላማ፣ በዝርዝር አላማና በይዘት ምርጫ ደረጃ በተናጠል ሲቀርቡ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች ግን በአንድነት የቀረቡበት ምክንያት በመርሀ ትምህርቱ ላይ አልተገለጸም :: የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በአጠቃላይ አላማና በዝርዝር አላማ ሥር እያንዳንዳቸውን

ችለው ቢቀርቡ የተሻለ ይሆናል ። ምክንያቱም በእያንዳንዱ ክሂል አንጻር ሊዳብሩ የሚገባቸውን ተፈላጊዎችን ንኡሳን ክሂሎች በገለጻ ለይቶ ለማስቀመጥና ትኩረት ሰጥቶ ለማለማመድ እንዲቻል ነው ። ቋንቋን በማስተማር ሂደት የቋንቋ ክሂሎች በአንድነትና በተናጠል ሊዳብሩ ይችላሉ ። በአንድ ክሂል ላይ ማተኮር ወይም አንዱን ክሂል ማዳበር ማለት ሌሎችን ክሂሎች በፍጹም አለማን ጋት ማለት አይደለም ።

እያንዳንዱ ክሂል በተናጠልና በጋራ ሊዳብር ይችላል፣/እንደርዉድ፣ 1989/። በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን ላይ አራቱም የቋንቋ ክሂሎች በአንድ ላይ ተቀናጅተው ሊቀርቡ ይችላሉ ። በአላማ ፣ በዝርዝር አላማና በይዘት ምርጫ ላይ ግን እያንዳንዱ ክሂል በተናጠል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ።

የቋንቋ ክሂሎች አንዱ በሌላው ውስጥ የሚገኙ፣ እርስ በርስ የተሳሰሩ ቢሆኑም እንኳ አንዱ ክሂል ትኩረት ሰጥቶ ለማዳበር ፣ የተፈለገውን ያህል ዳብሮም እንደሆነ ለመከታተል ክሂሎችን ነጣጥሎ ማየቱም አስፈላጊ ነው ። ማዳመጥን በተመለከተ፣ ከተማሪው የሚጠበቀውን የማዳመጥ ችሎታ ለመወሰን ፣ በተለያዩ የማዳመጥ አይነቶች ለማለማመድና የተለያዩ የማዳመጥ ዘዴዎችን ለተማሪው ለማስጨበጥ የሚያስችሉ ይዘቶችን ለመቀረጽ የሚቻለው ክሂሉን ከሌሎች ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ከማቅረብ በተጨማሪ በተናጠልም ትኩረት ሲሰጠው ነው ።

" <u>ዝርዝር አላማ</u> "

ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች አንድ ዓይነት ዝርዝር አላማዎች ቀርበዋል ። የትኛው ዝርዝር አላማ ለየትኛው ክሂል እንደሆነ ተለይቶ አልተገለጸም ። በአንደኛ ሴሚስተር አንድ ዝርዝር አላማ ብቻ:- 'ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ያዳብራሉ' ተብሎ ቀርቧል ፤ በየትኛው ክሂል አንጻር እንደሚከናወን ግልጽ አይደለም ። ከዚህም በላይ እንዲዳብር የተፈለገው ክሂል ሳይሆን <u>አስተሳሰብ</u> ነው ። በሁለተኛ ሴሚስተርም እንዲሁ አንድ ዝርዝር አላማ ብቻ ቀርቧል ። 'የተወሰነ ሀሳብ በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴን ያዳብራሉ' ይላል ። በዚህ ዝርዝር አላማ እንዲዳብር የሚፈለገው ችሎታ በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴ ነው ። ይህም አገላለጹ እንደሚያስረዳው ትኩረቱ የመናገር/በራስ አባባል የሚቀርበው በጽሁፍ ከሆነም የመጻፍ/ክሂል ላይ ነው ። በእርግጥ በራስ አባባል ለማቅረብ አስቀድሞ ማዳመጥን ወይም ማንበብን ይጠይቃል ። ሆኖም ግን ከላይ የቀረበው ዝርዝር አላማ አቀራረብ እንደሚያመለክተው የማዳመጥን ወይም የማንበብን ክሂል ለማዳበር ታቅዷል፣ ወይም የማዳመጥ ክሂል ላይ

ሠንጠረዥ፡ 1 የማዳመጥን ክሂል በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለማዳበር በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች ::

| የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ | ገጽ | ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| የውይይት ስርአት | 22 | በጥብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት | 65 |
| የክርክር ስርአት | 23 | | |
| የጭውውት ስርአት | 24 | ፍሬ ሃሳቦችን በማስታወሻ መያዝ | 66 |
| የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት | 60 | አንዱ ርእስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ | 66 |

ለፍላጎት አስቧ የተዘጋጁ መጠይቆችን ጥናቱ የሚመለከታቸው የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ፣ መምህራንና የመርሀ ትምህርት አዘጋጆች እንዲሞሉት ተመርጠዋል ::

መጠይቁን እንዲሞሉ የተመረጡ ተማሪዎችን ቢ ተመለከት ናሙና የተወሰደው በመጀመሪያ በአዲስ አበባ የሚገኙ ሃያ ዘጠኝ የመንግሥት፣ የህዝብና የግል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ዝርዝር በፊደል ተራ ቀደም ተከተላቸው በመመዝገብና በሰባተኛው ተራ ቁጥር ላይ የተመዘገበውን ት/ቤት በመምረጥ በእኩል ዕድል ሰጪ የናሙና አወሳሰድ ስልት አራት ት/ቤቶች ለጥናቱ ተመርጠዋል ::

እነርሱም :- 1. ቦሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
2. አየር ጤና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
3. ከፍተኛ 12 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
4. ዳግማዊ ምኒልክ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

ናቸው :: እነዚህ በአዲስ አበባ ከሚገኙ ሃያ ዘጠኝ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 13.7 %ቱን ይይዛሉ ::/ት/ ቤቶቹን በፊደል ተራ ቀደም ተከተላቸው መሠረት የሚያሳይ ዝርዝር በአባሪ 7 ይመለከታል/::

በናሙና ት/ቤቶች ከሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ ከእያንዳንዱ ት/ቤት ሰባ አምስት ተማሪዎችን በጠቅላላው ሦስት መቶ ተማሪዎችን፣ ከየክፍሉ በግምታዊ የናሙና አወሳሰድ ስልት በመምረጥና በአንዱ ክፍል ውስጥ በመሰብሰብ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል :: ተማሪዎቹ መጠይቁን በሚሞሉበት ሰዓት በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል:: በናሙና ት/ቤቶች ከሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መሀከል መጠይቁ በተሰራጨበት ወቅትና ቀደም ሲል የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህር የሆኑና የነበሩ ሁሉም የመምህራን መጠይቁ እንዲሞሉ [illegible]

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ያዙራል በሱ ለመደምደም ያዳግታል ::

በአላማ ደረጃ የማዳመጥ ክሂል ከመናገር ክሂል ጋር ተዳብሎ በመቀረቡ ዝርዝር አላማ ሲነደፍም ተለይቶ ትኩረት ሳያገኝ ቀርቷል::ወደ ይዘቱ ስንመጣ ከላይ እንደተገለጸው ይዘቱ በዝርዝር አላማው የቀረቡት ጉዳዮች ወደ ደንቡ ትምህርትነት የሚተረጎሙበት ክፍል ነው :: በዝርዝር አላማዎቹ ላይ የታየው የማዳመጥ ክሂል ትኩረት ማጣት በይዘት ምርጫው ላይ ምን ያህል ተንጸባርቆ እንደሆነ በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን ::

1: <u>የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ሆን ብለው የተመረጡ ይዘቶች</u>

1.1 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ለማዳበር በተመረጡት ይዘቶች የሚከተሉትን ልምምዶች እንዲያከናውኑ ይጠበቃል :-

<u>የውይይት ስርአት</u>

ተማሪዎቹ በተወሰነ ርእስ ላይ ከተለያዩ ቦታዎች ሀሳብ አሰባስበው በመምጣት በቡድን በቡድን ሆነው ይወያያሉ፤ አንዱ ቡድን ሲወያይ ሌላው ያዳምጣል ፤ ተራቸውን ጠብቀው ይናገራሉ ፤ በንግግር ብቻ ለማቀረብ የማያመቹ ሀሳቦችን በስዕላዊ መገለጫዎች አስደግፈው ያቀርባሉ፣ የውይይትን ፍሬ ነገር የማሳለፍና የመጫል ስርአትን ይለማመዳሉ ::

- በዚህ ልምምድ ሊዳበር የሚችል የማዳመጥ ንኡስ ክሂል=ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ የማዘጋጀት ፤ ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት ::

<u>የክርክር ስርአት</u>

በዚህ ይዘት ተማሪዎቹ ስላደመጡት ክርክር በምክንያት የተደገፈ አስተያየት መስጠትን፣ አንዱን ርእስ በመደገፍ ወይም በመቃወም መከራከርን፣ በተሰጣቸው ርእስ በአንዱ ወቅት ተዘጋጅተውበት በሌላ ጊዜ ደግሞ ሳይዘጋጁበት መከራከርን፣ ተቃዋሚው ክፍል ከሚያቀርበው ሀሳብ መከራከሪያ ነጥብ መግኘትን ይለማመዳሉ ::

- በዚህ ልምምድ ሊዳበሩ የሚችሉ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች =የተደመጠውን ነገር ቀደም ብሎ ስለጉዳዩ ካለ እውቀት ጋር ማገናዘብ ፤ ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት፣ ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት ::

የጭውውት ስርአት

በዚህ ዘዴ ተማሪዎች በሬዲዮና በቴሌቪዥን ከሚሰሟቸው ጭውውቶች መሀከል ጠቃሚ ናቸው በለው የሚያምኑባቸውን መርጠው ለክፍል ጓደኞቻቸው ፕሮግራም አቀራረቦችን መስለው ያቀርባሉ ፤ ቁም ነገር አዘል ጭውውት ያደርጋሉ ::

- በዚህ ልምምዱ ሊዳበር የሚችል የማዳመጥ ንኡስ ክሂል=ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት ::

1.2: የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተወሰነን ሀሳብ በራስ አባባል የማቀረብ ዘዴን ለማዳበር በተመረጠው ዘዴ የሚከተሉትን ተግባሮች ያከናውናሉ ::—

የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት

በዚህ ዘዴ ተማሪዎች የአንዱን ድርጊት መንስኤ ካዳመጡ በኋላ ውጤቱ ሊሆኑ የሚችሉትን በመገመት ይናገራሉ ፤ ስለተፈጸመ ድርጊት አዳምጠው የድርጊቱን መንስኤ ይገምታሉ ፤ የመንስኤና የውጤትን ግንኙነትና ልዩነት ያውቃሉ ::

- በዚህ ልምምዱ ሊዳበር የሚችል የማዳመጥ ንኡስ ክሂል = የንግግሩን ተከታይ ክፍሎች አስቀድሞ የመገመት ችሎታ ::

2. ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ ዘዴዎች

እነዚህ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት ዋና ዓላማ የመጻፍን ክሂል ለማዳበር ሆኖ ሣለ አገረ መንገዳቸውን የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ዘዴዎች ናቸው ::

በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት

በዚህ ዘዴ ተማሪዎች በሚያዳምጡት ንግግር ውስጥ ተጨባጭ ሀቅ የሆኑ ነገሮችንና የተናጋሪውን የግል አስተያየቶች ለይተው ያዳምጣሉ :: ሀቅ ነው ወይም የግል አስተያየት ነው ያሉትን ምክንያት ይናገራሉ ::

- በዚህ ልምምድ የሚዳበሩ ንኡሳን የማዳመጥ ክሂሎች፡ ስለሚደመጠው ነገር አጠቃላይ ግንዛቤ መውሰድ ፣ ተናጋሪው የሚሰጠውን መረጃ ስሜቱን መገንዘብ ፣ የተደመጠውን ነገር ቀደም ብሎ ስለ ጉዳዩ ካለ እውቀት ጋር ማገናዘብ ፣ ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት ።

## ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ

በዚህ ይዘት ለተማሪዎች የሚያዳምጡት ምንባብ ይቀርብላቸዋል ። ካደመጡት ያገኙትን ፍሬ ሀሳብ በማስታወሻ ይዘው ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሰማሉ ፤ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ያዳመጡትን ዜና ዋና ዋና ሀሳብ ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሰማሉ ።

- በዚህ ልምምድ ሊዳበሩ የሚችሉ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች ፡ ከሚያዳምጡት ውስጥ ፍሬ ሀሳቡን ለይቶ ማስታወሻ መያዝ፣ ከሚደመጠው ረጅም ንግግር አብይ ሀሳብ ወይም ጭብጥ ማውጣት

## አንዱን ርእስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቀረብ

በዚህ ይዘት ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ውይይት በማዳመጥ በውይይቱ ውስጥ የቀረበውን ሀሳብ በራሳቸው አባባል ያቀርባሉ ።

- በዚህ ልምምድ ሊዳበሩ የሚችሉ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች፡ ያዳመጡትን በራስ አባባል የማቀረብ ዘዴ፣ ስለሚደመጠው ነገር አጠቃላይ ግንዛቤ መውሰድ፣ የማይጠቅሙ መረጃዎችንና ድግግሞሽን መለየት ፣ ከረጅም ንግግር አብይ ሀሳብ ወይም ጭብጥ ማውጣት ።

የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራሉ ተብለው የተመረጡትን አራት ይዘቶችም ሆነ ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር ተመርጠው አገረ መንገዳቸውን የማዳመጥን ክሂል የዳሰሱትን ይዘቶች ስንመረምር ለእያንዳንዱ ንኡስ ክሂል ትኩረት ሰጥተው በግልጽና በዝርዝር ባያቀርቡም ከሞላ ጎደል ከላይ የተዘረዘሩትን የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች ሊያዳብሩ እንደተፈለገ ይዘቱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ በሚጠቁመው የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን በሚለው የመርሀ ትምህርቱ ክፍል ከቀረቡ ዝርዝር ነገሮች ለመረዳት ተችሏል ።

.../41

ከላይ በቀረቡት ይዘቶች የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ታቅዷል? የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ ይዘቶቹ በተተረጎሙበት የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን ላይ ሁለት አይነት ነገሮች ይታያሉ :: እነርሱም :—

1. ይዘቱን በተመለከተ አስፈላጊውን እውቀት ማስጨበጥና
2. ክሂሉን በልምምዱ ማዳበር ናቸው ::

አስፈላጊውን እውቀት ማስጨበጥን በተመለከተ ስለወይይት፣ክርክርና ጭውውት ስርአቶች፣ ስለመንስኤና ውጤት ግንኙነትና ልዩነት፣'ማሳወቅ' 'ማስተማር'፣ 'ማስገንዘብ'በሚሉ አንቀጾች የተገለጹ በይዘቱ ስለቀረበው ጉዳይ እውቀት የሚያስገኙ ዝርዝር ነገሮች ቀርበዋል:: እነዚህ እውቀቶች ክሂሉን ለማዳበር በሚከናወን ተግባራዊ ልምምድ ላይ ጠቀሜታ አላቸው :: ለክፍሉ በተዘጋጀው የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የወይይት፣ የክርክር፣ ወዘተ ... መምሪያዎች ተብለው የቀረቡትን ስናይ ግን የትምህርቱ ትኩረት የመናገር ክሂል ላይ እንጂ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር አለመሆኑን እንገነዘባለን :: በወይይቶች ፣ በክርክሮች፣ ወዘተ...እንዴት ማዳመጥ እንዳለብትና ለዚህም የሚረዱትን ንኡሳን የማዳመጥ ክሂሎች እንዲለማመዱ አይጠቁምም::/ አባሪ 6ን ይመለከቷል/::

ከላይ በይዘቶቹ አማካይነት ሊዳበሩ ይችላሉ የተባሉት የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በግልጽና በዝርዝር አለመቀረባቸውንና በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ስራ ክንውን ስር በቃላት ታጅለውና ተድበሰበሰው የተኛውን ክሂል ማዳበር እንደተፈለገ ለመለየት አሻሚ በሆነ መንገዱ ተጽፈው መገኘታቸውን አይተናል :: ተማሪዎቹ ይወያያሉ፣ ይከራከራሉ፣ ጭውውት ያደርጋሉ ፣ ወዘተ ... ሲሉ በወይይቱ ፣ በክርክሩና በጭውውቱ ጊዜ የሚተኮሩባቸው የማዳመጥ ዋናና ንኡሳን ክሂሎች የትኞቹ እንደሆኑ በይዘቱ ላይ በግልጽ አልተነገረም :: መርሀ ትምህርቱን ተንተርሶ የትምህርት መረጃዎችን እንደመማሪያ መጽሀፍት ያሉትን የሚያዘጋጁ ባለሙያ ወይም ትምህርቱን ለተማሪዎቹ የሚያስተላልፍ እያንዳንዱ መምህር በግልጽ ያልተቀመጠውን የትምህርት ይዘት በተለያየ መንገዱ ሊተረጉመው ይችላል :: ከዚህም የተነሳ እያንዳንዱ መምህር የተለያየ የትኩረት አቅጣጫን ይዞ ያስተምራል ማለት ነው:: የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች በአጠቃላይ አላማ፣ በዝርዝር አላማና በይዘት አመራረጥ ረገዱ በአንዱ ላይ መቀረባቸው ደግሞ ለዚህ አይነት የትኩረት አቅጣጫ መለያየት ተጨማሪ አስተዋጽኦ አለው ::

በዝግጁ ጽሁፎች ቀጥታ እንዳየነው የማዳመጥን ክሂል በሚያዳብሩ ይዘቶች ውስጥ የተለያዩ የማዳመጥ አይነቶች ሊቀርቡ ይችላሉ :: ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ ለማህበራዊ ምለለስ ማዳመጥና ለመረጃ መሻት ማዳመጥ ናቸው:: ከላይ በዝርዝር ያየናቸው ይዘቶች ከጭውውት ስርአት በስተቀር ሁሉም በመረጃ መሻት የማዳመጥ አይነት ላይ ያተኮሩ ናቸው :: ይህ ሁኔታ እንደርሰንና ሊንች/1988/ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማዳመጥን ትምህርት ይዘት በተመለከተ ተማሪው የማህበራዊ ምለልስ ክሂሎችን ለማዳበር በህብረሰቡ ውስጥ ሰፊ እድል ስላለው ፣ በትምህርት ቤት በይበልጥ ሊተኮርባቸው የሚገባው የመረጃ መሻት ክሂሎች ላይ ነው :: በማለት ካሰነዘሩት ሀሳብ ጋር ይስማማል::

የቋንቋ ትምህርት ይዘትን ስናነሳ ሌላው ሊታይ የሚገባው ጉዳይ የይዘት ቅንብር ነው :: የይዘት ቅንበር ፣ የይዘት ተከታታይነትን፣ ተለጣጣቂነትንና አንድነትን ይመለከታል ::በዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ውስጥ ያለውን የማዳመጥ ክሂል የይዘት ቅንብር ስንመለከት ተከታታይነትንና ተለጣጣቂነትን በተመለከተ በሁለቱም ሴሚስተሮች የቀረቡት ይዘቶች አንዱ በሌላው ላይ ተመስርቶ በየጊዜው እያደገ በሚሄድ ቀደም ተከተል አልቀረቡም:: በማዳመጥ የሚፈጸሙ ተግባሮች ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ እንደሚያደርጉት እንደርሰንና ሊንች ሲያስረዱ :- ወዲያውኑ ምላሽ የሚሹ ተግባሮች፣ካዳመጡ በኋላ ተፈላጊውን መረጃ መርጦ ከሚፈጸሙ ተግባሮች ይልቅ ቀላል ናቸው ፤ እነዚህ ደግሞ በተራቸው በስሜታዊና በተጨባጭ አስተያየቶች መሀከል ያለውን ልዩነት መገንዘብን ከሚጠይቅ የማዳመጥ ተግባር ይልቅ ቀላል ናቸው ይላሉ :: /እንደርሰንና ሊንች 1988/ በዚህ መሠረት በአንደኛው ሴሚስተር በቀረቡት ይዘቶች የሚፈጸሙትን የማዳመጥ ተግባሮች ስንመለከት፣ በሦስተኛው ይዘት /የጭውውት ስርአት /የቀረበው ተግባር :- ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት—ወዲያው ምላሽ የሚሻ ተግባር ነው ፣ በአንደኛውና በሁለተኛው ይዘቶች /የውይይት ስርአት፣ የክርክር ስርአት በቀደም ተከተል/ ከሚፈጸሙ ተግባሮች መሀከል ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት፣ የሚደመጠውን ነገር ቀደም ብሎ ስለጉዳዩ ካለ እውቀት ጋር ማገናዘብ የሚሉ ይገኙባቸዋል ::

በሦስተኛው ይዘት ከሚፈጸመው የማዳመጥ ተግባር ይልቅ በአንደኛውና በሁለተኛው ይዘቶች የሚፈጸሙት የማዳመጥ ተግባራት የሚደመጠውን ነገር መሮምሮ ከሌሎች ካልተነገሩ ሁኔታዎች ጋር አገናዝቦ መረዳትን ስለሚጠይቁ ከባድ ናቸው :: በሁለተኛ ሴሚስተር በቀረበው ይዘት የሚፈጸመው የማዳመጥ ተግባር :- የንግግሩን ተከታታይ ክፍሎች አስቀድሞ መገመት ተጨባጭ በሆኑ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ለምምዱ ቢሆን ፣ በአንደኛው ሴሚስተር ከምናገኘው —ተጨባጭ

አውነትንና የግል አስተያየትን መለየት ከሚለው የተናጋሪውን አስተሳሰብ መገንዘብን ከማሻ የማዳመጥ ተግባር ይልቅ ቀላል ነው :: በዚህ መሠረት በአንዱ ሴሚስተር ውስጥም ሆነ በተከታታይ ሴሚስተሮች የቀረቡት የማዳመጥ ይዘቶች ደረጃ በደረጃ ከቀላል ወደ ከባድ እያደጉ የሚሄዱ አይደሉም :: ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት በሌለበት ሁኔታም ስለይዘት አንድነት መናገር አይቻልም፤ ምክንያቱም አንድነት ከተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ይገኛልና ነው ::

ካጠቃላይ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡት ይዘቶች የሚከተሉት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ታይተውባቸዋል ::

<u>ደ ካ ማ ጎ ኖ ች :-</u>

1. ሌሎችን ክሂሎች ለማዳበር ከተመረጡት ይዘቶች ጋር ሲነጻጸሩ በቁጥር በጣም አነስተኛ ናቸው ለየአሰማው የተመረጡት ይዘቶች ብዛት አማካይ 10.6ሲሆን የማዳመጥ ይዘቶቹ ብዛት 4 ወይም ከጠቅላላው በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች 7.5 % ብቻ ነው ::

2. በየሴሚስተሩ ተመጣጣኝ አቀራረብ አይታይም፤ ለዚህም በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተሰጠ ምክንያት የለም :: በአንደኛው ሴሚስተር ሦስት ይዘቶች ተመርጠው ሲቀርቡ በሁለተኛው ሴሚስተር አንድ ይዘት ብቻ ተመርጦ ቀርቧል ::

3. በይዘቶቹ የተኛውን ክሂል ለማዳበር እንደተፈለገ በግልጽና በዝርዝር አልተጠቀሰም፤ ለምሳሌ "የውይይት ስርአት" ሲል በዚህ ይዘት አንጻር ሊተኮርባቸው የሚገቡ አጠቃላይና ንኡሳን የማዳመጥ ክሂሎች የትኞቹ እንደሆኑ አልተጠቀሰም ::

4. ግልጽነት ይጎድላቸዋል፤ አሻሚ ትርጉም ይሰጣሉ :: ለዚህም ምክንያቶቹ

   - በአጠቃላይ አላማና በዝርዝር አላማ ስር የማዳመጥ ክሂል ከመናገር ክሂል ጋር ተዳብሎ መቅረቡ፤

   - ይዘቶቹም ሆኑ በይዘቶቹ አንጻር የቀረቡት ልምምዶች የተገለ ጹበት ቋንቋ፤ ናቸው ::

5. የክብደት ደረጃቸውን ጠብቀው እያደጉ የሚሄዱ ልምምዶች አለቀረቡባቸውም ፤

– በአንደኛውና በሁለተኛው ይዘቶች ከቀረቡት ልምምዶች ይልቅ በሶስተኛው ይዘት የቀረበው በጣም ቀላል ነው ፤ በአንደኛው ሴሚስተር የቀረቡ ልምምዶች በሁለተኛው ሴሚስተር ከቀረበው የከበዱ ናቸው ::

ጠንካራ ጎን :-

1. ገለጻነት በጎደለው ሁኔታ በያሳት ተጨበሰበሰው ቢገኙም አንዳንዱ የማዳመጥ ዋናና ንኡሳን ክሂሎችን ለማዳበር ሞክረዋል:- ምሳሌ :- ተጨባጭ እውነትንና የግል አስተያየትን መለየት ፣ ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት ፣ ወዘተ ...

2. በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማዳመጥ ትምህርት ይበልጥ ሊተኮርባቸው በሚገቡ የይዘት አይነቶች ላይ በይበልጥ አተኩረዋል:-ለምሳሌ:- ለመረጃ መሻት ማዳመጥ::

## 4.2 <u>የመጠይቆች ምላሽ</u>

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ሲዘጋጅ የተማሪዎችን ችሎታና ፍላጎት በማጥናት በዚያ ላይ ተመስርቶ ስለመዘጋጀቱ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት አዘጋጆች ምላሽ በቃሉ ገደለ በተማሪው ፍላጎትና ችሎታ ላይ መመስረቱን ቢጠቅሙም በመርሀ ትምህርቱ መግቢያ ላይ የመርሀ ትምህርቱ አዘጋጃጀት በጥናት ላይ ያለ ተመሠረተ መሆኑ ተገልጿል ::
/ ትምህርት ሚኒስቴር የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ፣ ዘጠነኛ ክፍል፣ 1984/ ::

መርሀ ትምህርቱ የዚህ ክፍል ተማሪዎች አንድን የቋንቋ ትምህርት ይዘት ከዚህ እስከዚህ ድረስ ሊማሩ ይችላሉ በሚል ግምት ላይ ተመስርቶ ነው የተዘጋጀው :: ለዚህም በየክፍሉ የሚቀርቡ ይዘቶችን የሚያመለክት የትምህርት ይዘቶች ሠሌዳ /ፍሰው ቻርት/ በማዘጋጀት ፣ ለየክፍሉ የሚሆኑ መርሀ ትምህርቶች ሲዘጋጁ ይዘቶቹ ከዚያ ላይ ይመረጣሉ :: እንደመርሀ ትምህርት ባለሙያዎቹ አባባል የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ለመምረጥ የተጠቀሙበት የትምህርት ይዘቶች ሠሌዳ በ1972 ዓ/ም የተዘጋጀ ነው :: በሰሌዳው ላይ እንደሚታየው በዘጠነኛ ክፍል የማንበብና የመናገር ክሂሎችን እንዲያዳብሩ የተመረጡት ይዘቶች በአንደኛው ሲሚስተር የቀረቡት /የውይይት ስርአት፣ የክርክር ስርአት፣ የጭውውት ስርአት/ ይዘቶች ለተማሪው መሰጠት የሚጀምሩት ከሁለተኛ ክፍል ጀምሮ ነው ፣ በሁለተኛው ሲሚስተር የቀረበው /የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት /ይዘት ለተማሪው መሰጠት የሚጀምረው ከሰባተኛው ክፍል ጀምሮ ነው :: ዘጠነኛ ክፍል ሲደርስ ተማሪው ቀደም ባሉት ክፍሎች የይዘቶቹን መምሪያዎች ወይም ደንብ እያወቀና እየተለማመደባቸው እንደመጣና እዚህ ክፍል ሲደርስ የይዘቱን መምሪያዎች ወይም ደንብ የማሳወቅ ሁኔታ አብቅቶ የይዘት ልምምዱ ብቻ እንደሚቀጥል ይገለጻል :: በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሚታየው
በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሚታየው ሁኔታ ግን ከዚህ የተለየ ነው :: "የውይይት ስርአት" "የክርክር ስርአት"፣ "የጭውውት ስርአት" የሚሉት አገላለጾች ይዘቶቹ ለዘጠነኛ ክፍል

ተማሪዎች ገና በመምሪያና በፍች ደረጃ እንደሚቀርቡ ያሳያሉ ። በዚህም በተጨማሪ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥም መምሪያዎች ቀርበዋል ። ወርሀ ትምህርቱ ሲዘጋጅ ለይዘት ምርጫ መሠረት አድርጎታል የተባለውን የትምህርት ይዘቶች ሠሌዳ አሠራር እንጂ ለለ ተከተሉም ።

በዚህ አይነት መንገድ ተመርጠው የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከተማሪው ችሎታና ፍላጎት ጋር ምን ያህል ሊጣጣሙ እንደሚችሉ ለማየት በተማሪው ፣ በቋንቋ መምህሩና በወርሀ ትምህርት ባለሙያው የሚሞሉ መጠይቆች በማዘጋጀት መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል ። በመጠይቆች አማካይነት የተገኙ መረጃዎች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል ።

4.2.1. ከተማሪው መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ሠንጠረዥ 4፡- የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ

| አፍ መፍቻ ቋንቋ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| አማርኛ | 278 | 92.6 |
| ኦሮምኛ | 12 | 4.0 |
| ትግርኛ | 5 | 1.6 |
| ሌሎች | 5 | 1.6 |

ሠንጠረዥ 5፡- የተማሪዎች ዕድሜ

| ዕድሜ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| 13 አመትና በታች | 31 | 10.3 |
| ከ14–16 ዓመት | 222 | 74.0 |
| ከ17–19 " | 47 | 15.6 |
| 20 ዓመትና በታች | — | — |

ሠንጠረዥ 6፣ የተማሪዎች ጾታ

| ጾታ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| ወንድ | 125 | 41.6 |
| ሴት | 175 | 58.3 |

በዘጠነኛ ክፍል የምናገኛቸው ተማሪዎች አብዛኞቹ /92.6 %/ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ሲሆን ፤ 7.2 % አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚችሉ ናቸው ። አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋቸው ከሆኑት መካከል 4 % በኦሮምኛ ፤ 1.6 % በትግርኛ ፤ 1.6 % በአረብኛ፣ በጉራጌኛ፣ በሃዲይኛና በሰልጥኛ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ናቸው ።

ተማሪዎች ለትምህርት የቀረበላቸውን ቋንቋ በአፍ መፍቻነት ወይም በሁለተኛ ቋንቋነት የሚያውቁት መሆኑን ለይቶ ማወቅ የትምህርት ይዘትን በመምረጥ ረገድ ቋንቋው ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ሰዎች የሚፈጽሟቸውን ስህተቶችና የሚቸገሩባቸውን የቋንቋ ክፍሎች በይዘቱ ውስጥ ለማካተትና በቂ ልምምድ ለማቅረብ ያስችላል ።

በዚህ ክፍል በሚገኙ ተማሪዎች 41.6 %ወንዶች ሲሆኑ 58. 3 %ሴቶች ናቸው ። አብዛኞቹ ተማሪዎች / 74 % / ከ14-16 ዓመት ሲሆኑ፣ 15.6 % ከ17-19 ዓመት ፤ 10.3 % 13 ዓመትና ከዚያ በታች ናቸው ። የተማሪዎችን ዓራ ማወቅ ተማሪዎች በተወሰነ የዕድሜ ክልልና የጾታ ሁኔታ ሊኖራቸው የሚችለውን ዝንባሌ በመገመት የትምህርቱን ይዘት ከዝንባሌያቸው ጋር የተስማማ አድርጎ ለመምረጥ ይረዳል ።

...// 48

ማስታወሻ :- ከዚህ በኋላ በሚቀርቡ ሠንጠረዦች ውስጥ የመለሶችን የምርጫ ደረጃ የሚያሳዩ ቁጥሮች ትርጉም እንደየጥያቄው አቀራረብ የሚከተሉትን ይመስላል ::

5 = በጣም ከፍተኛ / በጣም በከፍተኛ ደረጃ
4 = ከፍተኛ / በከፍተኛ ደረጃ
3 = መካከለኛ /በመካከለኛ ደረጃ
2 = ዝቅተኛ / በዝቅተኛ ደረጃ
1 = በጣም ዝቅተኛ / በጣም በዝቅተኛ ደረጃ
0 = ምንም /ምንም ጥቅም አይሰጥም
x = መልስ ያልሰጡ

ወይም

4 = ሁል ጊዜ
3 = ብዙ ጊዜ
2 = በመጠኑ
1 = አንዳንድ ጊዜ
0 = በፍጹም
x = መልስ ያልሰጡ

ጥያቄ 1 : አማርኛን የሚማሩበት አላማ :-
ሠንጠረዥ 7 የማኅመጥን ከዜሎ ማኅበር ለሚለው አላማ የተሰጠ ምላሽ ፦

| ምርጫ | ብዛት | % |
| --- | --- | --- |
| 5 | 173 | 57.6 |
| 4 | 63 | 21.0 |
| 3 | 47 | 15.6 |
| 2 | 5 | 1.6 |
| 1 | 5 | 1.6 |
| 0 | 3 | 1.0 |
| x | 4 | 1.3 |

አማርኛን የሚማሩበትን አላማ እንዲያመለክቱ በተሰጣቸው ዝርዝር ውስጥ "አዳምጦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር" የሚለው አላማ 57.6 % በጣም በከፍተኛ ሁኔታ አላማቸውን ይገልጻል ሲሉ ፣ 21 % በከፍተኛ ሁኔታ ፣ 15.6 % በመካከለኛ ሁኔታ አላማቸውን ይገልጻል ብለዋል ። "የማዳመጥ ችሎታዬን ማዳበር ዋንኛውን የምማርበት አላማዬ አይደለም" ያሉት 1 % ብቻ ናቸው ።

2. የሚከተሉትን የማዳመጥ ተግባራት ምን ያህል ታዘወትራለህ /ሽ

ሠንጠረዥ 8:- ተማሪዎች የሚያዘወትሯቸው የማዳመጥ ተግባራት:-

| ምርጫ | የጥያቄ-ው ቁጥር | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2.1 | | 2.2 | | 2.3 | | 2.4 | | 2.5 | | 2.6 | | 2.7 | | 2.8 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 4 | 93 | 31.0 | 192 | 64.0 | 128 | 42.6 | 54 | 18.0 | 68 | 22.6 | 96 | 32.0 | 67 | 29.0 | 121 | 40.3 |
| 3 | 70 | 23.3 | 68 | 22.6 | 78 | 26.0 | 47 | 15.6 | 49 | 16.3 | 60 | 20.0 | 69 | 23.0 | 77 | 25.6 |
| 2 | 91 | 30.3 | 27 | 9.0 | 61 | 20.3 | 65 | 21.6 | 65 | 21.6 | 59 | 19.6 | 47 | 15.6 | 61 | 20.3 |
| 1 | 36 | 12.0 | 8 | 2.6 | 18 | 6.0 | 82 | 27.3 | 81 | 27.0 | 59 | 19.6 | 68 | 22.6 | 30 | 10.0 |
| 0 | 7 | 2.3 | 3 | 1.0 | 9 | 3.0 | 38 | 12.6 | 29 | 9.6 | 10 | 3.3 | 20 | 6.6 | 6 | 2.0 |
| x | 3 | 1.0 | 2 | 0.6 | 6 | 2.0 | 14 | 4.6 | 8 | 2.6 | 16 | 5.3 | 9 | 3.0 | 5 | 1.6 |

የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ማዉቅ በትምህርት ቤት በሚቀርብላቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ዉስጥ ከተማሪዎች ልምዱ ጋር የሚስማማና ከትምህርት ቤት ዉጭ ጥቅም ላይ ሊያዉሉት የሚችሉትን ይዘት ለመምረጥ ይረዳል :: በዚህ መሠረት የዚህ ክፍል ተማሪዎች አዘዉትረው የሚፈጽሟቸውን የማዳመጥ ተግባራት ተጠይቀው የሚከተሉትን መልሶች ሰጥተዋል ::

2.1 — የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን 31 % ሁልጊዜ ፣ 23.3 % ብዙ ጊዜ ፣ 30.3 % በመጠኑ ፣ 12 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጧለን ሲሉ ፣ 2.3 % በፍጹም እናዳምጥም ብለዋል ::

2.2 — በክፍል ዉስጥ መምህሩ የሚነግሯቸውን የአሰራር መመሪያ ፣ 64.0 % ሁልጊዜ ፣ 22.6 % ብዙ ጊዜ ፣ 9 % በመጠኑ ፣ 2.6 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጧለን ሲሉ ፣ 1 % በፍጹም እናዳምጥም ብለዋል ::

.../51

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

2.3 _ በአማርኛ ቋንቋ የሚሰጡ የሌሎች ትምህርቶችን ገለጻ 42.6 % ሁል ጊዜ ፣ 26 % ብዙ ጊዜ ፣ 20.3 % በመጠኑ ፣ አንዳ ንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ፣ 3 % በፍጹም አናዳምጥም ብለዋል ::

2.4 – በስልክ የሚተላለፉ መልእክቶችን 18 % ሁል ጊዜ ፣ 15.6 % ብዙ ጊዜ ፣ 21.6 % በመጠኑ 27.3 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ፣ 12.6 % በፍጹም አናዳምጥም ብለዋል ::

2.5 – ውይይቶችን ማዳመጥ ለሚለው 22.6 % ሁልጊዜ ፣ 16.3 % ብዙ ጊዜ፣ 21.6 % በመጠኑ፣ 27 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ ፣ 9.6 % በፍጹም አናዳምጥም ብለዋል ::

2.6 – የሌሎችን ጭውውት ማዳመጥ ለሚለው 32 % ሁልጊዜ ፣ 20 % ብዙ ጊዜ፣ 19.6 % በመጠኑ፣ 19.6 % አንዳንድ ጊዜ ፣ እናዳምጣለን ሲሉ 3.3 % በፍጹም አናዳምጥም ብለዋል ::

2.7 – በድምጽ ማጉያ የሚነገሩ ማስታወቂያዎችን 29 % ሁልጊዜ ፣ 23 % ብዙ ጊዜ፣ 15.6 % በመጠኑ፣ 22.6 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ ፣ 6.6 % በፍጹም አናዳምጥም ብለዋል ::

2.8 – በቃል የሚቀርቡ ጥያቄዎችን 40.3 % ሁልጊዜ ፣ 25.6 % ብዙ ጊዜ፣ 20.3 % በመጠኑ፣ 10 % አንዳንድ ጊዜ እናዳምጣለን ሲሉ ፣ 2 % በፍጹም አናዳምጥም ብለዋል ::

3. በክፍል ውስጥ የምታደምጠው ጉዳይ እንዴት ቢቀርብልህ ትመርጣለህ ?

ሠንጠረዥ 9 :- የማደመጥ ጉዳይ የአቀራረብ ዝንባሌ

| ምርጫ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| መምህሩ ቢያነቡት / ቢናገሩት | 222 | 74.0 |
| ተማሪው ቢያነበው / ቢናገረው | 17 | 5.6 |
| በካሴት ተቀድቶ ቢቀርብ | 50 | 16.6 |
| መልስ ያልሰጡ | 11 | 3.6 |

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲያዳምጡ የሚቀርብላቸውን ምንባብ ወይም ንግግር እንዴት ቢቀርብላቸው እንደሚመርጡ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ 74. % "መምህሩ ቢያቀርቡት"፤ 16.6 %" በካሴት ተቀድቶ ቢቀርብ"፤ 5.6 " ተማሪዎች ቢያቀርቡት "በማለት መልሰዋል ::

4. የሌሎችን ሰዎች ንግግር ስታዳምጥ /ጪ የሚከተሉት ችግሮች ለንተ/ ቺ ችግር የሚሆኑትን ደረጃ አመልክት / ቺ :-

ሠንጠረዥ 10 :- የተማሪዎች የማዳመጥ ችግር

| ምርጫ | የ ጥ ያ ቄ ው ቁ ጥ ር | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 4.1 | | 4.2 | | 4.3 | | 4.4 | | 4.5 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 75 | 25.0 | 55 | 18.3 | 63 | 21.0 | 39 | 13.0 | 46 | 15.3 |
| 4 | 38 | 12.6 | 37 | 12.3 | 39 | 13.0 | 60 | 20.0 | 31 | 10.3 |
| 3 | 70 | 23.3 | 69 | 23.0 | 59 | 19.6 | 55 | 18.3 | 65 | 21.6 |
| 2 | 40 | 13.3 | 73 | 24.3 | 62 | 20.6 | 56 | 18.6 | 58 | 19.3 |
| 1 | 69 | 23.0 | 62 | 20.6 | 63 | 21.0 | 82 | 27.3 | 95 | 31.6 |
| x | 8 | 2.6 | 4 | 1.3 | 14 | 4.6 | 8 | 2.6 | 5 | 1.6 |

ተማሪዎቹ የማዳመጥ ችግር ካለባቸው ለችግሩ ምክንያት የሆኑትን እንዲጠቁሙ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ መሠረት :-

4.1 ÷ የንግግሩን ድምጸት ለይቶ አለማወቅ ፤ 25 % በጣም ከፍተኛ 12.6 % ከፍተኛ፤ 23.3 % መካከለኛ ፤ 13.3 % ዝቅተኛ ፤ 23 % በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው በማለት መልሰዋል ፤

4.2 — በቋንቋ ውስጥ የሚላሉና የሚጠበቁ ድምጾችን ለይቶ አለማወቅ 18.3 % በጣም ከፍተኛ ፤ 12.3 % ከፍተኛ ፤ 23 % መካከለኛ 24.3 ዝቅተኛ ፤ 20.6 % በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው በማለት መልሰዋል ::

4.3 — የቋንቋውን ባለቤቶች ባህል አለማወቅ 21 % በጣም ከፍተኛ ፤ 13 % ከፍተኛ ፤ 19.6 % መካከለኛ ፤ 20.6 % ዝቅተኛ፤ 21 % በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው ብለዋል ::

4.4 — የተናጋሪውን ስሜት አለመረዳት 13 % በጣም ከፍተኛ ፣ 20 % ከፍተኛ 18.3 %. መካከለኛ ፣ 18.6 % ዝቅተኛ፣ 27.3 %በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው ብለዋል::

4.5 — ፍሬ ነገሩን ለይቶ ማዳመጥ አለመቻል— 15.3 % በጣም ከፍተኛ፣ 10.3 % ከፍተኛ ፣ 21.6 %. መካከለኛ 19.3 % ዝቅተኛ፣ 31.6 % በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው በማለት መልሰዋል::

5. በሚከተሉት ይዘቶች ጓደኞችህ/ሽ/ን ማኅበር በሀብረተሰቡ ውስጥና በትምህርት ቤት ለማዳበር ምን ያህል ያበረክታሉ/ቻ/ለ?

ሠንጠረዥ 11 :- የማዳበር ይዘቶች ጠቀሜታ

| | የጥያቄው ቁጥር | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5.4 | | 5.5 | | 5.6 | | 5.8 | | 5.10 | | 5.11 | | 5.12 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 118 | 39.3 | 127 | 42.3 | 134 | 44.6 | 91 | 30.3 | 95 | 31.6 | 151 | 50.3 | 83 | 27.3 |
| 4 | 80 | 26.6 | 73 | 24.3 | 67 | 22.3 | 78 | 26.0 | 87 | 29.0 | 56 | 18.6 | 81 | 27.0 |
| 3 | 58 | 19.3 | 48 | 16.0 | 54 | 18.0 | 77 | 25.6 | 77 | 25.6 | 66 | 22.0 | 58 | 19.3 |
| 2 | 32 | 10.6 | 23 | 7.6 | 24 | 8.0 | 29 | 9.6 | 29 | 9.6 | 16 | 5.3 | 33 | 11.0 |
| 1 | 9 | 3.0 | 27 | 9.0 | 15 | 5.0 | 19 | 6.3 | 16 | 5.3 | 8 | 2.6 | 18 | 6.0 |
| × | 3 | 1.0 | 2 | 0.6 | 6 | 2.0 | 6 | 2.0 | 7 | 2.3 | 11 | 3.6 | 4 | 1.3 |

..// 55

በጥያቄ ቁጥሮች ከ5.1–5.3 ፣ 5.7 ና 5.9 የቀረቡት ጥያቄዎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሌሉ ይዘቶች በመሆናቸው እዚሁ ለትንተና አላስፈለገም ::

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች ለተማሪዎቹ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ ለማወቅ ተጠይቀው በሁሉም ይዘቶች አብዛኞቹ ተማሪዎች / ከ16 % – 50.3 % ድረስ / " በመካከለኛ ደረጃ ያስፈልገናል " ከሚለው አንስቶ " በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ያስፈልገናል " እስከሚለው ድረስ ባሉት መለቦች ውስጥ ይገኛሉ ፤ ከ2.6 – 11 % የሚደርሱ ተማሪዎች ይዘቶች " ዝቅተኛ " ና " በጣም ዝቅተኛ " በሆነ ደረጃ ያስፈልገናል በማለት መልሰዋል ::

6. ከምታዳምጠው/ጪው ውስጥ ምን ያህሉን በእርግጠኝነት ታዳምጣለህ /ጫለሽ ?

ሠንጠረዥ 12 :– በማዳመጥ ችሎታ የመተማመን መጠን

| ምርጫ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| ከ20 % በታች | 21 | 7.0 |
| ከ21 – 40 % | 36 | 12.0 |
| ከ41 – 60 %. | 71 | 23.6 |
| ከ61 – 80 % | 97 | 32.3 |
| ከ80 % በላይ | 71 | 23.6 |
| መልስ ያልሰጡ | 4 | 1.3 |

ተማሪዎች በየምክንያቱ ከሚያዳምጡት ውስጥ ምን ያህሉን በእርግጠኝነት እንደሚያዳምጡ ተጠይቀው 23.6 % ከ80 % በላይ፣ 32.3 % ከ61 – 80 %፣ 23.6 % ከ41–60 % ፣ 12 % ከ21 – 40 %፣ 7 % ከ20 % በታች በሆነ እርግጠኝነት እናዳምጣለን ብለዋል ። በዚህ መሠረት አብዛኞቹ ተማሪዎች /79.6 %/ ከ40 % በላይ በሆነ እርግጠኝነት ሲያዳምጡም ፣ ከ40 % በታች በሆነ እርግጠኝነት የሚያዳምጡ ተማሪዎች ቁጥርም /19 % / ከግምት የሚገባና የማዳመጥ ልምምዱ በብዛት ማቀረብ እንደሚያስፈልግ የሚጠቁም ነው ።

7. በቋንቋ ክሂሎች በተጠቀም /ሚ/ ችሎታህ /ሽ/ ምን ያህል ነው ?

ሠንጠረዥ 13 :– በቋንቋ ክሂሎች የመጠቀም ችሎታ

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 7.1 | | 7.2 | | 7.3 | | 7.4 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 100 | 36.6 | 56 | 18.6 | 105 | 35.0 | 95 | 31.6 |
| 4 | 89 | 29.6 | 78 | 26.0 | 109 | 36.0 | 68 | 22.6 |
| 3 | 79 | 26.3 | 107 | 35.6 | 59 | 19.6 | 72 | 24.0 |
| 2 | 9 | 3.0 | 37 | 12.3 | 20 | 6.6 | 40 | 13.3 |
| 1 | 11 | 3.6 | 19 | 6.3 | 4 | 1.3 | 22 | 7.3 |
| × | 2 | 0.6 | 3 | 1.0 | 3 | 1.0 | 3 | 1.0 |

በአማርኛ ቋንቋ በሚጠቀሙበት ጊዜ በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ምን ያህል ችሎታ እንዳላቸው ተጠይቀው በሰጡት መልስ አዳምጦ የመረዳት ችሎታን /7.1/ በተመለከተ 36.6 % በጣም ከፍተኛ ፣ 29.6 % ከፍተኛ ፣ 26.3 % መካከለኛ ችሎታ አለን ሲሉ 3 % ና 3.6 % በቅደም ተከተል ችሎታችን ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው በማለት መልሰዋል ።

8. በቋንቋው በምትጠቀም /ሚ በት ጊዜ የሚከተሉት ክሂሎች ለአንተ /ቺ/ ጠቀሜታቸው ምን ያህል ነው ?

ሠንጠረዥ 14:- የክሂሎች መዳበር የሚያስገኘው ጠቀሜታ መጠን :-

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 8.1 | | 8.2 | | 8.3 | | 8.4 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 217 | 72.3 | 145 | 48.3 | 191 | 63.6 | 184 | 61.3 |
| 4 | 56 | 18.6 | 81 | 27.0 | 57 | 19.0 | 60 | 20.0 |
| 3 | 19 | 6.3 | 54 | 18.0 | 40 | 13.3 | 33 | 11.0 |
| 2 | 2 | 0.6 | 11 | 3.6 | 3 | 1.0 | 10 | 3.3 |
| 1 | 1 | 0.3 | 3 | 1.0 | 1 | 0.3 | 3 | 1.0 |
| 0 | 3 | 1.0 | 1 | 0.3 | 3 | 1.0 | 5 | 1.6 |
| x | 2 | 0.6 | 5 | 1.6 | 5 | 1.6 | 5 | 1.6 |

በቋንቋው በሚጠቀሙበት ጊዜ በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ምን ያህል እንደሚጠቀሙ ተጠይቀው ፣ የማዳመጥን ክሂል /8.1/ በተመለከተ 72.3 % በጣም በከፍተኛ ፣ 18.6 % በከፍተኛ ፣ 6.3 % በመካከለኛ ደረጃ ክሂሉ ይጠቅመናል ብለዋል :: የክሂሉ ጠቀሜታ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው ያሉት 0.6 % ና 0.3 % በቅደም ተከተል ሲሆኑ ፣ 1 % ክሂሉ ምንም አይጠቅመንም ብለዋል :: አብዛኞቹ ተማሪዎች / 90.9 % / ክሂሉ በጣም እንደሚጠቅማቸው ነው ያመለከቱት ::በዚህ መሠረት የማዳመጥ ክሂል ለተማሪው በሚሰጠው ከፍተኛ ጠቀሜታ አንጻር በበቂ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳበር ይገባል፡

10. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ማዳመጥ የምትፈልገ/ጊ/ው የምንባብ ወይም የንግግር ርእስ ስለምን የሚናገር ቢሆን ይሻላል?
ሠንጠረዥ 15 የተማሪዎች ዝንባሌ:- የሚዳመጥ ጉዳይ:-

| | የ ተ ማ ሪ ው ቁ ጥ ር | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 10.1 | | 10.2 | | 10.3 | | 10.4 | | 10.5 | | 10.6 | | 10.7 | | 10.8 | | 10.9 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 186 | 62.0 | 207 | 69.0 | 95 | 31.6 | 134 | 44.6 | 200 | 66.6 | 143 | 47.6 | 49 | 15.3 | 180 | 60_0 | 193 | 64.3 |
| 4 | 58 | 19.0 | 62 | 20.6 | 31 | 10.3 | 70 | 23.3 | 53 | 17.6 | 74 | 24.6 | 19 | 6.3 | 37 | 12.3 | 40 | 13.3 |
| 3 | 38 | 12.6 | 15 | 5.0 | 45 | 15.0 | 62 | 20.6 | 24 | 8.0 | 30 | 10.0 | 24 | 8.0 | 23 | 7.6 | 29 | 9.6 |
| 2 | 36 | 2.0 | 6 | 2.0 | 46 | 15.3 | 24 | 8.0 | 11 | 3.6 | 24 | 8.0 | 39 | 13.0 | 21 | 7.0 | 12 | 4.0 |
| 1 | 8 | 2.6 | 7 | 2.3 | 75 | 25.0 | 5 | 1.6 | 7 | 2.3 | 23 | 7 .6 | 161 | 53.6 | 37 | 12.3 | 17 | 5.6 |
| × | 4 | 1.3 | 3 | 1.0 | 8 | 2.6 | 5 | 2.6 | 5 | 1.6 | 6 | 2.0 | 8 | 2.6 | 2 | 0.6 | 9 | 3.0 |

..// 59

የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂሎ ለማዳበር የሚቀርቡ ይዘቶችን
ከዝንባሌያቸው ጋር የሚጣጣምና ስሜታቸው የሚስብ ፤ እንዲያዳምጡ የ
ሚያነቃቃ እንዲሆን ተማሪዎች ለማዳመጥ በሚቀርብላቸው ምንባብ ወይም
ንግግር ውስጥ እንዴት ያሉ ጉዳዮች ቢቀርቡላቸው እንደሚወዱ ተጠይቀው
ሲመልሱ፤ በጣም በከፍተኛ ደረጃ ከመረጧቸው ርእሶች ውስጥ 69 %
ስለትምህርት፤ 66.6 % ስለጤና ፤ 64.3 % ስለቤተሰብ ፤ 62 %
ስለሀገር፤ 60 % ስለ ሃይማኖት፤ 47.6 % ሣይንስ ነክ 44.6 %
ስለ ጓደኝነት ፤ 31.6 % ስለፍቅር ፤ 16.3 % ስለ ፖለቲካ የሚ
ናገሩ ርእሶችን እንመርጣለን ብለዋል ። በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ከ
መረጧቸው ርእሶች መሀከል 53.6 % ስለፖለቲካ ፤ 25 % ስለፍቅር፤
12.3 % ስለ ሃይማኖት፤ 7.6 % ሳይንስ ነክ ፤ 5.6 % ስለቤተሰብ
2.3 % ስለትምህርት ፤ 2.3 % ስለጤና፤ 2.6 % ስለሀገር ፤
1.6 % ስለጓደኝነት የሚናገሩ ርእሶችን በማለት መልሰዋል ።

የተማሪዎችን በጣም ከፍተኛ ምርጫና በጣም ዝቅተኛ ምርጫ ስን
መለከት ተማሪዎች በጣም በከፍተኛ ደረጃ ማዳመጥ እንፈልጋለን ካሏቸው
ርእሶች መሀከል ፖለቲካ ዝቅተኛውን ቁጥር / 16.3 % / ሲይዝ ፤
ትምህርት ከፍተኛውን ቁጥር /69. % / ይዟል ። በጣም ዝቅተኛ
ምርጫችን ና ቸው ካሏቸው መካከል ደግሞ ፖለቲካ ከፍተኛውን ቁጥር 53.6
% / ሲይዝ ፤ ጓደኝነት የሚለው ርእስ ዝቅተኛውን ቁጥር / 1.6 %/
ይዟል ።

11. በሚከተሉት የማዳመጥ ችሎታን በሚመለከቱ ዓ.ነገሮች አማካይነት ችሎታህ/ሽ/ ምን ያህል እንደሆነ አመልክት :–

ሠንጠረዥ 16 የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የ ጥ ያ ቄ ው ቁ ጥ ር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 11.1 | | 11.2 | | 11.3 | | 11.4 | | 11.5 | | 11.6 | | 11.7 | | 11.8 | | 11.9 | | 11.10 | |
| ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 80 | 26.6 | 83 | 27.6 | 71 | 23.6 | 56 | 18.6 | 59 | 19.6 | 59 | 19.6 | 88 | 29.3 | 116 | 38.6 | 113 | 37.6 | 96 | 32.0 |
| 75 | 25.0 | 123 | 41.0 | 109 | 36.3 | 88 | 29.3. | 65 | 21.6 | 80 | 26.6 | 89 | 29.66 | 77 | 25.66 | 101 | 33.6 | 107 | 35.6 |
| 88 | 29.3 | 268 | 22.6 | 95 | 31.6 | 93 | 31.0 | 93 | 31.0 | 81 | 27.0 | 91 | 30.3 | 65 | 21.6 | 57 | 19.0 | 63 | 21.0 |
| 24 | 8.0 | 14 | 4.6 | 12 | 4.0 | 38 | 12.6 | 48 | 16.0 | 44 | 14.6 | 15 | 5.0 | 18 | 6.0 | 11 | 3.6 | 11 | 3.6 |
| 16 | 5.3 | 5 | 1.6 | 4 | 1.3 | 12 | 4.0 | 25 | 8.3 | 25 | 8.3 | 9 | 3.0 | 6 | 2.0 | 8 | 2.6 | 1 | 0.3 |
| 17 | 5.6 | 7 | 2.3 | 9 | 3.0 | 13 | 4.3 | 10 | 3.3 | 11 | 3.6 | 8 | 2.6 | 18 | 6.0 | 10 | 3.3 | 22 | 7.3 |

ከሠንጠረዥ 16 የቀጠለ

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የ ጥ ያ ቄ ው ቁ ጥ ር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 11.11 | | 11.12 | | 11.13 | | 11.14 | | 11.15 | | 11.16 | | 11.17 | | 11.18 | | 11.19 | | 11.20 | |
| ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 115 | 38.3 | 74 | 24.6 | 95 | 31.6 | 88 | 29.3 | 108 | 36.0 | 89 | 29.6 | 45 | 15.0 | 80 | 26.6 | 60 | 20.0 | 120 | 40.0 |
| 87 | 29.0 | 107 | 35.6 | 111 | 37.0 | 89 | 29.6 | 99 | 33.0 | 86 | 28.6 | 55 | 18.3 | 86 | 28.6 | 80 | 26.6 | 80 | 26.6 |
| 49 | 16.3 | 67 | 22.3 | 56 | 18.6 | 91 | 30.3 | 60 | 20.0 | 75 | 25.0 | 107 | 35.6 | 77 | 25.6 | 98 | 32.6 | 64 | 21.3 |
| 21 | 7.0 | 28 | 9.3 | 23 | 7.6 | 15 | 5.0 | 18 | 6.0 | 25 | 8.3 | 49 | 16.3 | 32 | 10.6 | 39 | 13.0 | 18 | 6.0 |
| 7 | 2.3 | 7 | 2.3 | 7 | 2.3 | 9 | 3.0 | 7 | 2.3 | 20 | 6.6 | 37 | 12.3 | 13 | 4.3 | 19 | 6.3 | 14 | 4.6 |
| 21 | 7.0 | 17 | 5.6 | 8 | 2.6 | 8 | 2.6 | 8 | 2.6 | 5 | 1.6 | 7 | 2.3 | 12 | 4.0 | 4 | 1.3 | 4 | 1.3 |

..// 61

በጥያቄ 11 ላይ ለቀረቡት ሃያ የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች በአንድነት ታይተዋል ። በዚህም መሠረት አያንዳንዱ ጥያቄ ሶስት መቶ ምላሽ ስለሚኖረው በጠቅላላ ስድስት ሺህ ምላሾች ይኖራሉ ።

የሚከተለው ሠንጠረዥ የምላሾቹን አማካይ ውጤት ያሳያል ።

ሠንጠረዥ 17 :- የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ ማጠቃለያ

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር | |
|---|---|---|
| | ከ 11.1 — 11.20 | |
| | አማካይ | % |
| 5 | 84.75 | 28.25 |
| 4 | 90.15 | 30.05 |
| 3 | 76.25 | 25.4 |
| 2 | 25.35 | 8.4 |
| 1 | 12.5 | 4.1 |
| x | 11.0 | 3.6 |

የተማሪዎችን አጠቃላይ የማዳመጥ ችሎታ ለመገመት በተለያዩ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች ያላቸውን ችሎታ እንዲያመለክቱ ሲቀረበላቸው ጥያቄ ተማሪዎች በሰጧቸው መልሶች 28.25 % በጣም ከፍተኛ ችሎታ፣ 30.05 % ከፍተኛ ችሎታ ፣ 25.4 % መካከለኛ ችሎታ ፣ 8.4 %. ዝቅተኛ ችሎታ ፣ 4.1 % በጣም ዝቅተኛ ችሎታ እንዳላቸው አመለከተዋል ። አብዛኞቹ ተማሪዎች / 83.7 % / መካከለኛ ችሎታና ከዛ በላይ አጠቃላይ የማዳመጥ የችሎታ ደረጃ እንዳላቸው ነው ያመለከቱት ።

...//62

### 4.2.2 ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

መምህራን የተማሪዎቻቸውን የቋንቋ ችግር አስመልክቶ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ምክንያት የሚታይ ችግር እንዳለባቸው ተጠይቀው 85 % ቱ ተማሪዎቻቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ምክንያት የሚታይ የቋንቋ ችግር አለባቸው ሲሉ 15 % ቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ምክንያት የተለየ የቋንቋ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች እንዳላጋጠሟቸው ገልጸዋል ::

የተማሪዎች መጠይቅ ምላሽ እንደሚያሣየው 92.6 % አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ነው :: ከመምህሩ መጠይቅ በተገኘው ምላሽ ላይ 85 % መምህራን አጋጥሞናል ያሉት የተማሪዎቻቸው የቋንቋ ችግር ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሳይሆን ሌሎች ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ :: እሉ የተባሉት የቋንቋ ችግሮች የሥነ ልሣን ችሎታን የተመለከቱ ናቸው :: ለምሣሌ ቃላትን በትክክል ያለመናገር፣ ድምፆችን በአማርኛ ስርአት አለመጥራት፣ በንግግርና በጽሁፍ የስዋሰው ሕግ አለመጠበቅ ወዘተ ... የሚሉ ይገኙባቸዋል ::

ሠንጠረዥ 18 :- የተማሪዎች የቋንቋውን ባህሪ አገላለጾች የመረዳት ሁኔታ በመምህራን ምዘና

| የችሎታ ደረጃ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| በሚገባ ይረዳሉ | 5 | 25 |
| በመካከለኛ ደረጃ ይረዳሉ | 11 | 55 |
| በዝቅተኛ ደረጃ ይረዳሉ | 2 | 10 |
| በጭራሽ አይረዱም | – | – |
| አስተያየት የለኝም | – | – |
| መልስ ያልሰጡ | 2 | 10 |

የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች ማወቅ በኅብረተሰቡ ውስጥ ለማዳመጥ በጣም አስፈላጊ ነው ። ይህን በተመለከተ መምህራን የተማሪዎችን ችሎታ ሲገሊጠቁሙ ተጠይቀው 26 % በሚገባ ይረዳሉ ፣ 55 % በመካከለኛ ደረጃ ይረዳሉ ፣ 10 % በዝቅተኛ ደረጃ ይረዳሉ በማለት መልሰዋል ። አብዛኞቹ መምህራን /55 % / ተማሪዎቻቸው የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች በመረዳት ረገድ ችሎታቸው መካከለኛ እንደሆነ ነው የገለጹት ። በዚህ መሠረት የዚህ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂሎቻቸውን ለማዳበር በሚቀርቡላቸው ይዘቶች ውስጥ የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች አዳምጠ ለመረዳት የሚያስችላቸው ልምምዶችን የማቅረብ አስፈላጊነትን ሊጠቁም ይችላል ።

ሠንጠረዥ 19 :- <u>መምህራን ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩት ክሂል ።</u>

| የትኩረት ደረጃ | ክሂል | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ማዳመጥ | | መናገር | | ማንበብ | | መጻፍ | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1ኛ | 14 | 70 | 4 | 20 | 3 | 15 | 5 | 25 |
| 2ኛ | 1 | 5 | 11 | 55 | 4 | 20 | 2 | 10 |
| 3ኛ | 2 | 10 | 2 | 10 | 8 | 40 | 7 | 35 |
| 4ኛ | 3 | 15 | 3 | 15 | 5 | 25 | 6 | 30 |

መምህራን የዚህ ክፍል ተማሪዎችን የቋንቋ ክሂል በማዳበር ረገድ የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት ለየትኛው ክሂል እንደሆነ ተጠይቀው በ1ኛ ደረጃ ትኩረት ከሚሰጧቸው ክሂሎች መሀከል 70 % ለማዳመጥ ፣ 20 % ለመናገር 15 % ለማንበብ ፣ 25 % ለመጻፍ ክሂል ትኩረት የሚሰጡ መሆኑን አመልክተዋል ። የማዳመጥን ክሂል በተመለከተ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መሀከል 70 % በአንደኛ ደረጃ ፣ 5 % በሁለተኛ ደረጃ ፣ 10 % በሶስተኛ ደረጃ ፣ 15 % በአራተኛ ደረጃ ትኩረት እንሰጣለን ብለዋል ።

ለማዳመጥ ክሂል የሰጡትን የትኩረት ደረጃ አስመልክቶ ምክንያታቸውን ተጠይቀው የተለያዩ ምክንያቶችን ሰጥተዋል ። ከነዚህም ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ከፍተኛ ትኩረት እንሰጣለን ያሉት / በ1ኛና በ2ኛ ደረጃ የመረጡት/ ከሰጧቸው ምክንያቶች :-

- ተማሪዎች የማዳመጥን ክሂል ካላዳበሩ በሌሎች ክሂሎች የመጠቀም ችሎታቸው የተሟላ ስለማይሆን ፤
- የተነገረውን በማዳመጥ አዳምጠው በመናገር ክሂሉን ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ፤ በሌሎች ክሂሎች ግን እምብዛም አይጠቀሙም ፤
- ማስታወሻ ለመውሰድና ምንባቦችን አዳምጦ መልመጃ ለመሥራት ስለሚጠቅማቸው፤
- የማዳመጥ ክሂላቸው በሚገባ ያልዳበረ ስለሆነና መዳበር ስላለበት፤
- ተማሪዎች ካላዳመጡ ሊናገሩ፣ ሊያነቡ ወይም ሊጽፉ ስለማይችሉ፤
- የማዳመጥ ችሎታቸው ከፍተኛ ካልሆነ ምንባቡን አዳምጠው መረዳት ስለማይችሉ፤ የሚሉ ይገኙበታል ።

ለክሂሉ በሶስተኛና በአራተኛ ደረጃ ትኩረት አንሰጥለን ያሉ መምህራን ካቀረቧቸው ምክንያቶች መሀከል የሚከተሉት ይገኙበታል:-

- በመለመጃው የቀረቡት የማዳመጥ መለማመጃዎች አጭርና አነስተኛ በመሆኑ፤
- የማዳመጥ ዕድሉ ሰፊ በመሆኑ ከሌሎች ክሂሎች በተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛል በማለት ፤
- ተማሪዎቹ በሌሎቹ ክሂሎች ፍላጎታቸው አነስተኛ ስለሚሆን በነሱ ላይ አተኩራለሁ፤
- ለተማሪዎች በመናገር ይልቅ እራሳቸው እንዲሞክሩ ለማድረግ ነው በማለት መልሰዋል ።

ሠንጠረዥ 20 የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ዝርዝር ልምምዶች ብዛት

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 6.2 | | 6.3 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 1 | 5 | 1 | 5 |
| 4 | 5 | 25 | 11 | 55 |
| 3 | 8 | 40 | 3 | 15 |
| 2 | 6 | 30 | 4 | 20 |
| 1 | – | – | 1 | 5 |

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሚዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የተነደፉት ዝርዝር አላማዎች በጥያቄ ቁጥር 6.2 እና 6.3 ላይ የተገለጹት ብቻ ስለሆኑ እነዚህ ለትንተና የቀረቡትም እነዚህ ብቻ ናቸው ::

መምህራን በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሚዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የተመረጡ ዝርዝር አላማዎች የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት ምን ያህል እንደሚያሟሉ እንዲያመለክቱ ተጠይቀው ፣ " ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ማዳበር " የሚለውን ዝርዝር አላማ 5 %. በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ፣ 25 % በከፍተኛ ደረጃ ፣ 40 % በመካከለኛ ደረጃ ፣ 30 % በዝቅተኛ ደረጃ ፣ ያሟላል በማለት መልሰዋል ::

" የተወሰነ ሀሳብን በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴ " የሚለውን ዝርዝር አላማ 5 %. በጣም በከፍተኛ ደረጃ ፣ 55 % በከፍተኛ ደረጃ ፣ 15 % በመካከለኛ ደረጃ 20 % በዝቅተኛ ደረጃ 5 % በጣም በዝቅተኛ ደረጃ የተማሪዎችን ፍላጎት ያሟላል ብለዋል :: " ተጠያቃዊ አስተሳሰብን ማዳበር " የሚለው ዝርዝር አላማ በአብዛኛው መምህራን በመካከለኛ ደረጃ የተማሪዎችን ፍላጎት ያሟላል ተብሎ ሲጠየቅ በከፍተኛና በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ያሟላል ያሉና በዝቅተኛ ደረጃ ያሟላል ያሉ መምህራን ቁጥር እኩል / 30 % / ነው :: የተወሰነ ሃሳብን በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴ የሚለውን ዝርዝር አላማ አብዛኛው መምህራን /55 %/ በከፍተኛ ደረጃ የተማሪዎችን ፍላጎት ያሟላል ሲሉ ፣ 25 % መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎት በዝቅተኛና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ነው የሚያሟላው ብለዋል ::

ሠንጠረዥ 21 የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ይዘቶች ብቃት

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር 8.4 | | 8.5 | | 8.6 | | 8.8 | | 8.10 | | 8.11 | | 8.12 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 2 | 10 | 3 | 15 | 4 | 20 | 2 | 10 | 1 | 5 | 4 | 20 | 3 | 15 |
| 4 | 11 | 55 | 9 | 45 | 6 | 30 | 4 | 20 | 9 | 45 | 8 | 40 | 6 | 30 |
| 3 | 3 | 15 | 6 | 30 | 5 | 25 | 7 | 35 | 7 | 35 | 4 | 20 | 55 | 25 |
| 2 | 3 | 15 | 2 | 10 | — | — | 4 | 20 | 2 | 10 | 3 | 15 | 3 | 15 |
| 1 | — | — | — | — | 2 | 10 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 2 | 10 |
| × | 1 | 5 | — | — | 1 | 5 | 2 | 10 | — | — | — | — | 1 | 5 |

በጥያቄ ቁጥሮች ከ8.1–8.3፣ 8.7 ና 8.9 የቀረቡት ጥያቄዎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሌሉ ይዘቶች በመሆናቸው እዚሁ ለትንተና አላስፈለ ገም ::

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች የተማሪዎቻቸውን የማዳመጥ ክሂል የማዳበር ብቃታቸውን እንዲገልጹ ተጠይቀው ፣ " የውይይት ሥርአት " 10 % በጣም ከፍተኛ ፣ 55 %፣ 75 % መካከለኛ ፣ 15 % ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ክሂሉን የማዳበር ብቃት አለው ሲሉ ፣ የጭውውት ስርአት 15 % በጣም ከፍተኛ ፣ 45 % ከፍተኛ ፣ 30 % መካከለኛ ፣ 10 % ዝቅተኛ ክሂሉን የማዳበር ብቃት አለው ብለዋል :: የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት የሚለው ይዘት 10 % በጣም ከፍተኛ፣ 20 % ከፍተኛ ፣ 35 %. መካከለኛ ፣ 20 % ዝቅተኛ ፣ 5 % በጣም ዝቅተኛ ክሂሉን የማዳበር ብቃት አለው ብለዋል ::

በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት 5 % በጣም ከፍተኛ 45 % ከፍተኛ ፣ 35 % መካከለኛ ፣ 10 % ዝቅተኛ ፣ 5 % በጣም ዝቅተኛ ክሂሉን የማዳበር ብቃት አለው ብለዋል ፍሬ ሃሳቦችን በማስታወሻ መያዝ 20 %በጣም ከፍተኛ 40 %ከፍተኛ ፣ 20 % መካከለኛ፣ 15 %፣ ዝቅተኛ 5 % በጣም ዝቅተኛ ክሂሎችን የማዳበር ብቃት አለው ብለዋል:: አንዱን ርእስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ 15 % በጣም ከፍተኛ ፣ 30 % ከፍተኛ ፣ 25 % መካከለኛ ፣ 15 % ዝቅተኛ ፣ 10 % በጣም ዝቅተኛ ፣ ክሂሉን የማዳበር ብቃት አለው ብለዋል ::

መካከለኛ የብቃት ደረጃና ከዚያ በላይ ብቃት አላቸው የተባሉት ይዘቶች ውይይት 80 %፣ጭውውት 90 % ፣ ክርክር 75 % ፣ የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት 65 % ፣ የጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት 85 %፣ፍሬ ሃሳብን በማስታወሻ መያዝ 80 %፣አንዱ ርዕስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ 70 % ሲሆኑ ፣ እነዚህን ይዘቶች ክሂሉን የማዳበር ብቃታቸው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው ያሉ መምህራን በዛት ከአማካይ እስከ በጣም ከፍተኛ ብቃት አለው ካሉት መምህራን በጣም ያነሰ ነው ::

.../68

ሠንጠረዥ 22 የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ደረጃ በመምህራን ምዘና

| | የ ጥ ያ ቄ ዎ ቁ ጥ ር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 9.1 | | 9.2 | | 9.3 | | 9.4 | | 9.5 | | 9.6 | | 9.7 | | 9.8 | | 9.9 | | 9.10 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 2 | 10 | 3 | 15 | — | — | 1 | 5 | 1 | 5 | — | — | 1 | 5 | 1 | 5 | — | — | — | — |
| 4 | 5 | 25 | 5 | 25 | 7 | 35 | 2 | 10 | 2 | 10 | 5 | 25 | 5 | 25 | 5 | 25 | 6 | 30 | 8 | 40 |
| 3 | 12 | 60 | 9 | 45 | 8 | 40 | 14 | 70 | 13' | 65 | 7 | 35 | 7 | 35 | 9 | 45 | 5 | 25 | 7 | 35 |
| 2 | 1 | 5 | 3 | 15 | 5 | 25 | 3 | 15 | 4 | 20 | 5 | 25 | 7 | 35 | 4 | 20 | 7 | 35 | 5 | 25 |
| 1 | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | 2 | 10 | — | — | 1 | 5 | 1 | 5 | — | — |
| × | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | 1 | 5 | — | — | — | — | — | — | — | — |

ከሠንጠረዥ 22 የቀጠለ

| | የ ጥ ያ ቄ ዎ ቁ ጥ ር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 9.11 | | 9.12 | | 9.13 | | 9.14 | | 9.15 | | 9.16 | | 9.17 | | 9.18 | | 9.19 | | 9.20 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 2 | 10 | — | — | 2 | 10 | — | — | 1 | 5 | — | — | — | — | — | — | — | — | 1 | 5 |
| 4 | 12 | 60 | 4 | 20 | 5 | 25 | 3 | 15 | 4 | 20 | 3 | 15 | 4 | 20 | 6 | 30 | 5 | 25 | 5 | 25 |
| 3 | 4 | 20 | 10 | 50 | 6 | 30 | 8 | 40 | 12 | 60 | 10 | 50 | 5 | 25 | 7 | 35 | 4 | 20 | 8 | 40 |
| 2 | 2 | 10 | 5 | 25 | 6 | 30 | 7 | 35 | 3 | 15 | 7 | 35 | 6 | 30 | 7 | 35 | 6 | 30 | 4 | 20 |
| 1 | — | — | 1 | 5 | 1 | 5 | 2 | 10 | — | — | — | — | 5 | 25 | — | — | 5 | 25 | 2 | 10 |
| × | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — | — |

..// 69

በጥያቄ ቁጥር 9 ላይ ለቀረቡ ሃያ የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ ጥያቄ ዎች የተሰጡ መልሶች በአንድነት ታዩ ተዋል ፡፡ በዚህም መሠረት አያንዳንዱ ጥያቄ ሃያ ምላሽ ስለሚኖረው በጠቅላላው አራት መቶ ምላሾች ይኖራሉ ፡፡ የሚከተለው ሠንጠረዥ የዚህን ምላሽ አማካይ ውጤት ያሳያል :-

ሠንጠረዥ 23 የተማሪዎች የማዳመጥ ችሎታ መገመቻ በመምህራን ምዘና-ማጠቃለያ

| | የጥያቄው ቁጥር | |
|---|---|---|
| | ከ9.1 — 9.2 | |
| ምርጫ | አማካይ | % |
| 5 | 0.8 | 4.0 |
| 4 | 5.05 | 25.25 |
| 3 | 8.25 | 41.25 |
| 2 | 4.85 | 24.25 |
| 1 | 1.0 | 5.0 |
| × | 0.05 | 0.25 |

መምህራን " ተማሪዎች በሚከተሉት የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎች ምን ያህል ችሎታ አላቸው ? " ብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት መልስ 4 % በጣም ከፍተኛ ፣ 25.25 % ከፍተኛ ፣ 41.25 መካከለኛ ፣ 24.25 % ዝቅተኛ ፣ 5 % በጣም ዝቅተኛ ችሎታ አንዳላቸው ጠቁመዋል ፣ ተማሪዎቹ በጣም ከፍተኛ ችሎታ እንዳላቸውና ችሎታቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳዩ መልሶች ብዛት በጣም አነስተኛ ነው ፡፡ አብዛኛዎቹ መምህራን የተማሪዎቻቸው የማዳመጥ ችሎታ መካከለኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ፣ ከፍተኛና ዝቅተኛ ነው ያሉትም ቁጥራቸው ተቀራራቢ ነው ፡፡

ሠንጠረዥ 24 የተማሪዎች አዳምጦ የመረዳት መጠን በመምህራን ምዘና

| ምርጫ | ብዛት | % |
|---|---|---|
| ከ20 % በታች | 1 | 5 |
| ከ21 –40 % | 5 | 25 |
| ከ41 –60 % | 9 | 45 |
| ከ61 – 80 % | 3 | 15 |
| ከ80 % በላይ | 2 | 10 |

መምህራን፣ ተማሪዎቻቸው እንዲያዳምጡ ከሚቀርብላቸው ጉዳይ ውስጥ ምን ያህሉን እንደሚያዳምጡ እንዲጠቁሙ ተጠይቀው ሲመልሱ ፣ 5 % ተማሪ ዎቻቸው ከ20 % በታች እንደሚያዳምጡ፣ 25 % ተማሪዎቻቸው ከ21–40 % እንደሚያዳምጡ ፣ 45 % ተማሪዎቻቸው ከ41–60 % እንደሚያዳምጡ፣ 15 % ተማሪዎቻቸው ከ61–80 % እንደሚያዳምጡ ፣ 10 % ተማሪ ዎቻቸው ከ80 % በላይ እንደሚያዳምጡ ገልጸዋል :: አብዛኛዎቹ መምህራን /70 %/ ተማሪዎቻቸው ከሚቀርብላቸው ውስጥ ከ40 % በላይ የሆነውን አዳምጠው እንደሚረዱ ሲገልጹ ፣ 30 %ቱ ተማሪዎቻቸው ከሚቀርብላቸው የሚዳመጥ ጉዳይ ውስጥ አዳምጠው የሚረዱት ከ40 % ያነሰ መሆኑን ገልጸዋል :: የተማሪዎቹ አዳምጠው የመረዳት ችሎታ ከ40 % ያነሰ ነው ያሉ መምህራን ቁጥር / 30 %/ከግምት የሚገባ ነው :: ስለሆነም የተማሪዎችን አዳምጦ የመረዳት ችሎታ የሚያዳብሩ በርካታ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ሊቀርቡ ያሻል ::

ሠንጠረዥ 25 በአማርኛ ደንብ የማዳመጥ ችሎታ ለሌሎች ትምህርቶች ያለው ጠቀሜታ

| | የጥያቄው ቁጥር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 41.1 | | 11.2 | | 11.3 | | 11.4 | | 11.5 | | 11.6 | | 11.7 | | 11.8 | | 11.9 | | 11.10 | | 11.11 | | 11.12 | |
| ምርጫ | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 8 | 40 | 4 | 20 | 1 | 5 | 1 | 5 | – | – | – | – | 1 | 5 | – | – | 4 | 20 | 1 | 5 | 1 | 5 | 2 | 10 |
| 4 | 7 | 35 | 2 | 10 | 1 | 5 | 3 | 15 | 2 | 10 | 3 | 15 | 6 | 30 | 5 | 25 | 6 | 30 | 8 | 40 | 4 | 20 | 12 | 60 |
| 3 | 3 | 15 | 6 | 30 | 6 | 30 | 5 | 25 | 5 | 25 | 5 | 25 | 10 | 50 | 9 | 45 | 5 | 25 | 7 | 35 | 7 | 35 | 1 | 5 |
| 2 | 1 | 5 | 6 | 30 | 6 | 30 | 8 | 40 | 7 | 35 | 6 | 30 | 1 | 5 | 4 | 20 | 4 | 20 | 2 | 10 | 7 | 35 | 4 | 20 |
| 1 | – | – | 1 | 5 | 4 | 20 | 2 | 10 | 5 | 25 | 5 | 25 | 1 | 5 | 1 | 5 | – | – | 1 | 5 | 1 | 5 | – | – |
| 0 | – | – | – | – | 1 | 5 | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – |
| × | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 1 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 |

"ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ከሄሏቸውን ማኅበራቸው ሌሎች ትምህርቶ ችን ለመከታተል ምን ያህል ይጠቀማቸዋል ?" ብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ መም ህራን በሰጡት መልስ መካከለኛና ከዚ በላይ ጠቀሜታ አለው ባሉት ውስጥ 90 % ለአማርኛ ፣ 60 % ለእንግሊዝኛ፣40 % ለ ሂሳብ ፣ 45 % ለ ባዮሎጂ፣ 35 % ለፊዚክስ ፣ 40 % ለኬሚስትሪ፣35 % ለ ታሪክ ፣ 70% ለጂኦግራፊ፣ 75 % ለአርት ፣ 80 % ለባልትና፣ 55 % ለምርት ቴክኖ ሎጂ፣ 75 % ለእስፖርት ትምህርቶች ይጠቀማል ብለዋል ::ጠቀሜታው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው ከ ብሉት ውስጥ ለ ሂሳብ ፣ ለባዮሎጂ፣ ለኬሚስትሪና ለ ፊዚክስ የሚሉት መልሶች ከፍተኛውን ቁጥር / ከ50 – 60 % ይዟል :: ይህም የሚያሳየው በአማርኛ ቋንቋ የማዳወቅ ከሄል መኅበር ከ ቁጥር ጋር የ ተያያዙና የሣይንስ ትምህርቶችን ለመከታተል ከሚሰጠው ጠቀሜታ ይልቅ ለሌሎች ትምህርቶች የሚሰጠው ጠቀሜታ እንደሚበልጥ ነው ::

## 4.2.3: ከመርሀ ትምህርት ባለሙያው መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ለመርሀ ትምህርት ባለሙያው የተዘጋጀውን መጠይቅ ሰባት የአማርኛ ትም ህርት ኤክስፐርቶች ሞልተዋል :: ከነዚህ ሁለቱ አፍ መፍቻቸው አማርኛ ሲሆን፣ አንዱ አፍ መፍቻው አማርኛና አረምኛ ነው :: ሰባቱም ወንዶች ሲሆኑ የትምህርት ደረጃቸው ቢኤና ከቢኤ በላይ ናቸው :: የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርትንና የ መማሪያ መጽሐፍትን በማዘጋጀት ሥራ ላይ ከሰባት እስከ በደብት አመት የቆዩ ናቸው ::

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጠው በበንተኛ ቋንቋነት እንደሆነ ተጠይቀው ሁለቱ "በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ነው" ሲሉ አንዱ ግን "እንደ አንድ የትምህርት አይነት ነው የሚሰጠው"በማለት መልሰዋል ::

ለዘጠነኛ ክፍል የሚሆኑ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲመረጡ በምን መመዘኛ እንደተመረጡ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አንዱ "በተማሪዎች ችሎታ"፣ ሌላኛው "የበርአተ ትምህርት አነሳደፍ መርሀ ላይ ተመስርቶ"፣ ሲሉ ሰባተ ኛው "በምሳ ጉዳል የተማሪው ፍላጎትና ችሎታ፣ ቋንቋው በት/ቤትና በኅብረተ ሰቡ ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት፣ የቋንቋው ሥነ ልሣናዊ ባህሪ በመመዘኛነት ተወስደው ነው" ብለዋል ::

ሁለቱ ለበቆሎ የሚሆኑ ወርሀ ትምህርትና የመማሪያ መጽሀፍት በአንድ ቡድን /ፓነል/ እንደሚዘጋጁ ገልጸዋል ። እንጁ ግን ለዚህ ጥያቄ መልስ አልሰጡም ።

ለዘጠነኛ ክፍል በሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ሊሰጠው የሚገባውን የትኩረት ደረጃ በተመለከተ ሁለቱ በአንደኛ ደረጃ ሊቀርብላቸው ይገባል ሲሉ ለዚህም የሰጡት ምክንያት፡—

1. የቋንቋ አካባቢያዊ መሠረቱ ማዳመጥ ስለሆነ ፣
2. በተግባራዊ እንቅስቃሴ በይበልጥ የሚሠራበት ነገር በመሆኑ የማዳመጥ ክሂል ከዳበረ አያሌ ተግባሮችን ማከናወን ይቻላል ። የሚሉ ናቸው ።

ሠንጠረዥ 26 የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች የብቃት ደረጃ በወርሀ ትምህርት ባለሙያው ምዘና ፣

..../74

ሠንጠረዥ 26 የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች የብቃት ደረጃ በመርሀ ትምህርት ባለሙያው ምዘና፡፡

| ምርጫ | የጥያቄው ቁጥር | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 6.4 | | 6.5 | | 6.6 | | 6.8 | | 6.10 | | 6.11 | | 6.12 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 5 | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 | – | | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 |
| 4 | 1 | 33.3 | 1 | 66.6 | 1 | 33.3 | 2 | 66.6 | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 |
| 3 | 1 | 33.3 | 1 | – | – | – | 1 | 33.3 | – | – | – | = | – | – |
| 2 | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | – | 1 | 33.3 |
| 1 | – | – | – | – | – | – | – | – | 1 | 33.3 | 1 | 33.3 | – | – |
| × | – | – | – | – | 1 | 33.3 | – | – | – | – | – | – | – | – |

በጥያቄ ቁጥሮች ከ6.1 – 6.3 ፣ 6.7 እና 6.9 የተገለጹት ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ያልቀረቡ ይዘቶች በመሆናቸውና እዚህ ለትንተናው ስለማያስፈልጉ አልቀረቡም ::

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በቀጥታ የማዳመጥን ክሂል እንዲያዳብሩ የቀረቡ ይዘቶች በመርሀ ትምህርት ባለሙያዎቹ ምዘና መሠረት ብቃት አላቸው ተብለዋል :: አብዛኞቹ በከፍተኛ ደረጃና በጣም በከፍተኛ ደረጃ ብቁ ናቸው ተብለዋል :: በጥያቄ ቁጥሮች 6.10 ፣ 6.11 እና 6.12 የቀረቡ ይዘቶችን 33.3 % በከፍተኛ ደረጃ፣ 33.3 % በጣም በከፍተኛ ደረጃ ክሂሉን ያዳብራሉ ሲሉ ፣ 33.3 % በዝቅተኛና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ነው ክሂሉን ሊያዳብሩ የሚችሉት ብለዋል :: ክሂሉን የማዳበር ብቃታቸው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው የተባሉት ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ሌሎች ክሂሎችን ለማዳበር ተቀርጠው አግረመንገዳቸውን የማዳመጥን ክሂል ያዳብራሉ የተባሉ ይዘቶች ናቸው ::

4.3 :- <u>የመጠይቆች ምላሽ ትንተናና ንጽጽር</u>

ከተማሪው ከመምህሩና ከመርሀ ትምህርት ባለሙያው መጠይቆች በተገኘው መረጃ መሠረት:-

1. በዘጠነኛ ክፍል የምናገኛቸው ተማሪዎች አብዛኞቹ / 92.6 % / አፋቸውን በአማርኛ የፈቱ ናቸው ፣ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ 7.3 % ናቸው :: በጾታ ረገድ የሴቶቹ ቁጥር ከወንዶቹ በ16.6 % ይበልጣል :: የዚህ ክፍል ተማሪዎች አብዛኞቹ ዕድሜያቸው ከ14–16 ዓመት ሲሆን ፣ ከ13 ዓመት በታችና ከ17 –19 ዓመት ዕድሜ የሆኑ ተማሪዎችም አሉ ::

የተማሪዎቹን ዳራ ማወቅ የምናቀርብላቸውን የትምህርት ይዘት በንመርጥ ትምህርቱ ከተማሪዎቹ ዳራ ጋር ተስማሚ እንዲሆን ለማድረግ ይረዳል :: ለምሳሌ ተማሪዎች በተወሰነ የዕድሜ ክልል ሊኖራቸው የሚችለውን ዝንባሌ መገመት ይቻላል፣ ወይም ደግሞ ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ካሉ የትምህርት ይዘት ሲመረጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ምክንያት የሚፈጸሙ ስህተቶች ካሉ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ይጠቁማል :: በዚህ መሠረት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ይዘቶችን ስንመርጥ በወጥነት የዕድሜ ክልል ለሚገኙ ተማሪዎች ሥነ ልቦና የሚስማሙና አፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ለሚማሩ ተማሪዎች የሚሆኑ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን መምረጥ እንደሚኖርብን መዘንጋት የለብንም ::

2. ተማሪዎቹ፣ ቋንቋውን ከሚማሩባቸው አላማዎች አንዱ አዳምጦ የመረዳት ችሎታቸውን ማዳበር መሆኑን ገልጸዋል ። 15.6 % በመካከለኛ ፣ 78.6 % በከፍተኛና በጣም በከፍተኛ ደረጃ አላማቸው መሆኑን ገለጸዋል ።ይህም ተማሪዎቹ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር በሚቀርቡ ትምህርቶች ላይ በጉ ለመለካከትና ዝንባሌ እንደሚኖራቸው ይጠቁማል ።

3. የተማሪዎችን በትምህርት ቤትና በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ ማወቅ ከተማሪዎቹ ለምዱ ጋር የሚስማማና ሊጠቅሙበት የሚችሉትን የቋንቋ ትምህርት ይዘት ለመምረጥ ይረዳል ።በዚህ መሠረት ተማሪዎች፣ የሚያዘወትሯቸውን የማዳመጥ ተግባራትና የማዳመጥ ችግሮቻቸውን በጠቅላላ መሠረት በትምህርት ቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ በተለያዩ የማዳመጥ ተግባራት ለምሳሌ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን፣ በክፍል ውስጥ ገለጻዎችን ፣ መመሪያዎችንና ጥያቄዎችን፣ በድምጽ ማጉያ የሚነገሩ ማስታወቂያዎችን፣ በበለከ የሚተላለፉ መልእክቶችን፣ ውይይቶችና ጭውውት ችን እንደሚያዳምጡ ገልጸዋል ።በነዚህ የማዳመጥ ተግባራት በፍጹም አንሰ ተፍም ያሉ ተማሪዎች "በበለከ የሚተላለፍ መልእክቶችን" ማዳመጥ ከሚለው በስተቀር /12.6 %/ በሌሎቹ ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ነው ።

ስለዚህ በመረጃው ላይ የሚታየውን ልዩነት መሠረት ለዚሁ በሁሉም የማዳመጥ ተግባራት ላይ የተመሠረተ ልምምድ በተለያየ መጠን ሊቀርብላቸው ይገባል ።

የማዳመጥ ችግሮቻቸውን በተመለከተ የማዳመጥ ችግሮች ይሆናሉ ተብለው በቀረቡላቸው አምስት ዝርዝሮች ውስጥ "የንግግሩን ድምጸት ለይቶ አለማወቅ" ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ የማዳመጥ ችግሬ ነው ያሉትና፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅ ተኛ ችግሬ ነው ያሉት ቁጥራቸው በጣም ተቀራራቢ / 37.6 % ና 36.3% በተከታታይ / ነው ። በሌሎቹ የማዳመጥ ችግሮች ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ችግር ነው ካሉት ይልቅ ዝቅተኛ በጣም ዝቅተኛ ችግር ነው ያሉት ተማሪዎች ቁጥር ይበ ልጣል ። የተማሪዎችን የማዳመጥ ችግር ለማስወገድ እንዲቻል የትምህርት ይዘት በሚመረጥበት ጊዜ የችግሩን ደረጃ መለያየት መሠረት በማድረግ የማዳመጥ ችግሮ ቻቸውን ከግምት ያስገባ ይዘት መምረጥ ይቻላል ።

...//77

4. በክፍል ውስጥ የሚቀርበውን የማዳመጥ ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ ተማሪዎቹ የሚያዳምጡትን ነገር መምህሩ በንባብ ወይም በንግግር ቢያቀርቡላቸው ይመርጣሉ ። "በካሴት ተቀድቶ ቢቀርብ እንመርጣለን" ያሉ ተማሪዎች ቁጥርም ከግምት የሚገባ ነው ። በመርሀ ትምህርቱ ላይ የቀረቡ የማዳመጥ ይዘቶች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑበት መንገድ በሚጠቀምበት ጊዜ የተማሪዎቹን ዝንባሌ ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል ።

5. በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር በቀጥታና በተዘዋዋሪ የቀረቡ ይዘቶች ለተማሪዎቹ በትምህርት ቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ ለማዳመጥ ምን ያህል እንደሚጠቅሟቸውና ክሂሉን የማዳበር ብቃታቸው ምን ያህል እንደሆነ ከተማሪዎችና ከመምህራኖቻቸው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በሁሉም ይዘቶች ተማሪዎቹ / ከ16–50.3 %/ በመካከለኛ ደረጃ፣ በከፍተኛ ደረጃና በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ያስፈልገናል ብለዋል ። ይዘቶቹ በዝቅተኛና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ያስፈልገናል ያሉት ከ2.6 – 11 % የሚደርሱ ናቸው ።

መምህራን ከ65–90 % ሁሉንም ይዘቶች በመካከለኛ ደረጃና ከዚያ በላይ ክሂሉን የማዳበር ብቃት እንዳላቸው ቢገልጹ፣ የመርሀ ትምህርት ባለሙያዎችም 66 % ና ከዚያ በላይ ይዘቶቹ በከፍተኛና በጣም በከፍተኛ ደረጃ ብቃት አላቸው ብለዋል ። የይዘቶቹ ብቃት ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ነው ያሉት መምህራን ከ5 %–25 % ይደርሳሉ ። ይህ ቁጥር ከግምት የሚገባ በመሆኑ የይዘቶቹን ብቃት መመርመሩ አስፈላጊ ነው ።

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች በመምህራንም ሆነ በመርሀ ትምህርት ባለሙያዎች የተሰጠው ምላሽ ክሂሉን የማዳበር ብቃት እንዳላቸው ቢያሳይም ፤ መምህራን ከ5 % – 25 % የይዘቶቹ ብቃት ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል፤ ከዚህም ጋር ተማሪዎቹ ከ2.6 – 11 % የሚደርሱ በትምህርት ቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ ለማዳመጥ በይዘቶቹ አንጻር የሚያዳብሩት የማዳመጥ ክሂል ጠቀሜታው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል ።

6. በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማዳበር የተረጡ ዝርዝር አላማዎች ምን ያህል የተማሪዎቻቸውን የማዳመጥ ፍላጎት እንደሚያሟሉ መምህራን በሰጡት ምላሽ ። ተጠየቃዊ አስተሳሰብን ማዳበር ። የሚለውን ዝርዝር አላማ 70 % በመካከለኛ ደረጃና ከዚ በላይ የተማሪዎቹን ፍላጎት ያሟላል ሲሉ፣ 30 % በዝቅተኛ ደረጃ ያሟላል ብለዋል፤ ። የተሰበሰበን ሃሣብ በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴ ። የሚለውን ዝርዝር አላማ 75 % በመካከለኛ ደረጃና ከዚ በላይ የተማሪዎቹን ፍላጎት ያሟላል ሲሉ ፣ 25 % በዝቅተኛና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ያሟላል ብለዋል ::በሁሉም ዝርዝር አላማዎች በመካከለኛ ደረጃና ከዚያ በላይ ፍላጐታቸውን ያሟላል ያሉት መምህራን ቁጥር በርካታ ቢሆንም በዝቅተኛና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ነው የተማሪዎቹን ፍላጎት የሚያሟላው ያሉት ቁጥርም / 30 % ና 25 % በቅደም ተከተል / ከግምት የሚገባ ነው ::

7. የተማሪዎቹን የማዳመጥ ችሎታ ለመለከት የተለያዩ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች እንደሚያመለክቱት :-

- በተማሪውና በመምህሩ መጠይቆች ላይ ተማሪዎች ከሚቀርብላቸው የማዳመጥ ጉዳይ ምን ያህሉን እንደሚያዳምጡ የሚያሳየው መረጃ አብዛኞቹ ተማሪዎች ከመካከለኛ ደረጃ በላይ ቢያዳምጡም ከመካከለኛ ደረጃ በታች የሚያዳምጡት ቁጥርም ከግምት የሚገባ ነው:: ስለዚህ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ለተማሪዎቹ የማዳመጥ ክሂሎቻቸውን የሚያዳብሩ ይዘቶችና ልምምዶች ሊቀርቡላቸው ይገባል ::

- አብዛኞቹ ተማሪዎች / 66.2 % / በቋንቋው በሚጠቀሙ ጊዜ አዳምጠ የመረዳት ችሎታቸው ከመካከለኛ ደረጃ በላይ ነው ሲሉ ፣ 66.6 % ደግሞ ከመካከለኛ ደረጃ በታች መሆኑን አመልክተዋል :: የቀረት /26.3 % / መካከለኛ የችሎታ ደረጃ እንዳላቸው ገልጸዋል፣ የኋለኛው መረጃ ክሂሉ በበቂ ሁኔታ አለመዳበሩንና ተጨማሪ የማዳመጥ ልምምዶች እንደሚያስፈልጉ ይጠቁማል ::

- በተማሪውና በመምህሩ መጠይቆች ላይ የተማሪዎችን አጠቃላይ የማዳመጥ ችሎታ ለመገመት ለቀረቡት ጥያቄዎች በተሰጠው ምላሽ መሠረት አብዛኞቹ ተማሪዎች በተለያዩ የማዳመጥ ንኡስን ክሂሎች ችሎታቸው መካከለኛና ከዛ በላይ ነው:: መምህራን ተማሪዎቻቸው 41.25 % መካከለኛ ፣ 29.25 %

ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ችሎታ አላቸው ሲሉ ፣ ተማሪዎች 25.4 % መካከ
ለኛ 58.30 % ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ ችሎታ አለን ብለዋል ::ከተማሪዎች
32.5 % ችሎታቸው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ሲገልጹ፣ ከመምህራን
29.25 % የተማሪዎቻቸው የማዳመጥ ችሎታ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን
ገልጸዋል :: በዚህ መሠረት የዚህ ክፍል ተማሪዎች የተለያዩ የማዳመጥ ንዑሳን
ክሂሎችን ያካተተ የትምህርት ይዘት ሊቀርብላቸው ይገባል ::

- በመምህሩ መጠይቅ ተማሪዎች የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች ምን ያህል እንደሚረዱ
ለቀረበው ጥያቄ ከመምህራን 80 % ተማሪዎቻቸው የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች
በመካከለኛ ደረጃና ከዚ በላይ እንደሚረዱ ገልጸዋል :: ተማሪዎቹ አብዛኛቹ አፋ
ቸውን የፈቱት በአማርኛ ስለሆነ የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጽ በመረዳት ረገዱ
ያለባቸው ችግር መጠነኛ ነው:: ከመምህራን 10 % ተማሪዎቻቸው በባህላዊ
አገላለጾች የሚረዱት በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ገልጸዋል :: ተማሪዎቹ በበኩላ
ቸው 53.6 % የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች ስለማወቅ በሚያዳምጡበት ጊዜ
ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች አንዱ መሆኑን ገልጸዋል ::

8. ተማሪዎች ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች በየትኛው የበለጠ እንደሚጠቀሙ በሰጡት ምላሽ
የማዳመጥን ክሂል አስመልክቶ አብዛኛቹ ተማሪዎች / 90.9 % / ክሂሉ በጣም
እንደሚጠቀሙባቸው ነው ያመለከቱት :: በዚህ መሠረት የማዳመጥ ክሂሉ ለተማሪው
ከሚሰጠው ከፍተኛ ጠቀሜታ አንጻር በበቂ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳበር
ይገባል :: መምህራን ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መሀከል ለዚህ ክፍል ተማሪዎች
ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩት የትኛውን ክሂል እንደሆነ ሲያመለከቱ 70%.
የማዳመጥን ክሂል በ1ኛ ደረጃ ትኩረት እንሰጣለን:: ለዚህም ከሰጧቸው ምክን
ያቶች ውስጥ የተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል በሚገባ ባለመዳበሩ፣ የማዳመጥ ክሂላ
ቸው ካልዳበረ በሌሎች ክሂሎች የመጠቀም ችሎታቸው የተሟላ ስለማይሆን የሚሉ
ይገኙበታል:: ለማዳመጥ ክሂሉ በሦስተኛና በአራተኛ ደረጃ ነው ትኩረት
የምንሰጠው ያሉ መምህራን /25%/ ካቀረቧቸው ምክንያቶች ውስጥ በመለመኛ
የቀረቡ የማዳመጥ ልምምዶች እጅግ አነስተኛ በመሆኑ፣ የማዳመጥ አይሉ በፊ
ስለሆነ ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ ላይ ስለሚገኙ የሚሉ ይገኙበታል::

የመርሀ ትምህርት ባለሙያዎች ለዘጠነኛ ክፍል በሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ከአራት የቋንቋ ክሂሎች መሀከል 66.6 % በአንደኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ሲሉ ለዚህም የሰጡት ምክንያት የቋንቋ አካባቢያዊ መሠረቱ ማዳመጥ ነው ፣ በተግባራዊ እንቅስቃሴ በይበልጥ የሚሰራበት ንግግር በመሆኑ የማዳመጥ ክሂል ከዳበረ አያሌ ተግባሮችን ማከናወን ይቻላል የሚል ነው ። 33 % ማዳመጥ ከአራቱ ክሂሎች መሀከል በሶስተኛ ደረጃ ሊተኮርበት ይገባል ሲሉ ለዚህም የሰጡት ምክንያት የቋንቋ ክፍል በመሆኑ በዚህ ደረጃ ተማሪው በአብዛኛው አራሱ መናገርና መጻፍ አለበት የሚል ነው ።

ከተማሪዎች ፣ ከመምህራንና ከመርሀ ትምህርት ባለሙያዎች የተገኘው መረጃ በአብዛኙ የማዳመጥ ክሂል ለዚህ ክፍል ተማሪዎች በጣም ጠቃሚ እንደሆነና ከሌሎቹ ክሂሎች በበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳብር እንደሚገባ ያመለክታል ።

9. ተማሪዎች ማዳመጥ የሚወዱት እንዴት ያሉ ጉዳዮችን እንደሆነ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከቀረቡላቸው ምርጫዎች፡- ስለሀገር ስለትምህርት፣ ስለፍቅር፣ ስለጀግንነት፣ ስለጤና፣ ሣይንስ ነክ፣ ስለፖለቲካ፣ ስለ ኢኮኖሚ፣ ስለቤተሰብ ከሚሉ ርእሶች መሀከል ፖለቲካን በጣም ዝቅተኛ ምርጫቸው ነው ያሉ 53.6% ሲሆኑ ሌሎቹን ርእሶች ከ31.6 % – 69 % የሚሆኑት በጣም በከፍተኛ ደረጃ መርጠዋል ። ዝርዝር መረጃውን በማየትና የተማሪዎችን ዝንባሌ በማወቅ ለማዳመጥ ትምህርት በሚቀርቡላቸው ይዘቶች ውስጥ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ከዝንባሌያቸው ጋር የሚስማማ ማድረግ ይቻላል ።

10. መምህራን ተማሪዎቻቸውን በአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂሎቻቸውን ማዳበራቸው ሌሎች ትምህርቶችን ለመከታተል ምን ያህል እንደሚጠቅማቸው ሲገልጹ፣ ቀጥር ነክ ለሆኑና ለማይገበ ትምህርቶች ጠቀሜታው ዝቅተኛ ነው ሲሉ ፣ ለሌሎቹ በአብዛኛው በቃላት ገለጻ ማድረግን ለሚፈልጉ ትምህርቶች በመካከለኛ ደረጃና ከዚያ በላይ ጥቅም ይሰጣል ብለዋል ። ከዚህም ጋር የዚህ ክፍል ተማሪዎች የእርሻና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርቶችን በአማርኛ ቋንቋ እንደሚማሩ ይታወቃል ።

## ምዕራፍ 5:- ማጠቃለያና ጥቆማ

### 5.1 ማጠቃለያ

ማዳመጥ በኅብረተሰቡ ውስጥ በቋንቋ ለመግባባትም ሆነ በትምህርት መስክ ከፍተኛ ድርሻ አለው ። ስለዚህ የማዳመጥ ክሂል በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳበር ይገባል ። በተፈጥሮ የሚገኘው የማዳመጥ - ችሎታ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥና የተለያዩ ጉዳዮችን ለማዳመጥ ብቻውን በቂ አይሆንም ። በአፍ መፍቻ ቋንቋም እንኳ ቢሆን አዳምጦ የመረዳት ችሎታ መቶ ፐርሰንት መድረስ እንደማይችል ምሁራን ይናገራሉ ። ነገር ግን ሆን ተብሎ ክሂሉን ለማዳበር በሚቀርቡ ልምምዶች አማካይነት የማዳመጥን ክሂል ከተፈለገው ደረጃ ለማድረስ ይቻላል ።

ማዳመጥ በትምህርትም ሆነ በሥራ መስክ እንዲሁም በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ካለው ከፍተኛ ድርሻ አንጻር እንደሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ራሱን ችሎ በተናጠልና እንዲሁም ከሌሎቹ ክሂሎች ጋር ተዳብሎ አላማ ተነድፎለትና ይዘት ተመርጦለት ሊዳበር የሚገባው ክሂል ነው ። የማዳመጥን ክሂል ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አዋህዶ በማቅረብ ለማዳበር ቢቻልም ትኩረት ለመስጠት ሲባል በአላማና በይዘት ደረጃ ራሱን ችሎ መቅረቡ የተሻለ ይሆናል ።

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠውና ክሂሉን ያዳብራሉ ተብለው የተመረጡትን ይዘቶች ብቃት በተመለከትንበት ወቅት ከሚከተሉት የማጠቃለያ ነጥቦች ላይ ለመድረስ ተችሏል ።

1. የማዳመጥ ክሂል በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በአጠቃላይ አላማ፣ በዝርዝር አላማና በይዘት ደረጃ ከመናገር ክሂል ጋር ተዳብሎ ቀርቧል፣ ከዚህም ጋር ይዘቶቹ ግልጽ ባለመሆኑና አሻሚ በሆነ መንገድ ስለተጻፉ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ተንተርሶ ለሚያስተምር የቋንቋ መምህር ወይም የመማሪያ መጽሀፍ አዘጋጅ በየትኛው ክሂል ላይ ማተኮር እንደሚገባው በትክክል አያመለክትም ።

...//82

2. የማዳመጥ ክሂል ከመናገር ክሂል ጋር ተደብሎ በቀረበበት ሁኔታም ለሁለቱም ክሂሎች በአንድነት የቀረቡት ይዘቶች ብዛት ለሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ከቀረቡት ይዘቶች ብዛት ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው ። በአጠቃላይ በዚህ ክፍል የማዳመጥ ክሂል በቂ ትኩረት አላገኘም ።

በተማሪዎች የፍላጐት አሰሳ ጥናት ላይ ከተማሪው ፣ ከመምህሩና ከመርሀ ትምህርቱ ባለሙያው መጠይቆች የተገኘው መረጃ ለዚህ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል መዳበር በጣም አስፈላጊ መሆኑንና ከሌሎቹ ክሂሎች የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያሳያል ። በዚህ መሠረት በመርሀ ትምህርቱ ላይ የቀረቡት ይዘቶች ብዛት ከተማሪዎቹ ፍላጐት ጋር የሚመጣጠን አይደለም ። በጣም አነስተኛ ናቸው ።

3. በየሴሚስተሩ ተመጣጣኝ አቀርቦት አይታይም ፤ በአንደኛው ሴሚስተር ስድስት ይዘቶች ሲቀርቡ በሁለተኛው ሴሚስተር አንድ ይዘት ብቻ ተመርጦ ቀርቧል ።

4. የክብደት ደረጃቸውን በተመለከተ በአንደኛውና በሁለተኛው ይዘቶች ከቀረቡት ልምምዶች ይልቅ በስድስተኛው ይዘት የቀረበው በጣም ቀላል ነው ። በአንደኛው ሴሚስተር የቀረቡ ልምምዶች በሁለተኛው ሴሚስተር ከቀረበው የከበዱ ናቸው ። በይዘቶቹ አንጻር የቀረቡት ልምምዶች የክብደት ደረጃቸውን ያልጠበቁ ከቀላል ወደ ከባድ ሳያድጉ የማይሄዱ ልምምዶች ናቸው ።

5. በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ይዘቶቹ ግልጽነት በጐደለው ሁኔታ ቢጻፉም አንዳንዱ የማዳመጥ ዋና ንዑሳን ክሂሎችን ለማዳበር ሞክረዋል ። በዚህም በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማዳመጥ ትምህርት ይበልጥ ሊተኮርባቸው በሚገቡ ይዘት አይነቶች ማለትም ለመረጃ መሻት ማዳመጥ ላይ በይበልጥ አተኩረዋል ። በተማሪው መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት የተማሪዎቹ አፍ መፍቻ ቋንቋ የአብዛኛዎቹ / 92.6 % / አማርኛ መሆኑ አይዘነጋም ።

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ገና ከመግቢያው እንደሚጠቁመው መርሀ ትምህርቱ ሲዘጋጅ መሠረት ያደረገው "በተወሰነ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ምን ሊማሩ ይገባቸዋል ?" የሚለውን ጥያቄ ነው ። በመሠረቱ የቋንቋ መርሀ ትምህርት ሲዘጋጅ መሠረት ማድረግ ያለበት የኅብረተሰቡን በተለይም የተማሪውን የቋንቋ ፍላጎት ነው ። "ተማሪው ቋንቋውን የሚማረው በቋንቋው ምን ለማድረግ ነው ?" "በኅብረተሰቡ ውስጥ ቋንቋው የሚኖረው ሚና ምንድነው ?" "ቋንቋውን ለመማር ምን ማድረግ አለባቸው ? የሚሉትን ጥያቄዎች ይዞ ለነዚህ ጥያቄዎች ከሚሰጡ ምላሾች አኳያ ተስማሚው መርሀ ትምህርት ይዘጋጃል ። በመርሀ ትምህርት ዝግጅት ውስጥ ዋነኛው ጉዳይ ይዘት እንደሆነ የቋንቋው ትምህርት ምሁራን ይናገራሉ ። ለትምህርት የሚቀርበው ይዘት ሲመረጥ ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥናት ማድረግን ይጠይቃል ። በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶችን በመምረጥ ረገድ የተማሪው ዕድሜ፣ ፍላጎቱና ችሎታው ፣ ቋንቋውን የሚማርበት አላማ ሊተኮርባቸው የሚገባ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው ። በዚህ አንጻር የዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ሲዘጋጅ የተደረገ ጥናት ስለመኖሩ የሚጠቁም ነገር የለም ። እንዲያውም በመርሀ ትምህርቱ መግቢያ ላይ መርሀ ትምህርቱ በጥናት ላይ ያልተመሠረተ መሆኑን ይገልጻል ።

የቋንቋ መርሀ ትምህርት ሲዘጋጅ ከሁሉም በላይ የይዘት ምርጫ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥናት ሊደረግ እንደሚገባ ከላይ ተገልጿል ። በሚደረገው ጥናት ውስጥም የተማሪዎችን ፍላጎት ና ችሎታ ማጥናት አንዱ ነው ። በዘጠነኛ መርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ያለጥናት የተመረጡ መሆናቸው በመርሀ ትምህርቱ ላይ ተገልጿል ። ያለ ጥናት የቀረቡ ይዘቶች ደግሞ የተማሪውን ፍላጎት ምን ያህል ሊያሟሉ እንደሚችሉ በውሉ መገመት አያዳግትም ።

የማዳመጥን ክሂል በተመለከተ ክሂሉን በትምህርት ቤት የማስተማር አላማ ተማሪው የሚሰማውን ነገር የመረዳት የመተርጎም፣ የመገምገምና የራሱን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችለውን ክሂል ለማበልጸግ፣ በማዳመጥ ችሎታው እንዲተማመንና በኅብረተሰቡ ውስጥ ማዳመጥን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀም ለማስቻል በልዩ ልዩ የማዳመጥ አውዶችና የማዳመጥ አይነቶች ተግባራዊ ልምምድ መስጠት ነው ። በዚህም መሠረት የማዳመጥ ልምምዶች ሲዘጋጁ ተማሪዎች ሊጠቀ

ሙያቸውና ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ የማዳመጥ ሁኔታዎችንና ችግሮችን ከግምት ያስገቡ መሆን ይኖርባቸዋል :: በዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ግን በጥናት ላይ ያልተመሠረቱ በመሆናቸው የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ፣ ለማዳመጥ የሚፈልጉትን ርእስ ጉዳዮች፣ የሚዳመጥ ነገር የአቀራረብ ዝንባሌያቸውን፣ ማዳመጥ በተማሪዎች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለውና በርካታ ልምምዶች እንደሚያስፈልጉ፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ከግምት ያላስገባ ዝግጅት ነው ::

የተማሪዎችን ፍላጎትና ችሎታ እንዲሁም የቋንቋ አጠቃቀም ከማዳመጥ ክሂል አንጻር ለማጥናት የተደረገው ሙከራ ውጤት እንደሚያሳየው በዘጠነኛ ክፍል የምናገኛቸው ተማሪዎች አብዛኞቹ አማርኛ አፍ መፍቻቸው የሆኑ ናቸው :: ቋንቋውን ከሚማሩበት አላማቸው አንዱ አዳምጠ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ሲሆን አብዛኞቹ ተማሪዎች የማዳመጥ ችሎታቸው መካከለኛና ከዚ በላይ ቢሆንም ችሎታቸው ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎች ቁጥርም ከግምት የሚገባ ነው :: የመጠይቆቹ ምላሽ የተማሪዎችን ፍላጎት ችሎታና የቋንቋ አጠቃቀም በተመለከተ በርካታ ዝርዝር ሁኔታዎችን አመልክቷል ::ይህንንም "የመጠይቆች ምላሽ ትንተናና ንጽጽር "ከሚለው ክፍል / ገጽ 63 —67 / መመልከት ይቻላል :: በአጠቃላይ ግን ለዚህ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል በትምህርትቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ በጣም ጠቃሚ እንደሆነና ከሌሎቹ ክሂሎች በበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳበር እንደሚገባ ከመጠይቆቹ የተገኘው ምላሽ ያመለክታል :: በለዚህ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል የሚያዳብሩ በርካታ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከተማሪው ፍላጎት አንጻር ተመርጠው ለተማሪዎቹ የሚያስፈልጋቸውን የማዳመጥን አጠቃላይና ንኡሳን ክሂሎች በግልጽና በዝርዝር ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል ::

5.2:- ጥቆማ፤

በዚህ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር በቀረቡ ይዘቶች ላይ በተደረገ ጥናት በተገኘው ውጤት መሠረት የሚከተሉት የጥቆማ ነጥቦች ቀርበዋል ። :-

1. የማዳመጥን ክሂል መቶ ፐርሰንት ማድረስ ባይቻልም በማስተማር ክሂሉን ለተፈለገው አላማ ማዳበር እንደሚቻልና ይህም ደግሞ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማዳመጥንም የሚመለከት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።
2. የማዳመጥ ክሂል በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን ላይ ከሌሎቹ ክሂሎች ጋር ተዋህዶ ቢገኝም በአላማና በይዘት ምርጫ ደረጃ ግን በተናጠል ቢቀርብ ክሂሉን ትኩረት ሰጥቶ ለማዳበር ያስችላል ።
3. ይዘቶቹ ሲጻፉ ሊዳብር የተፈለገውን ክሂል ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያሳዩ ሆነው መጻፍ አለባቸው ። ትርጉማቸው አሻሚ በሆነ መንገድ ከተጻፉ ከተፈለገው ግብ ማድረሳቸው አጠራጣሪ ነው ።
4. ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥን ክሂል የሚያዳብሩ በርካታ ይዘቶች ሊቀርቡላቸው ይገባል ። ከፍላጎት አሰሳው የተገኘው ውጤት ይህንኑ ያመለክታል ።
5. የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከመመረጣቸው በፊት የተማሪዎችን ፍላጎት ማጥናት አስፈላጊ ነው ። ይህንንም ተማሪዎችን፤ መምህራንና የመርሀ ትምህርት አዘጋጆችን መጠይቆችን በማስሞላት ማከናወን ይቻላል ። ማንኛውም ትምህርት በአንዱ አይነት ፍላጎት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የፍላጎት አሰሳ የማድረጉ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም ።
6. የመርሀ ትምህርት አዘጋጆች ከተማሪዎችና ከቋንቋ መምህራን ጋር በመተባበርና በመቀራረብ መሥራት አለባቸው ። የትምህርቱን ይዘት በተመለከተ በየጊዜው ከመምህራንም ሆነ ከተማሪዎች አስተያየት መሰብሰብ ተገቢውን ይዘት ለመምረጥ ይረዳል ።
7. መርሀ ትምህርት በየጊዜው ለግምገማ መቅረብና የግምገማ ሃሳቦችን ሰብስቦና በየጊዜው የሚፈልቁ አዳዲስ የቋንቋና ቋንቋን የማስተማር ቲዮሪዎችን ተንተርሶ መሻሻልና መለወጥ የሚችል ሆኖ መቅረብ አለበት ።

# የዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር

Allen, J.P.B., 1984. "General Purpose language Teaching : A Variable focus Approach", General English Syllabus Design. ELT Documents 118. C.J. Brumfit (edt). Oxford : pergomon press Ltd. (pp.61-74.)

Anderson, A., and Tony L. 1988. Listening. Oxford: Oxford University Press.

Bhatia, Aban Tavadia. 1986. "Communicative Language Skills and ESP" ESP in Practices. Models and challenges for teachers. Peterson, pat Wilcox (edt.) English Language programs Division Bureau of Educational and Cultural Affairs United States Information Agency Washington, D.C. (pp. 10-15).

Borg, Walter R., and M. D, Gall. 1989. Educational Research: An Introduction. London: Longman Group UK Limited.

Brown, G., and J.Yule. 1983 Teaching the Spoken Language. Cambridge: Cambridge University Press.

Byrne, Donn. 1986. Teaching Oral English. London: Longman Group UK. Limited.

Dubin, Fraida and Elite Olshtain. 1986. Course Design: Developing Programs and Materials for Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Harmer, Jeremy. 1983 The Practice of English Language Teaching. London; Longman Group UK Limited.

Hutchinson, Tom, and Alan Waters. 1987 English for Specific Purpose: A Learning Centered Approach. Cambridge; Cambridge University Press.

Lewis, Michael and Jimmie Hill. 1986. Practical Techniques for Language Teaching. London: Biddles Ltd.

Littlewood, William. 1981. Communicative Language Techniques for Language Teaching. London: Biddles Ltd.

Munby, John. 1978. Communicative Syllabus Design. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J.C. 1990. The Language Teaching Matrix Cambridge: Cambridge University Press.

R[illegible]on, Shelagh. 1986 **Developing Listening Skills.** London: Mac millan Publishers Ltd.

Rost, Michael. 1990. Listening in Language Teaching. London: Longman Group UK Limited.

Stern, H.H. 1984 " Review and Discussion " General English Syllabus Design. ELT Documents 118. C.J. Brumfit (edt). Oxford: Pergamon Press Ltd. (pp. 5 - 12 ).

Tarone, Elanie, and George Yule. 1989. Focus on The Language Learner. Oxford University Press.

Tesfaye Shewaye, and Charles V. Taylor. 1976. " Language Curricula ", Language in Ethioia M.L. Bender, and others ( edts.) London: Oxford University Press. (pp. 371-399).

Tyler, Ralph. W. 1949. Basic Principles of Curriculum and Instruction. Chicago" The University of Chicago Press.

Underwood, Mary. 1989. Teaching Listening. London: Longman Group UK Limited.

Ur, Penny. 1984. Teaching Listening Comprehension. Cambridge: Cambridge University Press.

White, R.V. 1988. The ELT Curriculum. Cambridge: Basil Blackwell Inc.

Widdowwon, H.G. 1990. Aspects of Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Yalden, Janice. 1987. Principles of Course Design for Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

ስለሞን ደስታ፣ 1976፣ በአዲስ አበባ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ1975 ዓ/ም የተሰጡ የአማርኛ ፈተናዎች ግምገማ:: ለቢኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ሰለሞን ገዛው ፤ 1978፤ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍት ግምገማ / ከ1966–1976/፤ ለቢኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ::

በበርስተ ትምህርት ሱፐርቪዥን መምሪያ የአማርኛ ትምህርት ቡድን፤ የአማርኛ ቋንቋ ስርአተ ትምህርት /ከ1–8 ክፍል / ፤ የተባዘ/ ::

ተሰፋዬ ሽዋዬ፤ 1982 ፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን የማስተማሪያ አላማዎች ትንታኔ፤ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ሲምፖዚየም የቀረበ :: / የተባዘ/ ::

ትምህርት ሚኒስቴር፤ 1984 ፤ የአማርኛ መማሪያ ዘጠነኛ ክፍል ፤ ትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ::

____________፤ 1984 ፤ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰው፤ ዘጠነኛ ክፍል፤ ትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ::

ይልማ ከበደና አሸቶ ከበደ ፤1982 ፤ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ስርአተ ትምህርት የአሁኑና ወደፊት መሆን የሚገባው፤ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ሲምፖዚየም የቀረበ :: / የተባዘ/ ::

ደመቀ ብርሃኑ ፤ 1973 ፤ የሁለተኛ ደረጃ መለቀቂያ የአማርኛ ፈተናና የስርአተ ትምህርት/ ከ1969 – 1972 / ፤ ለቢኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፤ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ፈቃደ አዘዘ ፤ 1982 ፤ አንዳንድ ነጥቦች ስለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች፤ ስለስርአተ ትምህርቶች፤ ስለመማሪያ መጽሀፍት እና ስለ ሥነጽሁፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት /1940 – 1982 / ፤ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ሲምፖዚየም የቀረበ :: / የተባዘ ::

# አባሪዎች

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አባሪ 1

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

### የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት/ሲለበስ/ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ለመገምገምና ለመተንተን የተዘጋጀ መጠይቅ::

**መግቢያ፤** **የተማሪው መጠይቅ**

የዚህ መጠይቅ አላማ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ተገቢነትና ብቃት ለመመርመር ለሚደረገው ጥናት የሚያገዝ መረጃ መሰብሰብ ነው::ጥናቱ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘትን በመምረጥና በመወሰን ሂደት ሊከተሏቸው የሚገቡ ደረጃዎችንና ሊዘርጓቸው የሚገቡ ነጥቦችን በማመልከት ረገድ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይገመታል::

ይህ አላማ ከግቡ ሊደርስ የሚችለው የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት ተማሪዎች በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ በሥራ መስክና በኅብረተሰቡ ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ምን ያህል እንደሚጠቀሙና በቋንቋው ያላቸውን የማዳመጥ ችሎታ በመግለጽ በዚህ ጥናት ሲሳተፉ ነው:: ስለዚህ አንተም በዚህ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና ካነበብህ በኋላ የምትስማማበትን መልስ በመስጠት እንድትተባበር አንጠይቃለ:: ስለትብብርህ በቅድሚያ እናመሰግናለን::

**ማስታወሻ፤**

- በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አስፈላጊ አይደለም
- የቀረቡት ጥያቄዎች በሙሉ በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀምና ችሎታ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ተገንዝበህ የምትሰጣቸው መልሶችም የአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀምህን በትክክል የሚያሳዩ መሆን እንደሚገባቸው አስተውል::
- በተባእት ጾታ መጠቀሙ የተለመደ በመሆኑና በመጠይቁ ላይ የሚያመጣው ለውጥ እንደሌለ በማመን፤ በሁለቱም ጾታዎች ለመግለጽ መሞከሩ ለተዛባ እንዳያስቸግር በማለት ጥያቄዎቹ በተባእት ጾታ ብቻ ቀርበዋል::

1. **ግላዊ መረጃ**

የትምህርት ቤት ስም ______________________

የአፍ መፍቻ ቋንቋህ ______________________

ከአፍ መፍቻ ቋንቋህ ሌላ የምትችላቸው ቋንቋዎች ____________

____________

____________

ፆታ:- ወንድ [ ] ሴት [ ]

ዕድሜ:- 13 ዓመት ወይም በታች [ ]

ከ14-16 ዓመት [ ]

ከ17-19 ዓመት [ ]

20 ዓመት ወይም በላይ [ ]

ፕፕ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምርጫ ላላቸው ከተሰጡት ምርጫዎች የምትስማማበትንመልስ የያዘው ፊደል ወይም ቁጥር በመክበብ ወይም ተስማሚውን ቁጥር በመጻፍ መልስ :: ምርጫ ለሌላቸው ጥያቄዎች ደግሞ በተወሰኑ አረፍተ ነገሮች መልስህን በመጻፍ መልስ::

1. የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች አማርኛ የምትማርበትን አላማህን የሚገልጹትን ደረጃ አመልከት:-

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ
0 = በፍጹም አይገልጹም

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1.1. በቋንቋው ሌሎች ትምሀርቶችንመማር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.2. በቋንቋው የመናገር ችሎታዬን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.3. በቋንቋው የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ጉዳዮችን አዳምጦ የመረዳት ችሎታዬን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.4. በቋንቋው የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ጽሁፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.5. ልዩ ልዩ ዓይነት ጽሁፎችን የመጻፍ ችሎታን ማዳበር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.6. ቋንቋውን መማር ግዴታ ስለሆነ ብቻ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1.7. ፈተና ለማለፍ ስል ብቻ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

2. የሚከተሉትን የማዳመጥ ተግባራት ምን ያህል ታዘወትራለህ?

4 = ሁሉጊዜ
3 = ብዙ ጊዜ
2 = በመጠኑ
1 = አንዳንድ ጊዜ
0 = በፍጹም

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1. | በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሚተላለፍ ፕሮግራሞችን ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.2. | በክፍል ውስጥ መምህሩ የሚናገሩትን የፈተና ዎችን ወይም የመለመጃ ዎችን የአሠራር መመሪያዎች ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.3. | በአማርኛ ቋንቋ የሚሰጡ የሌሎች ትምህርቶችን ገለጻ ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.4. | በስልክ የሚተላለፍ መልእክትን ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.5. | ውይይቶችን ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.6. | የሌሎችን ጭውውት ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.7. | በድምፅ ማጉያ የሚነገሩ ማስታወቂያዎችን ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 2.8. | በቃል የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ማዳመጥ | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |

3. በክፍል ውስጥ የምታዳምጠው ጉዳይ እንዴት ቢቀርብልህ ትመርጣለህ?

ሀ. መምህሩ ቢያነቡት ወይም ቢናገሩት
ለ. ከተማሪዎች አንዱ ቢያነበው ወይም ቢናገረው
ሐ. በካሴት ተቀድቶ ቢቀርብ

4. የሚከተሉት የሌሎችን ንግግር በምታዳምጥበት ጊዜ ሃሳባቸውን በቀላሉ እንዳትረዳ የሚያደርጉ ችግሮች ናቸው ተብሎ ይገመታል:: ላንተ ችግር የሚሆኑበት ደረጃ ምን ያህል ነው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

4.1. የንግግሯን ይዘት/የመስማማት፣የጥያቄ፣ የቁጣ፣ የትዕዛዝ፣ ወዘተ. መሆኑን/ ለይቶ አለማወቅ 5 4 3 2 1

4.2. በቋንቋው ውስጥ የሚሹና የሚጠብቁ ይዘቶችን ለይቶ አለማወቅ 5 4 3 2 1

4.3. የቋንቋውን ባለቤቶች ባህል አለማወቅ 5 4 3 2 1

4.4. የተናጋሪውን ስሜት አለመረዳት 5 4 3 2 1

4.5. ፍሬ ነገሩን ለይቶ ማዳመጥ አለመቻል 55 4 3 2 1

5. በትምህርት ቤትም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚነገረውን ለማዳመጥ የሚከተሉት የቋንቋ ችሎታዎች ለአንተ አስፈላጊ የሚሆኑት ደረጃ ምን ያህል ነው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

5.1. የቃላትን ቀጥተኛ ትርጉም ማወቅ 5 4 3 2 1

5.2. የቃላትን፣ የሀረግና የአረፍተ ነገርን ትርጉም ከአገባብ መረዳት 5 4 3 2 1

5.3. በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት 5 4 3 2 1

5.4. የውይይት ስርአት ማወቅ 5 4 3 2 1

5.5. የክርክር ስርአት ማወቅ 5 4 3 2 1

5.6. የጭውውት ስርአት ማወቅ 5 4 3 2 1

5.7. ምስጢራዊ አነጋገሮች መገንዘብ፣ መተርጎምና በነርሱም መገልገል/ምሣሌ:— ቅኔ፣ዘይቤ፣ወዘተ/ 5 4 3 2 1

5.8. የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነትን ማወቅ 5 4 3 2 1

5.9. የሚያስፈልጉና የማያስፈልጉ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት 5 4 3 2 1

5.10. በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መሀከል ያለውን ልዩነት ማወቅ 5 4 3 2 1

5.11. ፍሬ ሃሳቦችን በማስታወሻ መያዝ 5 4 3 2 1

5.12. አንዱን ርዕስ ጉዳይ አዳምጦ በራስ አባባል ማቅረብ 5 4 3 2 1

6. ከምታዳምጠው ውስጥ ምን ያህሉን በእርግጠኝነት ታዳምጣለህ?

ሀ. ከ20% በታች
ለ. ከ21–40%
ሐ. ከ41–60%
መ. ከ61–80%
ሠ. ከ80%በላይ

7. በአማርኛ ቋንቋ በምትጠቀምበት ጊዜ በሚከተሉት ክሂሎች ችሎታህ የቱን ያህል ነው?

5= በጣም ከፍተኛ
4= ከፍተኛ
3= መካከለኛ
2= ዝቅተኛ
1= በጣም ዝቅተኛ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7.1. | በተለያዩ ሰዎች ስለተለያየ ጉዳይ የሚደረጉ ንግግሮችን አዳምጦ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 7.2. | በተለያዩ ርዕሶች ላይ ሃሳብ አሰባስቦ ንግግር ማድረግ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 7.3. | በተለያዩ ርዕሶች ለተለያየ አላማ የተጻፉትን አንብቦ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 7.4. | በተለያዩ ርዕሶች የድርሰት አጻጻፍ ስርአትን ተከትሎ መጻፍ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

8. በአማርኛ ቋንቋ በምትጠቀምበት ጊዜ የሚከተሉት ክሂሎች ለአንተ ጠቀሜታቸው ምን ያህል ነው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ
0 = ምንም

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8.1 | ማዳመጥ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.2 | መናገር | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.3 | ማንበብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.4 | መጻፍ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

9. እዚህ ክፍል ከምትማራቸው የትምህርት ዓይነቶች የማስተማሪያ ቋንቋቸው አማርኛ የሆኑ ትምህርቶችን ጻፍ:— ______________________

______________________________________________

10. በአማርኛ ቋንቋ ከፍለ ጊዜ ማዳመጥ የምትፈልገው የምንባብ ወይም የንግግር ርዕስ ስለምን የሚናገር ቢሆን ይሻላል? የምርጫ ደረጃህን አመልክት

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

| | | |
|---|---|---|
| 10.1 | ስለሀገር | 5 4 3 2 1 |
| 10.2 | ስለ ትምህርት | 5 4 3 2 1 |
| 10.3 | ስለ ፍቅር | 5 4 3 2 1 |
| 10.4 | ስለ ጓደኝነት | 5 4 3 2 1 |
| 10.5 | ስለ ጤና | 5 4 3 2 1 |
| 10.6 | ሣይንስ ነክ | 5 4 3 2 1 |
| 10.7 | ስለ ፖለቲካ | 5 4 3 2 1 |
| 10.8 | ስለ ሃይማኖት | 5 4 3 2 1 |
| 10.9 | ስለ ቤተሰብ | 5 4 3 2 1 |

10.10 ሌሎች እዚህ ያልተጠቀሱ ካሉ ግለጽ:-____________________

________________________________________

11. ከዚህ በታች የማዳመጥ ችሎታን የሚያመለክቱ አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል:: ከተሰጡት አምስት የችሎታ ደረጃዎች የአንተን ችሎታ የሚገልጸውን የአንቅን ቁጥር በመከበብ ችሎታህን አመልክት:: ጥያቄዎቹ ፈተና ስላልሆኑ ችሎታህን በትክክል ለመግለጽ ሞክር::

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

11.1 የማታውቃቸውን ቃላትና ሀረጎች ትርጉም ከአገባባቸው የመረዳት ችሎታ 5 4 3 2 1

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11.2. | በቃል የሚነገሩህን መመሪያዎች በቀላሉ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.3. | በንባብ ወይም በንግግር ቀርቦ ከምታዳምጠው ውስጥ ዋናውንና ዝርዝር ሃሣቡን ለይተህ የመረዳት ችሎታ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.4. | በተለያዩ ሰዋሰዋዊ ቅንብር የሚቀርብልህን ሃሣብ አዳምጠህ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.5. | በመደበኛና በኢ-መደበኛ ንግግር መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.6. | በግራፍ፣ በሠንጠረዥ ወይም በካርታ የተደገፉ መረጃዎችን አዳምጦ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.7. | ከምታዳምጠው ውስጥ ምክንያትንና ውጤትን ለይተህ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.8. | የንግግር ዷንዷን ባህሪ ማወቅ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.9. | የንግግሩን ዓይነት/የጥያቄ፣ የመገረም የመስማማት፣ የመቃወም፣ወዘተ መሆኑን/ አዳምጠህ መለየት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.10. | የምታዳምጠውን ነገር አስቀድሞ ከምታውቀው ነገር ጋር ማገናዘብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.11. | በግልጽ የተነገሩ መረጃዎችን አዳምጠህ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.12. | በንግግር ውስጥ በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.13. | በንግግር ውስጥ ተናጋሪው የሚያተኩርባቸውን ነጥቦችና የንግግሩን አላማ ለይተህ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.14. | ተናጋሪው በንግግሩ ወቅት ሃሣብ ለማስተዋወቅ ሃሣብ ለማዳበር፣ ከአንዱ ሃሣብ ወደሌላ ሃሣብ ለመሸጋገርና ሃሣቡን ለማጠቃለል የሚጠቀምባቸውን ነጥቦች ለይተህ መገንዘብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.15. | ከሚነገረው ውስጥ ጠቃሚውን መረጃ ለይተህ ማዳመጥ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 11.16. ከምታዳምጠው ውስጥ የማይጠቅሙ መረጃዎችንና ድግግሞሽን በመለየት አሳጥረህ ማቅረብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.17. በንግግር የቀረበለህን መረጃ ወደ ግራፍ፣ ሠንጠረዥ ወይም ካርታ መተርጐም | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.18. ያዳመጥከውን በራስህ አባባል ማቅረብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.19. በምታዳምጠው ቲያትር ንግግር ወይም ምንባብ ውስጥ ወደፊት የሚነገረውን አስቀድመህ የመገመት ችሎታ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11.20. ከምታዳምጠው ውስጥ ፍሬ ሃሳቡን በማስ ታወሻ የመያዝ ችሎታ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

..

አባሪ 2

~~አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ~~

<u>የድሀረ ምረቃ ትምሀርት ቤት</u>

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መረሀ ትምሀርት/ሲለበስ/ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ለመገምገምና ለመተንተን የተዘጋጀ መጠይቅ::

## የመምሀሩ መጠይቅ

### መግቢያ

የዚህ መጠይቅ አላማ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መረሀ ትምሀርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ተገቢነትና ብቃት ለመመርመር ለሚደረገው ጥናት የሚያገዝ መረጃ መሰብሰብ ነው:: ጥናቱ የአማርኛ ቋንቋ ትምሀርት ይዘትን በመምረጥና በመወሰን ሂደት ሊከተሏቸው የሚገቡ ደረጃዎችንና ሊዙርባቸው የሚገቡ ነጥቦችን በሚመለከት ረገድ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ይገመታል::

የጥናቱ አላማ ግቡን ሊመታ የሚችለው የቋንቋው መምሀራን በክፍል ውስጥ ቋንቋን በማስተማር ተግባር ላይእያሉና በኅብረተሰቡ ውስጥ ያስተዋሏቸውን የተማሪዎቻቸውን የቋንቋ ፍላጎትና/      / ችሎታ በመግለጽና ከሙያቸው አንጻር የትምሀርቱ ይዘት ምን መልክ ሊኖረው እንደሚገባ ሃሳባቸውን በመሰንዘር ቀና ትብብር ሲያደርጉ እንደሆነ ይታመናል::

ስለዚህ እርስዎም በዚህ መጠይቅ ላይ የሚሰነዝሩት አስተያየትና ለጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በመገንዘብ መጠይቁን በመሙላት እንዲተባበሩ በትሀትና እንጠይቃለን:: ስለትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን::

### ፩. ደራዊ መረጃ

የሚያስተምሩበት ት/ቤት ______________፣ የሚያስተምሩባቸው ክፍሎች ____
እና መፍቻ ቋንቋ __________________፣ ዕድሜ ____፣ ፆታ _______
የትምሀርት ደረጃ _____________፣ በ9ኛ ክፍል አማርኛን በማስተማር ስንት
ዓመት ሰርተዋል ______________

ፐፐ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምርጫ ካላቸው ከተሰጡት ምርጫዎች የሚስማሙ በትን መልስ የያዘውን ፊደል ወይም ቁጥር በመክበብ፣ ወይም በተሰማሚ ቁጥር በማመልከት ይመልሱ፤ ምርጫ ለሌላቸው ጥያቄዎች ደግሞ በተወሰኑ አረፍተ ነገ ሮች መልስዎን ይግለጹ::

1. በዘጠነኛ ክፍል ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማ ርኛ ባለመሆኑ ምክንያት የተለየ የአማርኛ ቋንቋ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አጋጥምዎታል?

   ሀ. አጋጥመውኛል ለ. አላጋጠሙኝም

2. ለጥያቄ '1' መልስዎ አጋጥመውኛል ከሆነ የችግሩን ዓይነት ይግለጹ

______________________________________________

3. ተማሪዎችዎ የቋንቋውን ባህላዊ አገላለጾች/ለምሳሌ የጋብቻ፣ የወሊድ፣ የደስታ፣ የሀዘን፣ የበአላት፣ የዝምድና፣ ወዘተ ... ሁኔታዎች የሚገለጹባቸውን / በትክክል ይረዳሉ::

   ሀ. በሚገባ ይረዳሉ ለ. በመካከለኛ ደረጃ ይረዳሉ ሐ. በዝቅተኛ ደረጃ ይረዳሉ መ. በጭራሽ አይረዱም ሠ. አስተያየት የለኝም

4. ለዚህ ክፍል ተማሪዎች የበለጠ ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩት ክሂል የትኛው ነው? 1ኛ ፤ 2ኛ ፤ 3ኛ ፤ 4ኛ እያሉ በደረጃ ያመልክቱ

   ___ የማዳመጥ ክሂል
   ___ የመናገር ክሂል
   ___ የማንበብ ክሂል
   ___ የመጻፍ ክሂል

5. በጥያቄ '4' ለማዳመጥ ክሂል የሰጡትን የትኩረት ደረጃ አስመልክቶ ምክንያ ትዎን ቢገልጹ ______________________________________________

______________________________________________

6. የሚከተሉት የቋንቋ ትምህርት ዝርዝር አላማዎች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የተነደፉ ናቸው:: በአርስዎ አመለካከት እነዚህ ዝርዝር አላማዎች የተማሪዎችዎን ፍላጎትና ችሎታ ምን ያህል ያሟላሉ?

   5 = በጣም ከፍተኛ ደረጃ
   4 = በከፍተኛ ደረጃ
   3 = በአማካይ ደረጃ
   2 = በዝቅተኛ ደረጃ
   1 = በጣም በዝቅተኛ ደረጃ

6.1 የቋንቋ ችሎታቸውን ማዳበር 5 4 3 2 1

6.2 ተጠያቂ አስተሳሰብን ማዳበር 5 4 3 2 1

6.3 የተወሰነን ሃሳብ በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴን ማዳበር 5 4 3 2 1

7. እርስዎ ለዚህ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂሎታቸውን ለማዳበር ምን ምን አ[illegible]ማዎችን ይነድፋሉ:- ______________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

8. የሚከተሉት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ናቸው በእርስዎ አመለካከት እነዚህ ይዘቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል የማዳበር ብቃታቸው ምን ያህል ነው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

8.1 የቃላት ቀጥታ ትርጉም 5 4 3 2 1

8.2 የቃላትን፣ የሀረጋትና የአረፍተ ነገርን ትርጉም በአገባብ መረዳት 5 4 3 2 1

8.3 በግልጸ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት 5 4 3 2 1

8.4 የውይይት ስርዓት 5 4 3 2 1

8.5 የጭውውት ስርአት 5 4 3 2 1

8.6 የክርክር ስርዓት 5 4 3 2 1

8.7 ምስጢራዊ አነጋገሮችን መገንዘብ፣ መተርጎምና በነርሱም መገልገል/ቅኔ፣ዘይቤ የቋንቋ ሥነውበት/ 5 4 3 2 1

8.8 የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት 5 4 3 2 1

8.9 የሚያስፈልጉና የማያስፈልጉ ዝርዝር ሃሳቦችን መለየት 5 4 3 2 1

8.10 በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት

8.11 ፍሬ ሃሳቦችን በማስታወሻ መያዝ 5 4 3 2 1

8.12 አንዱን ርዕስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቀረብ 5 4 3 2 1

8.13 ሌሎች እዚህ ያልተጠቀሱና እርስዎ የተማሪ ዎችዎን ፍላጎት ያሟላሉ ብለው የሚያምኑባቸው የማዳመጥ ክሂል የሚያዳብሩ ይዘቶች ካሉ እባክዎ ይግለጹ:- ________________

________________________________

________________________________

________________________________

9. የዚህ ክፍል ተማሪዎች ቀጥሎ ባቀረቡት የማዳመጥ ክሂሎች ምን ያህል ችሎታ አላቸው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ

9.1 የማያውቋቸውን ቃላትና ሀረጋት ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት 5 4 3 2 1

9.2 በቃል የሚነገሯቸውን መመሪያዎች በቀላሉ መረዳት 5 4 3 2 1

9.3 በንባብ ወይም በንግግር ቀርቦላቸው ከሚያዳምጡት ውስጥ ዋናውንና ዝርዝር ሃሳቡን ለይተው መረዳት 5 4 3 2 1

9.4 በተለያየ ስዋሰዋዊ ቅንብር የሚቀርብላቸውን ሃሳብ አዳምጠው መረዳት 5 4 3 2 1

9.5 በመደበኛና በኢመደበኛ ንግግር መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ 5 4 3 2 1

9.6 በግራፍ፣በሰንጠረዥ ወይም በካርታ የተደገፉ መረጃዎችን አዳምጠው መረዳት 5 4 3 2 1

9.7 ከሚያዳምጡት ውስጥ ምክንያትና ውጤትን መለየት 5 4 3 2 1

9.8 የንግግር ድንድን ባህሪ መረዳት 5 4 3 2 1

9.9 የንግግሩን ድምፀት አዳምጠው መለየት 5 4 3 2 1

9.10 የሚያዳምጡትን ነገር አስቀድሞ ካላቸው ዕውቀት ጋር ማገናዘብ 5 4 3 2 1

9.11 በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን አዳምጠው መረዳት 5 4 3 2 1

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9.12 | በንግግር ውስጥ በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.13 | በንግግር ውስጥ ተናጋሪው የሚያተኩርባቸውን ነጥቦችና የንግግሩን አቋም መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.14 | ተናጋሪው በንግግሩ ወቅት ሃሳብ ለማስተዋወቅ፣ ሃሳብ ለማዳበር፣ ከአንዱ ሃሳብ ወደ ሌላ ሃሳብ ለመሸጋገርና ሃሳቡን ለማጠቃለል የሚጠቀምባቸውን ነጥቦች መለየት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.15 | ከሚነገረው ውስጥ ጠቃሚውን መረጃ ለይቶ ማዳመጥ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.16 | ከሚያዳምጡት ውስጥ የማይጠቅሙ መረጃዎችንና ድግግሞሽን መለየት አጣርቶ ማቀረብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.17 | በንግግር የቀረበላቸውን መረጃ አዳምጠው ወደ ግራፍ፣ሠንጠረዥ ወይም ካርታ መተርጎም | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.18 | ያዳመጡትን በራሳቸው አባባል ማቀረብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.19 | በሚያዳምጡት ተከታታይ ንግግር ወይም ምንባብ ውስጥ ወደፊት የሚነገረውን አስቀድሞ መገመት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9.20 | ከሚያዳምጡት ውስጥ ፍሬ ሃሳቡን ለይቶ ማስታወሻ መያዝ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

9.21 እዚህ ያልተጠቀሱ የተማሪዎችዎን የማዳመጥ ችሎታ የሚያሳዩ መረጃዎች ካሉ አባክዎ ይግለጹ፡- ________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

10. በአጠቃላይ ተማሪዎችዎ እንደሚያዳምጡ ከሚቀርብላቸው ውስጥ ምን ያህሉን አዳምጠው ይረዳሉ?

ሀ. ከ20% በታች　　ለ. ከ21–40%　　ሐ. ከ41–60%
መ. ከ61–80%　　ሠ. ከ80% በላይ

11. ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂሎቻቸውን ማዳበራቸው በዚህ ክፍል የሚሰጡ ትምህርቶችን ለመከታተል የሚሰጠው ጥቅም ምን ያህል ነው?

5 = በጣም ከፍተኛ
4 = ከፍተኛ
3 = መካከለኛ
2 = ዝቅተኛ
1 = በጣም ዝቅተኛ
0 = ምንም ጥቅም አይሰጥም

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11.1 | አማርኛ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.2 | እንግሊዝኛ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.3 | ሂሣብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.4 | ባዮሎጂ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.5 | ፊዚክስ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.6 | ኬሚስትሪ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.7 | ታሪክ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.8 | ጂኦግራፊ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.9 | እርሻ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.10 | ባልትና/የኑሮ ዘዴ/ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.11 | የምርት ቴክኖሎጂ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |
| 11.12 | እስፖርት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 0 |

12. በ1984 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በአሁኑ ጊዜ እየተሰራበት ባለው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት በቀረቡት ይዘቶች ላይ ያለዎትን አጠቃላይ አስተያየት ቢገልጹ:- ______________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

አባሪ 3

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**
**የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት**

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት /ሲለበስ/ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶችን ለመገምገምና ለመተንተን የተዘጋጀ መጠይቅ::

## የመርሀ ትምህርት ባለሙያው መጠይቅ

**መግቢያ፡**

የዚህ መጠይቅ አላማ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የተማሪውን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የሚቀርብለትን የትምህርት ይዘት በተመለከተ በመርሀ ትምህርት ውስጥ የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች በተማሪው የቋንቋ ፍላጎትና ችሎታ ላይ ተመስርተው የተመረጡ መሆን አለመሆናቸውንና ብቃታቸውን ለመፈተሽ ለሚደረገው ጥናት መረጃ መሰብሰብ ነው::

አላማው ግቡን ሊመታ የሚችለው ስርአተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት በመንደፍ፣ የማስተማሪያ መጽሀፍትን በማዘጋጀትና በማስተማር ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የቋንቋውን ትምህርት ይዘት በተመለከተ አስተያየታቸውን በመሰንዘር ቀና ትብብር ሲያደርጉ እንደሆነ ይታመናል:: በዚህም መሠረት እርስዎም በዚህ መጠይቅ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ ለጥናቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በመገንዘብ መጠይቁን በመሙላት እንዲተባበሩ በትህትና እንጠይቃለን:: ስለ ትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን::

I. ግላዊ መረጃ

አፍ መፍቻ ቋንቋ ____________ የሥራ መደብ ____________

የትምህርት ደረጃ ____________ ልዩ ሥልጠና ____________

አሁን ባሉበት የሥራ መስክ ስንት ዓመት ሰርተዋል ____________

II. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች የሚስማማዎትን መልስ የያዘው ፊደል ወይም ቁጥር በመክበብ ይመልሱ::
መልስዎ ከቀረቡት ምርጫዎች የተለየ ከሆነ በተተወው ክፍት ቦታ ላይ በተወሰኑ አረፍተ ነገሮች መልስዎን ይግለጹ::

1. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው:-
   ሀ. በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ነው::
   ለ. በሁለተኛ ቋንቋነት ነው::
   ሐ. የተለየ መልስ ካለዎት ይግለጹ ____________________
   ____________________________________________

2. ለዘጠነኛ ክፍል የሚሆኑ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲመረጡ ለተገቢነታቸው በመመዘኛነት የታየው ምንድነው?
   ሀ. የተማሪዎች ፍላጎት
   ለ. የተማሪዎች ችሎታ
   ሐ. ቋንቋው በትምህርት ቤት የሚሰጠው አገልግሎት
   መ. ቋንቋው በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት
   ሠ. የቋንቋው ሥነ ልሳናዊ ባህሪ
   ረ. መልስዎ እዚህ ከተጠቀሱት የተለየ ከሆነ ይግለጹ ________________

   ________________________________________________

3. ለዚህ ክፍል የሚሆኑ ወርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጽሀፍት የሚዘጋጁት በአንድ ቡድን /ፓነል/ ነው?

   ሀ. አዎ                ለ. አይደለም

4. ለዚህ ክፍል ተማሪዎች በሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች /ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍ/ መሀከል ለማዳመጥ ክሂል ምን ያህል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለው ያምናሉ?
   ሀ. ከአራቱ ክሂሎች መሀከል በአንደኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።
   ለ. ከአራቱ ክሂሎች መሀከል በሁለተኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።
   ሐ. ከአራቱ ክሂሎች መሀከል በሦስተኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።
   መ. ከአራቱ ክሂሎች መሀከል በአራተኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።
   ሠ. የተለየ አስተያየት ካልዎት ይግለጹ ________________

   ________________________________________________

5. በጥያቄ "4" ለማዳመጥ ክሂል የሰጡትን የትኩረት ደረጃ አስመልክቶ ምክንያትዎን ቢገልጹ? ________________________________________________

   ________________________________________________

   ________________________________________________

6. የሚከተሉት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ናቸው። በእርስዎ አመለካከት እነዚህ ይዘቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል የማዳበር ብቃታቸው ምን ያህል ነው?

   የስምምነትዎን መጠን ከተሰጡት ምርጫዎች የአንዱን ቁጥር በመክበብ ያመልክቱ፡-

   5 = በጣም ከፍተኛ
   4 = ከፍተኛ
   3 = መካከለኛ
   2 = ዝቅተኛ
   1 = በጣም ዝቅተኛ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6.1 | የቃላት ቀጥታ ትርጉም | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.2 | የቃላትን፣ የሀረጋትና የአረፍተ ነገርን ትርጉም ከአገባብ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.3 | በግልጽ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.4 | የውይይት ስርዓት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.5 | የጭውውት ስርዓት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.6 | የክርክር ስርዓት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.7 | ምስጢራዊ አነጋገሮችን መገንዘብ፣ወትር ጉምና በነርሱም መገለገል/ቅኔ፣ዘይቤ፣ የቋንቋ ስነ ውበት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.8 | የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.9 | የሚያስፈልገውና የማያስፈልገው ዝርዝር ሃሳብ ችን መለየት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.10 | በጭብጥና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.11 | ፍሬ ሃሳቦችን በማስታወሻ መያዝ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6.12 | አንዱን ርዕስ ጉዳይ በራስ አባባል መቅረብ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

7. በዘጠነኛ ክፍል ወርሀ ትምህርት ላይ የማዳመጥና ክሂል ለማዳበር የተመረጡ አላማዎችንና ይዘቶችን በተመለከተ የሚሰጡት አስተያየት ካለዎት ይግለጹ

________________________________________

________________________________________

________________________________________

...

አባሪ 4   የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት አወቃቀር

| የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ | ዝርዝር አላማ | ይዘት | የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን | ግ ም ገ ማ |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| 1. የማዳመጥና መናገር ክሂሎችን ያዳብራል፤ | | | | |
| 2. የማንበብ ክሂልን ያዳብራል፤ | | | | |
| 3. የመጻፍ ክሂልን ያዳብራል፤ | | | | |
| 4. የሥነ ልሣን እውቀትን ያዳብራል፤ | | | | |
| 5. የስነ ጽሁፍ እውቀትን ያዳብራል፤ | | | | |

አባሪ 5 ጥናቱ ያቀረበተ የመርሀ ትምህርቱ ክፍል

አንደኛ ሴሚስተር

| የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ | ዝርዝር አላማ | ይዘት | የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን | ግ ም ገ ማ |
|---|---|---|---|---|
| የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራሉ፡፡ | ተጠያቂ አስተሳሰብን ያዳብራሉ፡፡ | 15. የውይይት ስርአት | 1. ለውይይት ከመቀረበበፊት ስለርዕሱ ... ጠቃሚ ሀሳብ ማግኘት ተገቢ መሆኑን ማለማመድ፡፡<br>2. ተማሪዎችን በቡድን መድቦ ... አንዱ ሲወያይ ሌላው አዳምጦ አስተያየት እንዲሰጥ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>3. በውይይት ጊዜ ተራቸውን ጠብቀው እንዲናገሩና እንዲጠይቁ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>4. ... ሀሳቦችን በስዕል፡ በሰንጠረዥ፡ በካርታ በግራፍ፡ ወዘተ ... አስደግፈው ማቅረብ እንዲችሉ ማስተማር፡፡<br>5. የውይይቱን ፍሬ ነገር በውሳኔ ሃሳብ መልክ ... የማሳለፍ ወይም የመጣል ስርአትን እንዲያውቁ ማለማመድ፡፡ | 1. ለውይይት ከመቀረባቸው በፊት መረጃ ሀሳቦችን መሰብሰብ መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡<br>2. ... ተራቸውን ጠብቀው አስተያየት ... ጥያቄ ... መቻላቸውን መከታተል፡፡<br>3. ሀሳቦችን በልዩ ልዩ መገለጫዎች አስደግፈው ማቅረብ....<br>4. የውሳኔ ሃሳብ የማሳለፍ /የመጣል/ ስርአትን መለመዳቸውን ... |
| | | 16. የክርክር ስርአት፡፡ | 1. ክርክር ለማሸነፍ የተቃዋሚን ደካማ ጎን መረዳት እንደሚያስፈልግ ... ማለማመድ፡፡<br>2. ከክርክር በፊት ... ስለርእሱ ... ነጥቦችን መሰብሰብ እንዳለባቸው ማለማመድ፡፡<br>3. ስለሰሙት ክርክር በምክንያት የተደገፉ አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>4. የክራካሪዎች አሸናፊነት የሚወሰነው በሚያቀርቡት ነጥቦች ብዛትና የማስረጃ ጥንካሬ መሆኑን በደረጃው ማለማመድ፡፡<br>5. ... በቡድን መድቦ አንዱን ርዕስ በመደገፍና በመቃወም እንዲከራከሩ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>6. ... ተስናቆጥውና ሳይሰናቁ መከራከር፡፡<br>7. ... ተቃዋሚ ክፍል ከሚያቀርበው ሀሳብ መከራከሪያ ነጥቦች ሊገኙ እንደሚችሉ ማስገንዘብ፡፡ | 1. ስለሰሙት ክርክር በምክንያት የተደገፈ አስተያየት መስጠት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡<br>2. በመደገፍ ወይም በመቃወም መከራከር መቻላቸውን ...፡፡<br>3. ... ተስናቆጥውና ሳይሰናቁ መከራከር መቻላቸውን፡፡<br>4. የተቃዋሚ ክፍል ከሚያቀርበው ሀሳብ የመከራከሪያ ነጥቦች ማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡ |

| | የጠቅላላ ትምህርቱ አጠቃላይ አላማ | ዝርዝር አላማ | ይዘት | የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን | ግ ም ገ ማ |
|---|---|---|---|---|---|
| አንደኛ ሴሚስተር | | | 17. የጭውውት ስርአት | 1. ካዳመጧቸው ጭውውቶች ... መርጠው ለክፍል ጓደኞቻቸው ማቀረብ፡፡<br>2. ጭውውት በቀልዱና በፌዝ ሳቅ ብቻ የተወሰነ አለመሆኑንና ቁም ነገር በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንደሚደረግ ማለማመድ፡፡ | በሬዲዮና በቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ከሰሟቸው ጭውውቶች መካከል:—<br>ሀ. ጠቃሚ መስለው የሚታዩአቸውን ለጓደኞቻቸው ማቀረብ ፡፡<br>ለ. ፕሮግራም አቀራረባቸውን መስለው ማቀረብ መቻላቸውን መመልከት፡፡ |
| ሁለተኛ ሴሚስተር | የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራሉ፡፡ | የተወሰነን ሀሣብ በራስ አባባል የማቀረብ ዘዴን ያዳብራሉ፡፡ | 16. የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት | 1. ... በአንዱ ሁኔታ ላይ ውጤት ሆኖ የቀረበ ነገር በሌላ ሁኔታ ላይ መንስኤ ሊሆን እንደ ሚችል በማስረዳ ... ማለማመድ ፡፡<br>2. መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ... ሁኔታዎች ጠቀስ.. ሊከተል የሚችለውን ድርጊትና ውጤቱን እንዲገልጹ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>3. ... አንዱ ድርጊት አቀርቦ ... መነሻ ሊሆን የሚችለውን በጽሑፍም ሆነ በንግግር እንዲገልጹ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>4. መንስኤ ለድርጊት መፈጠር ምክንያት ሲሆን ከድርጊት በኋላ ደግሞ ውጤት የሚገኝ መሆኑን በልዩ ልዩ መለመጃዎች ማስተማር፡፡<br>5. ... የመንስኤና የውጤትን ግንኙነትና ልዩነት የሚያስረዱ በማድረግ ማለማመድ፡፡<br>6. የተወሰኑ ርእሶችን መርጦ በሁለት በመክፈል በአንዱ ረድፍ የገማቹን መነሻ፡ በሌላ ረድፍ የሌሎችን ድርጊቶች ውጤት በመሰጠት እያገናኙ ተማሪ በመረጠው ርዕስ አጠር ያለ መግለጫ ጽፎ እንዲያቀርብ በማድረግ ማለማመድ፡፡ | 1. ከአንዱ መነሻ ከሆነ ነገር ሊከተሉ የሚችሉትን ድርጊቶችና የድርጊት ውጤቶች ተከታትለው መግለጽ መቻላቸውን፡ማየት፡፡<br>2. የመንስኤና የውጤትን ግንኙነትና ልዩነት ከሰጧቸው መለመጃ መረዳት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡ |

[ሁለተኛ ሴሚስተር]

| የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ | ዝርዝር አላማ | ይዘት | የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሥራ ክንውን | ግምገማ |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| ሌሎች ክሂሎችን ለማ ዳበር ተመርጠው እግረ መንገዳቸውን የማዳመጥ ክሂል የሚያዳብሩ ይዘቶች። | | 22. በጥብቅና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት<br>23. ፍሬ ሀሳቦችን በማስ ታወሻ መያዝ<br>24. አንድን ርእስ ጉዳይ በራስ አባ ባል ማቀረብ | ቆ. ከሰሙት ንግግር .... ሀቆችንና ስሜታዊ አስተያየቶችን ለየብቻ በመዘርዝር .... ያሳቸውን ምክንያት በዝርዝር እንዲናገሩ በማድረግ ሀቁና ስሜታዊ አስተያየትን መለየት እንደቻሉ ማለማመዱ ።<br>1.... ካዳመጡት ያገኙትን ፍሬ ሀሳብ በማስታወሻ እንደወሰዱ ...<br>2. .. ያዳመጡትን ዜና ዋና ሃሳብ በማስ ታወሻ ይዘው<br>3. ... ውይይቶችን እያዘጋጁ በማቀረብ ሀሳቡን በራሳቸው አባባል አቀነባበረው | |

አባሪ 6 በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተለያዩ ክሂሎችን ለማዳበር እንደረዱ ከቀረቡት መምሪያዎች ከማዳመጥ ጋር ግንኙነት ያላቸው::

## የማዳመጥ መምሪያ

1. ማዳመጥ መልአክት መቀበያ መሆኑን ተገንዘብ::
2. ማንኛውም መልአክት በቃል ሲነገርህ ወይም ሲነበብልህ በጥሞና አዳምጥ
3. አንዱ መልአክት በታዳምጥ ጆሮችህን ብቻ ሰጥተህ ጭጭ አትበል::
4. የሰዎችን ንግግር ስታዳምጥ አታቋርጣቸው:: ማቋረጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በስርዓት ይቅርታ በመጠየቅ ያቋረጥከበትን ምክንያት ጠይቅ::
5. ካዳመጥከው ሃሳብ ውስጥ ስህተት የሆነ ነገር ተሰንዝሮ ከሆነ ፊት ለፊት ልክ አይደለም፣ ስህተት ነው፣ ከማለት ይልቅ ስርአት ባለው መንገድ ያል ተስማማህበትን ሃሳብ ከነምክንያቶቹ በጥሞና ለማስረዳት ሞክር::
6. ለሰዎች ንግግር ተገቢውን ግምት ሰጥ እንጂ በንቀት መንፈስ ለማንኳሰስና ለማጥላላት አትሞክር::
7. ካዳመጥከው ንግግር ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን ለመለየት ሞክር::
8. ያዳመጥከውን ፍሬ ሃሳብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በጽሁፍ አዘጋጅ::
9. ያዳመጥከውን ፍሬ ሃሳብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሳታዛባ ለሌሎች አስተላልፍ / ገጽ 85/

## የማስታወሻ አያያዝ መምሪያ

1. ማስታወሻ የሚያዝባቸው:-
   1.1 በምታዳምጥበት ጊዜ፣
   1.2 ዝግጅት በምታደርግበት ጊዜ፣
   1.3 በግል በምታነብበት ጊዜ ወዘተ ...፣
2. ማስታወሻ ወረቀትና ብእር ወይም እርሳስ ይኑርህ::
3. ዋና ዋና ሃሳቦችን በቃላት፣ በሀረግና በዐ/ነገር ጻፍ::
4. ሁሉን ነገር ሳይሆን ዋና ዋና መረጃዎች ናቸው የምትላቸውን ጻፍ::
5. በዘገባ መልክ እንድትዘጋጅ ከተነገረህ ግልጽ በሆነና ቀደም ተከተሉን ጠብቀህ ሳታንዛዛ፣ ሳትጨምርና ሳትቀንስ አቅርብ::/ገጽ 87–88/

## የውይይት ዝግጅትና አቀራረብ መምሪያ

ውይይት አላማ ያለው በእቅድ የተዘጋጀና የአንድን ርእስ ጉዳይ የተለያዩ ገጽታዎችን የሚመለከት ነው::

1. <u>የውይይት ዝግጅት መምሪያ</u>

1.1 ርእስን በሚገባ ማስተዋል፣

1.2 ርእሱን በሚመለከት ረገድ፣

1.2.1 ወደ ቤተ መጽሀፍት በመሄድ በርእሱ የተዘጋጁ ልዩ ልዩ ጽሁፎችን በማንበብ ፍሬ ሃሳቦችን ሰብስብ::

1.2.2 ስለ እርሱ የጠለቀ እውቀት ካላቸው ሰዎች ጋር በቃለምልልስ በመነጋገር ፍሬ ነገሮችን ውሰድ::

1.2.3 የሰበሰብካቸውን ነጥቦች በቅደም ተከተል አዘጋጅ::

1.2.4 ዝግጅትህ ከተደራሲያኑ ፍላጎት፣ ልምድና እውቀት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን አጢን::

1.2.5 ዝግጅትህ ሁሉን የሚያሳትፍ፣ የሚያነጋግርና የሚገፋፋ መሆኑን አስተውል፣

1.2.6 ዝግጅትህ የርእሱ ጉዳዩን የተለያዩ ገጽታዎች የሚዳስስ መሆኑን አስተውል::

1.2.7 ዝግጅትህ ወቅታዊ መሆኑን አረጋግጥ::

1.2.8 የዝግጅትህን ጠቃሚነት ገምግም::

2. <u>የውይይት አቀራረብ መምሪያ</u>

2.1 ለውይይት ስትቀርብ ሰብእናህን አሟላ:: ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል

2.1.1 አለባበስን

2.1.2 ንጽህናን

2.1.3 ሥነ ምግባርን

2.2 የውይይቱን አላማ አስተዋውቅ::

2.3 የውይይቱን ርእስ አስተዋውቅ::

2.4 የውይይትህን ጭብጥ በቅደም ተከተል ለተደራሲያኑ አቅርብ::

2.5 ውይይትህን በምታቀርብበት ጊዜ ለተደራስያን እንዲሰማ —ቸው ባለ ድምጽ ተናገር::

2.6 ውይይትህን በምታቀርብበት ጊዜ ሳትፈራና ግድየለሽ ሳትሆን ስርአት ባለው መንገድ ውይይትህን አቅርብ::

2.7 የውይይቱ ሃሳብ ተቀባይነትን እንዲኖረው በቂ ምክንያትና ማስረጃ አቅርብ::

2.8 በተቻለ መጠን ተደራሲያንን በአገላለጽህ አርካ::

2.9 ውይይትህ ፍሬያማ እንዲሆን ጥረት አድርግ::

2.10 ውይይትህ ፍሬ ሃሳብ ካቀረብክ በኋላ ለተደራስያን የጥያቄና የአስተያየት መስጫ ጊዜ እንዲኖር አድርግ::

2.11 ውይይትህ በተወሰነው የጊዜ ገደብ እንዲያበቃ አድርግ::

2.12 ከተደራስያን የሚቀርቡትን አስተያየቶችና ጥያቄዎች በሚገባ በማዳመጥ ማስታወሻ በመያዝ ተጨባጭና መፍትሄ የሚሆኑ ሃሳቦችን አቅርብ::

2.13 ተደራሲያንን በጥሞናና በሥነ ስርአት ስላዳመጡህ አመስግን::

## የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ መምሪያ

ክርክር ሁለት ሰዎች ወይም ሁለት ቡድኖች ጎኖች በመሰየም የሚያደርጉት ስርአት ያለው ሙግት ነው::

1. የክርክር ዝግጅት፤
   - 1.1 ርእሱን በሚመለከት ከተለያዩ ምንጮች ሃሳብ መሰብሰብ::
     ለምሳሌ:-
     - 1.1.1 ከባለሙያዎች
     - 1.1.2 ከልዩ ልዩ ጽሁፎች
   - 1.2 በርእሱ መሠረት ጠይቀህ ካገኘኸውና ካነበብከው ለክርክርህ ጠቃሚ የሆኑትን ሃሳቦች በቅደም ተከተል አስተካክለህ ያዝ::
   - 1.3 ክርክርህን ለአድማጮች ከማቅረብህ በፊት ልምምድ አድርግ::
   - 1.4 ለክርክር ከመቅረብህ በፊት ሰብእናህን በስነ ስርአት አሟላ::

2. የክርክር አቀራረብ:-
   - 2.1 የመከራከሪያ ርእስህን ለአድማጮች አስተዋውቅ::
   - 2.2 የክርክርህን ፍሬ ሀሳቦች በቅደም ተከተል አቅርብ::
   - 2.3 ክርክር በምታደርግበት ጊዜ ረጋ ካለ መንፈስ በልበ ሙሉነት አቅርብ
   - 2.4 ከክርክርህ ጋር የማይስማማ እንቅስቃሴ አታድርግ
   - 2.5 ተቃዋሚህ የሚሰጠውን ሃሳብ በትክክል በማዳመጥ ማስታወሻም በመያዝ የተቃውሞ ሃሳብ አዘጋጅ::
   - 2.6 አነስተኛ ወይም ብጣሽ ወረቀት ለመያዝ ብትችል ማንበብህና መያዝህ እንዳይታወቅ አድርግ፤:
   - 2.7 የምታቀርበው ሃሳብ ወይም ማስረጃ በአድማጮችህ ችሎታ የተመጠነ ይሁን::
   - 2.8 ለክርክር የተሰጠህን የጊዜ ገደብ አክብር::
   - 2.9 በክርክር ወቅት ከርእስህ ውጪ የሆነ ሃሳብ እንዳታቀርብ ጥንቃቄ አድርግ::
   - 2.10 ክርክርህን ስታበቃ አድማጮችህን አመስግን::/ገጽ 95/

## በጽሁፍና በንግግር ላይ አስተያየት ማቀረብ፣

አስተያየት የአንድን ጽሁፍ ወይም የአንድን ንግግር ጠንካራና ደካማ ጎን ከስሜታዊነት ነጻ በሆነ መንገድ ከ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ የራስን ሃሳብና አመለካከት የሚያቀርቡበት ዘዴ ነው:: በመሆኑም አስተያየት ከማቀረብህ በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች አስተውል::

1. የቋንቋ አጠቃቀም
   1.1 የቃላት አመራረጥ
   1.2 የሀረጎች አመራረጥና አሰካክ
   1.3 የአረፍተ ነገሮች ቀንበር
2. የተለየ የአጻጻፍና የንግግር ስልት መከተሉ አለመከተሉን፣
3. አስተያየት የምትሰጥበት ጽሁፍ ወይም ንግግር ግልጽነት ያለው መሆን ያለመሆኑን፣
4. የጽሁፍ ወይም የንግግሩ ይዘት፣
   4.1 የሚታመን ወይም የማይታመን መሆኑን፣
   4.2 ከኅብረተሰቡ አቋም ጋር ያለውን ዝምድና፣ ቀራኒና ተቀባይነቱን፣
   4.3 የሃሳቡን ከበደትና ቀለት መመዘን፣
5. የጽሁፍ የንግግሩ ዋና መልእክት ምን እንደሆነ በመመርመርና በማወቅ አስተያየት መስጠት::
   5.1 የጽሁፉን ወይም የንግግሩን መልእክት መገምገም፣
   5.2 ጽሁፉ ወይም ንግግሩ የሚሰጠውን ትምህርት ከራስ አስተሳሰብ ጋር ማዛመድ፣
   5.3 ከተለያዩ ምንጮች ሃሳቦችን በማሰባሰብ አስተያየትህን አጠናክር::

/ገጽ 99–100/

አባሪ ፡ 7፡ በአዲስ አበባ የሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በፊደል ተራ ቅደም ተከተላቸው መሠረት፡-

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ሊሴ ገ/ማርያም | ከፍተኛ | ሁለተኛ | ደረጃ | ት/ቤት |
| 2. መድኃኔዓለም | " | " | " | " |
| 3. ምሥራቅ አጠቃላይ | " | " | " | " |
| 4. ሽመለስ ሀብቴ | " | " | " | " |
| 5. ቅዱስ ዮሴፍ | " | " | " | " |
| 6. ቅድስተ ማርያም | " | " | " | " |
| 7. ቦሌ | " | " | " | " |
| 8. ተግባረዕድ | " | " | " | " |
| 9. ናዝሬት | " | " | " | " |
| 10. ንፋስ ስልክ | " | " | " | " |
| 11. እቴጌ | " | " | " | " |
| 12. አብዮት ቅርስ | " | " | " | " |
| 13. አወልያ | " | " | " | " |
| 14. አየር ጤና | " | " | " | " |
| 15. አዲስ ከተማ | " | " | " | " |
| 16. ኢትዮጵያ ትቅደም | " | " | " | " |
| 17. ኤስ ኦ ኤስ | " | " | " | " |
| 18. እንጦጦ | " | " | " | " |
| 19. ከፍተኛ 4 | " | " | " | " |
| 20. ከፍተኛ 7 | | | | |
| 21. ከፍተኛ 12 | " | " | " | " |
| 22. ከፍተኛ 20 | " | " | " | " |
| 23. ኮልፌ | " | " | " | " |
| 24. ኮከበ ጽባህ | " | " | " | " |
| 25. ወንድይራድ | " | " | " | " |
| 26. ዊንጌት | " | " | " | " |
| 27. የካቲት 12 | " | " | " | " |
| 28. ዳግማዊ ምኒሊክ | " | " | " | " |
| 29. ጥቁር አንበሳ | " | " | " | " |

/ ከክልል 14 ት/ቤቶች ጽህፈት ቤት ትምህርት ክፍል የተገኘ መረጃ/

መግለጫ :-

ይህ ቴሲስ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና በሌላ በየትኛውም ዩኒቨርሲቲ ያልቀረበ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ ።

ስም = አቴነሽ ተገኝ

ፊርማ = ____________

ቦታ = የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ ፲ 1986